# የተሐድሶ ጥሪ

## መመርመር - መመለስ - መታደስ

# የተሐድሶ ጥሪ

## መመርመር - መመለስ - መታደስ

## በግልም በቤተ ክርስቲያንም ደረጃ

*"እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን፤
ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ" ሰቆ. 5፥21*

በመንፈሳዊ ተሐድሶ ፎረም

1. ቢብሊካ ኢትዮጵያ
2. የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ምሩቃን ማኅበር (EvaSUE)
3. ደወል የወንጌል አገልግሎት
4. ቃለ እግዚአብሔር አንባብያን ማኅበር
5. ኀልደን አይል አገልግሎት
6. ኢቫንጀሊካል ቲዮሎጂካል ኮሌጅ (ETC)

በጋራ አስተባባሪነት የተዘጋጀ

ሰኔ 5-6 ቀን፣ 2007 ዓ.ም.
ኢቫንጀሊካል ቲዮሎጂካል ኮሌጅ

## በጽሑፍ ዝግጅት ላይ የተሳተፉ ግለ ሰቦች

1. ወንድም ፈቀደ ተፈራ
2. ወንድም አክሊሉ ይልማ
3. ወንድም በልሁ ደለለኝ
4. ደሳለኝ ደምሴ (ወንጌላዊ)
5. ወንድም ያሬድ ጥላሁን (ወንጌላዊ)
6. ፍሬው ታምራት (ዶ/ር)
7. ንጉሴ ተፈራ (ዶ/ር)
8. ዓለም ባዘዘው (ዶ/ር)
9. ፈቃዱ ታደሰ (መጋቢ ዶ/ር)
10. ስምዖን ሙላት (ዶ/ር)
11. አታላይ አለም (ፕሮፌሰር)
12. ስዩም አንቶኒዮስ (ዶ/ር)
13. ተስፋዬ ጋቢሶ (መጋቢ)
14. በፈቃዱ አትመው (መጋቢ)
15. ወንድም ዳንኤል ይልማ
16. ወንድም ቴዎድሮስ በየነ
17. ወንድም አክሊሉ በቀለ
18. ወንድም የኋላሸት ካሳ
19. ወንድም ሚክያስ በላይ
20. ወንድም ናሁሠናይ አፈወርቅ
21. ወንድም ንጉሴ ቡልቻ
22. ወንድም ሰለሞን ከበደ

# ተሐድሷዊ ጉዞ

*መመርመር -- መመለስ -- መታደስ*

በግልም በቤተ ክርስቲያንም ደረጃ

## አጠቃላይ መግቢያ

*“እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን፤*

*ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ” ሰቆ 5፥21*

በኢትዮጵያ ያለችው ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ ምኅዳሮች ውስጥ እያለፈች እዚህ ደርሳለች፡፡ ያለፈችባቸው ሁኔታዎች በአካሄዷ ላይ የራሳቸውን ተጽእኖ እንዳሳደሩባት የታወቀ ነው፡፡ በስደት በተጓዘችባቸው ዓመታት በኅብረት መሰብሰብ አስቸጋሪ ሆኖ፣ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የማምለኪያ ቦታቸውን አጥተው በኅቡዕ በመደራጀት በመኖሪያ ቤቶች መሰብሰብ ተገደው ነበር። የተዘጉት በከፍተኛ ስደት ውስጥ ሲያልፉ አንጻራዊ ነፃነት የነበራቸው ደግሞ በአመዛኙ አገልግሎታቸውን ለማስቀጠልና ወደ እነርሱ ለመገልገል የመጡትን ለማስተናገድ በራቸውን በመክፈት ተጠምደው ቆይተዋል።

በወቅቱ የነበረው ስደት የራሱ የሆነ ተጽእኖ በቤተ ክርስቲያን ላይ ቢያሳድርም በዚያ ጊዜ የነበረው ወንጌላዊው ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ በአብዛኛው የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ የሚያስቀድም ቁርጠኛ ወገን ነበረ። ለፍቅር፣ ለአንድነትና ለኅብረት ነፍሱ የነቃች በጉጉት ወደ እግዚአብሔር ማኅበር የሚገሰግስ፣ ለሕይወት ንጽሕና ክቡር ስፍራ የሚሰጥ ጠንቃቃ ሕዝብ ነበረ። በዚህም ምክንያት በሚቃወሙት የኅብረተ ሰብ ክፍሎች እንኳ ስለ ታማኝነትና ትጉሕ አገልግሎት በየቦታው የሚፈለግ ማኅበረ ሰብ ነበረ። በስቃይና በመከራ ውስጥም የወንጌልን ብርሃን በየጥሻው ለመለኮስ ቅንዓት ነበረው፤ በዚያ ሁኔታ የማይጠበቅ ትልቅ ዕድገት በቤተ ክርስቲያን ተከስቷል። በቤት፣ በሰፈር፣ በትምህርት ቤት፣ በመሥሪያ ቤት፣ በየስፍራው ሁሉ በታላቅ መሥዋ ዕትነት ከጌታው ጋር ለመኖር የቆረጠ በእጦቱ ለመጽናት፣ ሀብት ንብረቱን፣ ሹመት ማዕረጉን እንኳ ስለ ጌታና ስለ ወንጌሉ ሲል ለማጣት ዝግጁ የሆነ ብርቱ ማኅበረ ሰብ ነበረ።

የስደቱ ዘመን አልፎ የነጻነት ወቅት ሲተካ ለቤተ ክርስቲያን ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ፤ ደጆች ተከፈቱ፤ ወንጌል ሥርጭት አደባባይ ወጣ፤ የጀማ ስብሰባዎችና መነቃቂያዎች ቀድሞ በማይታሰቡ የሕዝብ መሰብሰቢያ ሥፍራዎች መካሄድ ጀመረ። የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መመሥረትም በቤተ እምነቶች መካከል መቀራረብን ሲፈጥር የወንጌል ተልእኮን ሥራም በቅንጅት ለማካሄድ ዕድል አመቻቸ። በአንድ በኩል መተናነጽ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ልምድና አገልጋይ መለዋወጥ በአማኞች መካከል የነበረውን ኅብረት በመጥቀም ረገድ የነበረው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነበር።

ለእግዚአብሔር ክቡር ይሁንና በምድራችን በተከበረው የእምነት ነጻነት የተነሣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት እየሰፋ መምጣት ብቻ ሳይሆን ለበለጠ ዕድገትና ተሳትፎ ያለው ተስፋ እየጨመረ መጥቷል። እነዚህ አመቺ ሁኔታዎች ብዙዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲጨምሩ፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቍጥር ከእጥፍ በላይ እንዲጨምር፣ በኅብረተ ሰቡም ውስጥ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴና ተሳትፎ የበለጠ ዕውቅና እንዲያገኝ ረድቷል። ከምንጊዜውም ይልቅ ዛሬ የአገልጋዮችና የአገልግሎቱም መንገድና ዐይነት እየበረከተ መጥቷል።

በዚህ ሁሉ መልካም አጋጣሚ መካከል በቍጥር እየጨመረ የሚሄደው የአማኞች ብዛትና ያንንም ተከትሎ የሚተከለው ቤተ ክርስቲያን መበራከት ብዛት ያላቸው አገልጋዮችን ይበልጥ አስፈላጊ እያደረገ ሄደ። ይህንንም ተከትሎ የተጠናከሩትና አዲስ የተከፈቱት የነገረ መለኮት ትምህርት ቤቶች ለብዙዎች ዐይን ገላጭ በመሆንና ደርዝ ያለው ትምህርት ምን ያህል ፋይዳ እንዳለው አመላካች መሆን ጀመሩ። የእነዚህ ተቋማት መብዛትም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና አመራር ላይ የራሱን መልካም አሻራ ማሳረፍ ችሏል። እየታዩ ላሉት በጎ ሥራዎች ሁሉ ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሁን።

እነዚህ በጎ ሁኔታዎች የሚያበረታቱን ቢሆንም እንኳ፣ ነጻነት ካልተከበረበት ዘመን አንጻር ሲታይ ዛሬ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ያሉበትን ሁኔታ በአንክሮ ለሚያጤን ሰው እጅግ አሳሳቢ ጉዳዮች በፊታችን እንደተደቀኑ በግልጽ የሚታይና በርካታ ጥያቄዎችን የሚያስነሣ ነው።

- ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠንን ሰፊ የወንጌል አገልግሎት ዕድል በአግባቡና በብቃት እየተጠቀምንበት ነው ወይ?
- እግዚአብሔር ከሰጠን ሰፊ የእምነት ነጻነትና ከአገልግሎት እድል አኳያ ሲታይ በኅብረተ ሰቡ ዘንድ የሚጠበቀውን ያህል በጎ ተጽእኖ ማሳደር ችለናል ወይ? ኑሮአችንና አካሄዳችን ጌታን የሚያስከብር፣ የጌታ መሆናችንን በግልጥ የሚያሳይ መልካም ምስክርነት ያለው ነው ወይ?
- በብዙ ስፍራና ሁኔታዎች የሚገለጠው አስተምህሯችንስ እውነትን የሚያሳይና የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል የሚገልጥ ነው ወይ? ወይስ ለብዙዎች ግራ የሚያጋባና ሲያልፍም ለስሕተት የሚዳርግ ሆኖ ነው የሚታየው?
- አስተዳደራችን ጽድቅንና ፍትሕን መቀባበልንና መከባበርን ያሳያልን?
- የቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር መርሐችን ምን ያህል መንፈሳዊና በጎ ሥነ ምግባርን የተከተለ ነው?
- ችግሮቻችንን በሰከነ አመራር በመንፈሳዊ አካሄድና እግዚአብሔርን በመፍራት መንገድ መፍታትስ ችለናል ወይ?
- ይቅርታ ማድረግና እርቅን በሚመለከትስ በውስጣችን የሚታየው ገጽታ ምን ይመስላል?

የሚሉትና ሌሎችም ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን አጠቃላይ የአመራር፣ የአስተምህሮና የአምልኮ አቅጣጫዎቹን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ደጋግመው እየተነሡ ነው፡፡

ስለሆነም ዛሬ ያለንበትን ሁኔታ መልካሙንም ደካማውንም በተለያየ አቅጣጫ ያጋጠሙንን ቀውሶች በየፈርጁ ማስቀመጥና ማየት የወቅቱ ጥያቄ መሆን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የጣለብን አደራ መሆኑን እናምናለን። በተለይ በአሁኑ ጊዜ በመካከላችን እየገዘፉ ለመጡት ተግዳሮቶች ወቅታዊ ምላሽ መስጠት ካልቻልን አገልግሎታችን ሁሉ አሳፋሪና አስከፊ እንደሚሆን፣ አንድነታችንና ኅብረታችን እንደሚደክምና እንደሚፍረከረክ ያገኘናቸውም የአገልግሎት ዕድሎች ሁሉ ሊመክኑ እንደሚችሉ የሚያጠራጥር አይሆንም።

በተለይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን በመምራት በተለያየ ቦታና ኀላፊነት ላይ ያለን ሁላችን ይህንን ሰማያዊ ዐደራ በቻልተኝነት ልንመለከተው እንዴት እንችላለን? ቃሉ የሚለን "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (ሐዋ. 20፥28) ነው። ለዚህ ተግዳሮት መልስ በመስጠት ቤተ ክርስቲያን እየሄደችበት ያለውን ይህንን የቁልቁለት ጉዞ መግታት ካልቻልን በእግዚአብሔርም ዘንድ በትውልድም ተጠያቂ ከመሆን አናመልጥም።

ይህን በፊታችን የተጋረጠ አደጋ ለመቋቋምና ለማስወገድ ዛሬ ምን እናስብ? ምን እናድርግ? የአሁኑ ወቅት ይህ ብርቱ ጉዳይ የሚመለከተን ሁሉ በጥሞና ሆነን የምንጠያየቅበት፣ የሕያው አምላክን ፊት የምንሻበት የእድሳት ኀይልና ብርሃን የምንማጠንበት ወሳኝ ጊዜ ሊሆን ይገባል። ይህም ጉባኤ የተጠራው በዚህ አሳሳቢ ምክንያት ነው።

ይህ ጉባኤ ለመጠራቱ ምክንያት የሆኑ ወገኖች በጊዜው ስላለው የክርስቲያን ማኅበረ ሰብ ጠቅላላ ሁኔታ እየቃኙ፣ እያሰቡ እና እየጸለዩ ለሁለት ዓመታት ከቆዩ በኋላ ይህንን ሸክም ለብዙዎች የማካፈልን አስፈላጊነት በመገንዘባቸው ሐሳባቸውን ለሌሎች ሲያካፍሉ ቆይተዋል። አሁን ያለንበት መንፈሳዊ ውድቀቶች በሦስት ዋና አቅጣጫዎች ተገናዝበዋል፤ እነዚህም፡-

1. የሕይወት ጥራት፣
2. የአስተምህሮ ጥራት እና
3. የአመራር ጥራት ናቸው።

ይህንን ሸክም ሸክማቸው አድርገው የሚያገለግሉ ስድስት የአገልገሎት ድርጅቶች ዓላማ በመቅረጽ፣ ስልት በመንደፍና ግብ በማስቀመጥ ችግሩ የጋራ ችግር ሆኖ በጋራ መፍትሔ ለመፈለግ በግንባር ቀደምትነት የማነሣሣትና የማትጋት ሚና ለመወጣት ተሰልፈዋል፤ እነርሱም፡-

1. ቢብሊካ ኢትዮጵያ
2. የኢትዮጵያ ወንጌላውያን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና ምሩቃን ማኅበር (EvaSUE)
3. ደወል የወንጌል አገልግሎት
4. ቃለ እግዚአብሔር አንባብያን ማኅበር
5. ጎልደን አይል አገልግሎት
6. ኢቫንጀሊካል ቲዮሎጂካል ኮሌጅ (ETC) ናቸው።

ይህ ጊዜ ከወደቅንበት የመነሣት፣ ከኮበለልንበት የመመለስ፣ የንስሓና የተሐድሶ፣ የለውጥ ወቅት ሊሆን እንደሚገባ በጽኑ እናምናለን፤ ይህም እምነትና ሸክም የጥቂቶች ብቻ ሳይሆን የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሆነ እና የተግባሩም ሂደት እየጨመረ በሁሉ ዘንድ ሊሰርጽ የሚገባ መሆኑም እሙን ነው፡፡

ሁላችንም ልብ ልንለው የሚገባው ነገር የዚህ መሰባሰብ ትኩረቱ መልካም መልካም የሆኑ ገጽታዎቻችንን ነቅሰን እያወጣን ለመጽናናትና ራሳችንንም ለማሞካሸት ሳይሆን ራስን ለመፈተሽ፣ ለመመለስና ለመታደስ መሆኑን ነው። ስለሆነም ሆን ተብሎ አሳሳቢ በሆኑ ገጽታዎቻችን ላይ የምናተኩርበትና የሚለወጡበትን ሁኔታዎች በመቃኘት አዎንታዊ ለውጥን ለማግኘት የምንሻበት ነው። ድክመቶችም ሲነሡ ሁሉም ድክመቶች ሁላችንንም በእኩል ደረጃ ይመለከታሉ ማለት ላይሆን ይችላል። አንዳንድ ድክመቶች ከእኛ የተወሰነ ክፍልን ብቻ የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁንና ድክመቶቹ የሁላችንም እንደሆነ የሚያመለክት ቋንቋ መጠቀም ተመርጧል፤ ምነው ቢባል አንዱ ፈራጅ ሌላው ተፈራጅ የሚሆንበት ጉባኤ ስላልሆነ ነው። 'ሁላችንም ተጠያቂዎች ነን' የሚል ዕሳቤን የተመረኮዘ አቀራረብ ነው፤ የሚቀርቡትም ጽሑፎች በዚህ መልክ የተቀረጹት ናቸው (የዕዝራን፣ የነህምያንና የዳንኤልን ጸሎቶች ያስታውሷል)።

ይህ ጉባዔ ከአንድ ወገን የችግሮች መፍትሔ የሚቀርብበት ገበታ ሳይሆን ሁላችንም በጋራ ምክክርና ጸሎት፣ በንስሓም በመመለስ ለርምጃችን የሚበጀንን ፈለግ የምንቀይስበት፣ መንገድም የምንጠርግበት ነው፡፡ ከምክክር መድረኩ የሚጠበቁ ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

- በብሔራዊ ደረጃ ቤተ ክርስቲያን ስለምትገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ ጥርት ባለ መንገድ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር፤
- የእግዚአብሔር መንፈስ እንደሚረዳን መጠን ካለንበት ዐዘቅት ለመውጣት (ለመመለስ) ቁርጥ እርምጃ ለመውሰድ መነሣት፤
- የማያቋርጥና ብርቱ ራስን የመመርመርና የተሐድሶ ንቅናቄ መጀመር፤
- ራስን መመርመር መመለስና መታደስ በግልም በቤተ ክርስቲያንም ደረጃ ሕያው የቤተ ክርስቲያን ባሕል እንዲሆን ማድረግ የሚሉት ናቸው።

እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልን፣ ይመልስልን፤ በመመለስ የሚገኘውን የሕይወት ሙላት ይላክልን፤ ተልእኳችንንም የመወጣት ልብና ዐቅም ይለግሰን። አሜን።

# የተሐድሶ ጥሪ

መመርመር - መመለስ - መታደስ
በግልም በቤተ ክርስቲያንም ደረጃ

*"እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን፤*

*ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ" ሰቆ. 5÷21*

# የሕይወት ጥሪት

# I. መግቢያ

የክርስቶስ ተከታይ መሆን የሰውን መላ ሕይወት የሚዳስስ ታላቅ ጥሪ ነው። የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር መተዋወቅ ሕይወትን መቀበል ነው፤ "ልጁ ያለው ሕይወት አለው"። ክርስቲያንነት በቀዳሚ ደረጃ የእምነት አንቀጽ መቀበል ወይም የአምልኮ ሥርዐት መውረስ ወይም በቤተ ክርስቲያን ማኅበር ውስጥ መመዝገብ ሳይሆን አምላክም ሰውም ከሆነው ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር የሚደረግ ሕያው ግንኙነት ነው። ከዚህ ግንኙነት አዲስ ሕይወት ይፈልቃል፤ ይህ ሕይወት የሚያድግ፣ የሚጎለብት፣ እየበሰለ የሚሄድ ንቁ ሕይወት ነው። ሊያሳ ድገው የሚችለውን ንጹሕ ምግብ ሲያጣ፣ ከሕይወት መሥመሩ ከግንዱ ጋር ያለው መያያዝ ሲላላ፣ መርዛማ ነገር ሲጠናወተው ግን በማደግ ፈንታ ይደገድጋል፣ እየከሣ፣ እየሚሸሸ ይሄዳል።

ወንጌላዊ የሆነው ይህ ማኅበረ ሰብ ዛሬ የግልም ሆነ የማኅበር ሕይወቱ በጣም አጠያያቂ ደረጃ ላይ ደርሷል። እውነተኛው ክርስቲያናዊ ሕይወት በቅዱስ አኗኗር፣ በመልካም ሥነ ምግባር፣ በደማቅ ምስክርነትና በፍቅር ሊገለጥ ሲገባው በአስደንጋጭ የሞራል ውድቀት፣ በተፈረካከሰ አንድነት፣ በተዛባ የኑሮ ዘዬ ከዚህም የተነሣ በተከሰተ ተጽእኖ አልባነት የታወቀ ሆኗል።

የሕይወት ጥራት ችግሮቻችን ምንድን ናቸው? እንዴት ልንኖር ይገባናል? ምን ዐይነት የእድሳት ርምጃዎች ያስፈልጉናል? የሚሉትን ብርቱ ጥያቄዎች ይዘን ልንነጋገር፣ ያለንበትን ሁኔታ ልንቃኝና ወደ ጠራው ሕይወት አኗኗር ልንመለስ ይገባል።

# II. እየተደመጡና እየታዩ ያሉ ወቅታዊ የሕይወት ጥራት ችግሮች

### 1. የሞራል ዝቅጠት ወይም የምግባር ብልሹነት

ምግባረ ብልሹነት ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ ተግዳሮት ሆኗል፤ ይህም የአደባባይ ምስጢር ነው። ዛሬ ያለነው ወንጌላውያን ቤተ እምነቶች "... የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ ..." (1ጴጥ. 1፥14-15) የሚለውን አምላካዊ ጥሪ/ግብዣ የዘነጋንበት በትኩረትም የማናስተምርበት ወቅት ላይ ነን። ቅዱሱ ወንጌል በቅድስና መያዝ ያለበት መሆኑን ማስተጋባት ቸል የተባለበት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የቅድስናን ኑሮ ወደ ጎን የተተወበት ጊዜ ላይ ነን። "እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ሁሉ እነሱም ከዓለም አይደሉም። ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው" (ዮሐ. 17፥16-17) በማለት ጌታ ኢየሱስ የጸለየውን ጸሎት ዘንግተነዋል። ለቅድስና ባይተዋር የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ ኢየሱስም ባይተዋር መሆኗ አይቀርም።

የዘመኑ ወንጌላዊ ክርስትና አቅፎ ለያዛቸው ምእመናን ብቻ ሳይሆን ከውጭ ላሉትም ጆሮ የሚቀፍ፣ ለማሰብ የሚዘገንን የሞራል ውድቀትና የኑሮ ሰንካላነት እያስተናገደበት ነው። ይህ ውድቀት የእግዚአብሔርን መንፈስ የሚያሳዝን፣ ጽድቅን የሚያፈቅሩትን አንገት የሚያስደፋ፣ ላልዳኑትም የወንጌሉን ብርሃን እንዳያበራ የሚጋርድ የጨለማ ሥራ ነው። ለዘብተኛ ከሆነ አመለካከትና አስተምህሮ የተነሣ አማኞች በዕለታዊ አኗኗራችን ክርስቶስን በማሳየት ብርሃንና ጨው ከመሆን ይልቅ በምግባረ ብልሹነትና በልዩ ልዩ የሕይወት ጉድለት የምንከሰስ ሆነናል። ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በኅብረተ ሰቡ ላይ የጽድቅ ጫና ማሳደር አልቻለችም።

በዚህ ዘመን ከቅድስና መጉደል አኳያ ቤተ ክርስቲያንን እየናጡዋት ያሉትን ጉዳዮች ሁሉ መዳሰስ የሚያዳግት ቢሆንም እጅጉን የከፉት፣ ጎልተውም የሚታዩትን መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል።

- ሳያገቡ በፊት የሚፈጸም ወሲብ (ሴሰኝነት):- በርካታ ወጣቶች፣ ጎልማሶችና፣ ምእመናንና አገልጋዮች የዚህ ወጥመድ ሰለባ ሆነዋል። በ2005 ዓ.ም. በተመረጡ 12 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ በተደረገ ጥናት መጠይቅ ከቀረበላቸው 150 ወጣቶች መካከል 46ቱ ማለትም 30.7 በመቶው ቅድመ ጋብቻ ወሲብ በተለያዩ ጊዜያት መፈጸማቸውን ገልጠ ዋል። ይህ የሚያመለክተው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአማካይ ከሦስት ወጣቶች መካከል አንዱ በዚህ ልምምድ ውስጥ እንደሚያልፍ ነው።
- ምንዝርና:- ከጋብቻ ኪዳን ውጪ የሚፈጸሙ ወሲባዊ ግንኙነቶች እየተበራከቱ ናቸው። በሐሳብም በተግባርም ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ታማኝነት ሊያሳዩ ሲገባ አሁን ግን ከዚህ ኪዳን ውጭ ብዙ የአውስቦን አጋሮች ማበጀት መለመዱ አስደንጋጭ ሆኗል፤ ይህ ዐይነቱ አካሄድ በቸልታ እየታለፈ መሆኑም ይልቁን ያስደነግጣል።
- ፍቺና ድኅረ ፍቺ ጋብቻ:- የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ መፋታትን የሚቃወም መሆኑ እየታወቀ ዛሬ አስደንጋጭ በሆነ መጠን ፍቺ የቤተ ክርስቲያን ዋነኛ ተግዳሮት ሆኖ ተገኝቷል። ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ ለፍቺ እየቀረቡ ያሉ ምክንያቶች አጥጋቢ ያለመሆናቸው ሲሆን ሰዎች በትንቢት ተጋብተው፣ በትንቢት የሚፋቱበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም።
- ግብረ ሰዶማዊነት:- "... በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንዲቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን ... የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ጸድቃችኋል።" (1ቆሮ. 6፥9-1)። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ እያለ ሳለ ሰዶማዊነት ውስጥ በሐሳብም ሆነ በተግባር መጠመድ፣ ይህንኑ አደጋ በቸልታ ማየት እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ይህ ሁኔታ ተፈጥሯዊ ግዴታ እንደ ሆነ የሚያቀነቅነው አስተሳሰብ መሠረት የሌለው መሆኑና ቃሉ እንዳስረገጠልን ትድግናና ለውጥ ሊኖረው እንደሚችል ያለመገንዘብ ይስተዋላል። እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይቀር የዚህ አጸያፊ የኑሮ ዘይቤ ሰለባ የሆኑበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ይሁንና ቤተ ክርስቲያን አሁንም ድረስ ይህንን ጉዳይ ተገቢ ትኩረት አልሰጠችውም።
- ሳይጋቡ አብሮ መኖር:- በርካቶች ያለ ኪዳንና ሕጋዊ ጋብቻ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚመላለሱበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ይህ ዐይነቱ ግንኙነት ምንዝርና መሆኑ በግልጽ እየታወቀ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተገቢውን የማስተካከያ ርምጃ ሲወስዱ አለመታየታቸው ችግሩን የከፋ አድርጎታል።

- ወሲባዊ ርቃን (ፖርኖግራፊ):- የርኩሰት ትዕይንት የተሞሉ ፊልሞችን፣ መጽሔቶችን፣ ድረ ገጾችን ወዘተ. በመመልከት ራስን የማርከስ ልምምድ እንደ ሰደድ እሳት ትውልዱን እያጠፋ ያለ ተግዳሮት ሲሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በርካታ አዳጊዎች፣ ወጣቶችና ጎልማሶች የዚህ ወሲባዊ ርኩሰት ሰለባ ሆነዋል። ይህ ዐይነቱ ልምምድ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ላለው ወሲባዊ ርኩሰትና ፍቺ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።
- ውርጃ:- ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ለጋ ሕፃናትን በማሕፀን ውስጥ ሳሉ መግደል በአማኞችም ዘንድ እየታየ ነው። ከዚህ የተነሣ ብዙዎች የሥነ ልቡና ችግር ተጠቂዎች ሆነዋል።
- ሌሎች ሕፀፆች ሱሰኝነት፣ ዘፋኝነት፣ ጉቦ፣ ፍትሕን ማዛባት፣ የቅጂ መብት አለመጠበቅና የመሳሰሉት የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት ያጎደፉ ክስተቶች ሆነዋል።

በደፈናው ባላመኑትና በእኛ መካከል ደምቆ ይታይ የነበረው የልዩነት መሥመር ዛሬ ደብዝዞ ልዩነታችንን የሚገልጥ ነገር በመጥፋቱ ለነፍሳት ወደ ጌታ መምጣት ትልቅ እንቅፋት ሆኗል።

2. ዓለማዊነትን የሚያስተናግድ የአስተሳሰብ አዝማሚያ

ድኅረ ዘመናዊነት (Postmodernism) በቤተ ክርስቲያን ላይ እያሳረፈ ካለው አሉታዊ ተጽእኖ የተነሣ የሞራል ድንበሩ ጠፍቶ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሐሳብም ሆነ በተግባር ከዓለም ጋር የመቀላቀሉ ሂደት ፈጣንነት እጅግ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። 'የምንአለበት' ሕይወትና አገልግሎት እንደ ወረርሽኝ ከወረረን ዋል አደር ብሏል። እንዲያውም ዕሴቶቻችንን ማጣታችንና ለቃሉ ሥልጣን አለመገዛታችን ከማሳፈር ይልቅስ እንደ ዐዋቂነት እየተቈጠረ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ድኅረ ዘመናዊነት ነባራዊ እውነታን የሚክድ፣ ሞራላዊ መለኪያን የሚሰብር፣ ሁሉን አንጻራዊ የሚያደርግ፣ የእውነትን ካስማ የሚነቅል ፍልስፍና ነው። ይህ ፍልስፍና በቤተ ክርስቲያን ላይ እያሳደረ ያለው ክፉ ጫና በቅዱስ ኑሮ እና በቅድስና ዐልባ አኗኗር መካከል ያለውን ድንበር ደብዛ ማሳጣት ነው። 'ምን አለበት?'፣ "በእኔ አመለካከት/አስተያየት'፣ 'እግዚአብሔር እኮ ፍቅር ነው'፣ ወዘተ. በሚል አጉል ፈሊጥ ክርስቲያኖች መስፈርት ዐልባ እንድንሆን እያደረገን ነው። ከዚህም የተነሣ አማኞች/አገልጋዮች/መሪዎች በዐይናችን መልካም መስሎ የሚታየንን ያለ ምንም ገደብ ከማድረግ የማንመለስበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል። ስለዚህ ቍጥሩ ጥቂት የማይባል ሕዝበ ክርስቲያን በቃልም ሆነ በተግባር ልቅ የሆነበት ዘመን ነው።

3. ለግለ ሰብ ማጠን (ግለ ሰብ እንደ ጣዖት/**Celebrity mindset**)

ዝነኝነትን የመሻት ልብ የተጠናወተን አገልጋዮችና መሪዎች እንደ ሆሊዉድ እና ቦሊዉድ ተዋንያን፣ የቤተ ክርስቲያንን መድረክ ራሳችንን የምንሸጥበት፣ አማኞችን በሕልም ዓለም የምናስዋኝበት መድረክ አድርገነዋል። ይህ ክስተት በምድራችን በቤተ ክርስቲያን ቅዱስ መድረክ ላይ ሲፋንን መስተዋል ከጀመረ ቆይቷል።

በዚህ ውስጥ ያለነው ለምንናገረው ነገር ተጠያቂነት አይሰማንም። አንዳንዶቻችን መድረኩ የእግዚአብሔር መገኛ ስፍራ መሆኑን ዘንግተን የምንገበዝ፣ ተሰብሳቢውን በስሜት እያጦዝን ከግራ ቀኝ እያልን፣ እላይ ታች እየዘለልን የምናደርገውን የማንገነዘብ በመሆናችን፣ የሆነው ከሆነ በኋላ ላደረግነው ድርጊትና ለሚያስከትለው መዘዝ ኀላፊነት አንወስድም።

4. ምድራዊነትን የሚያራግብ "የብልጽግና ወንጌል" መበራከቱ

ከስግብግብነት የተነሣ ሀብትና ንብረት አምላክ የሆነበት ዘመን ነው። በመሆኑም ብዙ ሰዎች "ብልጽግናን" ሲያሳድዱ ሕይወታቸውን በመራራ ጦር እየወጉና እያጠፉ ይገኛሉ። ጥቅም ከመፈለጋችን የተነሣ ከእውነት ጋር መወገን ተራራ ሆኖብናል። የክርስቶስ ተከታይ እየተባልን ጽድቅንና ዐመፅን ለመለየት በተሰየመ የፍርድ ቦታ ላይ ወይም ሕዝብ ፍትሐዊ አገልግሎት ማግኘት የሚገባው ወንበር ላይ ተቀምጠን የሕዝብ ሀብት መዝረፍ፣ በነዋይ ፍቅር የተነደፈ፣ ማንነታችንን የዘነጋን፣ በዓለማዊነት ጭቃ የተከበብን መሆናችን እጅግ አሳፋሪ ነው።

እግዚአብሔር በምድራዊ ሀብት ያበለጸገን ጥቂት ወገኖች የብልጽግናን ወንጌል በሚያራምዱ አገልጋዮች ሐሳብ መማረካቸው አማኞች እውነተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን በረከት እንዳይለማመዱ አድርጓል። ከዚህ በከፋ መልኩ ግን የብልጽግናን ወንጌል እየሰበክን ድኻውን የምንበዘብዝ፣ መበለቲቷ ጥራ ግራ ያገኘችውን ሳንቲም ለመልቀም በ'ትባረኪያለሽ ያለሽን አምጪ' አባዜ፣ ያላቸውን ደግሞ በማስፈራራትም ሆነ በሽንገላ ቃላችን የምንዘርፍ "ሰባኪያነ ወንጌል" የተበራከተበት ዘመን ላይ እንገኛለን።

5. በጸጋ ስጦታዎች ስም ሽፋን የሚከሰቱ አደጋዎች

እግዚአብሔር በሰፊ ቸርነቱና በጥልቅ ፍቅሩ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲሠሩ ሰጥቷል፤ ዛሬም ይሠራል። እግዚአብሔር ስጦታዎቹን የሰጠበትን ምክንያት ስንመለከት ከመንግሥቱ ርቀው የሚገኙትን ወደ መንግሥቱ ለመመለስ፣ ሕዝቡን በፈቃዱ መንገድ ለማምራትና ለማነጽ፣ ንጽሕትና ክብርት ቤተ ክርስቲያንን በፊቱ ለማቅረብና ታላቅነቱንና ክብሩንም ለመግለጽ ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን የጸጋ ስጦታዎች የተሰጡበት ዐላማ ተዘንግቶ ወይም ሆን ተብሎ ተለውጦ፣ አሠራራችን መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝን፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍል ክስተት እየሆነ ለመምጣቱ ጠቋሚዎች አሉ። ጥቂቶቹን እናንሣ:-

- ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች ጥቂቶቻችን ለክብር፣ ለዝናና እንደ ሸቀጥ በገቢ ምንጭነት ስንጠቀምባቸው፣ ብዙኀኑ ደግሞ ሲበዘበዙባቸው ይታያሉ፤

- ምእመናን በግል ጌታን በማወቅ እንዲታመኑበት ከማድረግ ይልቅ አገልጋዮች በተባልነው ላይ ተደጋፊ እንዲሆኑና ሃይ ባይና ከልካይ ሳይኖር

‘አድርግ፣ በል’ በሚሉ ከንቱ መመሪያዎችና ትእዛዞች ጊዜያቸውን እንዲፈጁ ስናደርግ እንታያለን፤

- መሠረት የሌላቸው ትዳሮች እንዲወጠኑና ነባር ትዳሮችም እንዲናጉ ምክንያት እየሆንን እንገኛለን፤
- በምንሰጣቸው እውነትነት የሌላቸው ተስፋዎች ምክንያት መልእክተኛውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ዋሾ አድርጐ በመቍጠር የብዙዎች ሕይወት እንዲፈርስና ከጌታ ቤትም እንዲለዩ ሆነዋል፤ እየሆኑም ናቸው፤
- ‘ባርኮቱ ወደ እናንተ እንዲመጣ የበረከት ዘር በእኔ ላይ ዝሩ’ ለምንል “ቅቡኣን” ንብረታቸውን አስረክበው ባዶ እጃቸውን የቀሩ፣ ኑሯቸው የተናጋና እውነትነት በሌላቸው ባዶ ተስፋዎች ምክንያት ከጌታ ቤት የተለዩትና የንግድ ተቋማቸው የፈረሱባቸው ጥቂት አይደሉም፤
- ድርጊቶቹ ቅን አማኞችን አንገት ሲያስደፉ ለእግዚአብሔር ስም መሰደብ፣ ለታማኝ አገልጋዮችና በጽድቅ ለሚገለጥ የእግዚአሔር ጸጋ ስጦታ አገልግሎት ደግሞ መቅለልና መናቅ ምክንያት እየሆኑ ይገኛሉ፤
- የጸጋ ስጦታዎች የተሳሳተ አጠቃቀማችን፤ እንደ ቃሉ ያልሆነውን ልምምድንና ትምህርታቸውን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እንዲዘሩ ለሐሰት መምህራን ዕድሉን አስፍቷል። ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሐሰት ትምህርቶች እዲበከል ምክንያት እየሆነ መጥቷል።

> በእግዚአብሔር ቅናት እቀናላችኋለሁ፤ እናንተን እንደ ንጽሕት ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ባል አጭቻችኋሁና። ነገር ግን እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋሉ። ምክንያቱም አንድ ሰው ወደ እናንተ መጥቶ እኛ ከሰበክንላችሁ ኢየሱስ ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክላችሁ፣ ወይም ከተቀበላችሁት መንፈስ የተለየ መንፈስ ብትቀበሉ ወይም ከተቀበላችሁት ወንጌል የተለየ ወንጌል ብትቀበሉ፣ ነገሩን በዝምታ ታልፉታላችሁ ማለት ነው። 2ቆሮ. 11፥2-4

በአጠቃላይ ከዚህ ሥነ ምግባር ከጎደለው የተሳሳተና እንደ ቃሉ ያልሆነ የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም የእግዚአብሔር ሕዝብ በሩ ተከፍቶ በተተወ ጋጥ ውስጥ የሚያድር፣ ከንጥቂያ የሚታደገው እረኛ የሌለው መንጋ ሆኖ ተገኝቷል።

ችግሮቹን መዘርዘራችንን ገታ አድርገን፣ በቅዱስ ቃሉ ውስጥ በሰፈረው መለኪያ አንጻር የክርስቲያን ሕይወት ጥራትን መሠረታዊ በሆኑ ክፍሎች አንጻር ለመመልከት እንሞክር።

## III. የክርስትና ሕይወት ጥራት በግለ ሰብ

የክርስትና ሕይወት የግለ ሰብ ጥሪ፣ የግለ ሰብ ኑሮና ዐላማ ያለበት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከጨለማ አገዛዝ ወደ ልጁ መንግሥት ቢያፈልስም እያንዳንዱ የራሱን ጥሪ ተከትሎ፣ ምላሽ ሰጥቶና ወስኖ የሚጀምረው የኅብረት ጉዞ ነው። ሰው በግሉ የሚመራው ሕይወት በማኅበር ተጽእኖ ውስጥ የሚያልፍ ቢሆንም ወሳኙና አራማጁ ግን ግለ ሰቡ ራሱ ነው። የአዲስ ኪዳኑ ኑሮ እስራኤል ከግብፅ ሲወጣ በኅብረት እንደተመመ፣ ሕግ እንደ ተቀበለና በማኅበር እንደ ተመራ አይደለም። ሕገ እግዚአብሔር በልቦና በሚጻፍበትና መንፈስ ቅዱስ አማኙን በተናጠል ማደሪያ በሚያደርግበት የአዲሱ ኪዳን ሥርዐት የክርስትና ሕይወት በተናጠል የሚኖር በኅብረት ደግሞ የሚጸና ነው።

“እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን” (1ቆሮ. 6፥19) ተብሎ እንደ ተጻፈ እያንዳንዱ አማኝ የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው። እምነትና ንጽሕና በሚጠየቅበት በዚህ ሕይወት ግን ካለማነው ያጠፋነው፣ ካነጽነው ያፈረስነው እየበዛ ነው። አማኝ ከጌታ በአደራ ብቻ ሳይሆን ከጸጋ ጋር የተቀበለውን ሕይወት እንደ አልባሌ ነገር በመቍጠር ከጽድቁ መለኪያ በወረደ ደረጃ ይመራዋል። አሁን የሚታየው ሁኔታ የአንድ ጊዜ ጥፋት ወይም ድንገተኛ መሳሳት ሳይሆን አዳጉል የኑሮ ዘይቤ ሆኗል።

እንደ ብርሃንና ጨው ልዩነት መፍጠር ሲገባን ልናሰማው የሚገባንን ዓለም እንዲሁ በመቀላቀል የመለኮታዊው መፍትሔ አካል በመሆን ፈንታ የችግሩ ክፍል እየሆንን ነው። ዛሬ ዛሬ በአማኝና በሌላው መካከል ያለው መሥመር እየጠፋ ነው የመጣው። ትትነው የተሻገርነውን ሕይወት መንፈሳዊ መልክና ይዘት ይዘን እየተመለስንበት ነው። ወጥተንበት እንደ ናፋቂ ንብኚ ተመልሰንበታል፤ የስም ለውጥ ሆኗል እንጂ የምግባር፣ የአመለካከትና የሕይወት ዘይቤ ባለበት ቀጥሏል።

የአገልጋዩ ሕይወት ከአማኙ፣ አማኙም በጌታ ካላመነው ጋር እየተዋሐደ ድብልቅ ሕዝብ እየተገነባ ይገኛል። የእግዚአብሔር ስም በብዙዎች ይነቀፋል፤ ቀድሰን ከፍ ልናደርገው ሲገባ በአልባሌና አሳፋሪ ነገር እንዲነሣ እያደረግነው ነው። ክርስቶስ ያልቀደመበት፣ ራስ ግን የገነነበት ሕይወት እዚህም እዚያም እየተኖረና እንደ ምሳሌም ቀዳሚ ሆኖ እየታየ ነው።

## IV. ክርስቲያናዊ ትዳር

ጋብቻ (ትዳር) በእግዚአብሔር የተመሠረተ፣ በክርስቶስም የተቀደሰ ኪዳናዊ ተቋም ነው። በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት በፈቃደኝነታቸው ላይ የሚመሠረት አንዳቸው ለአንዳቸው ተቀድሰው፣ ታማኝ ሆነው የሚኖሩበት የፍቅር ውል ወይም ስምምነት ነው። ባል ሚስቱን እንደገዛ ሥጋው ሊወድ ሚስትም በሷን ልትታዘዝ እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል። ልጆቻቸውን በጋራ በፈሪሃ እግዚአብሔር በክርስትና መርሕ፣ በመንፈስ፣ በአእምሮ፣ በአካል እንዲያድጉ፣ በተግሳጽና በምክር እንዲቀኑ የጋራ ኀላፊነት ያለባቸው ናቸው። ልጆችም እግዚአብሔርን፣ ወላጆቻቸውንም በማክበር አምላካዊ ትእዛዝ መፈጸም አለባቸው፤ ይህንንም የማስገንዘብ፣ የመገንዘብም ኀላፊነት የወላጆችም የልጆችም ነው። ይህ ሲሆን የክርስቲያን ትዳር ሕይወት ለጐረቤት፣ ለማኅበረ ሰቡም ብርሃንና ምሳሌ ይሆናል፤ እግዚአብሔርም ይከብርበታል።

የትዳር ሕይወት በአሁኑ ዘመን ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞታል። ብዙ የክርስቲያን ትዳሮች እየፈረሱና ለመውደቅ እየተንገዳገዱ ነው። በተለይም የብዙ አገልጋዮች ጋብቻ ቀውስ ውስጥ እየገባ ነው፤ ልጆች ከቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ሕይወት እያፈነገጡ ለአደጋም እየተዳረጉ ነው።

ግብረ ሰዶማዊው ነፋስ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የትዳር መሠረት ሊያናውጠው እንደሚችል የታወቀ ነው፤ በምዕራቡ ዓለም የወሲብ አብዮት በመባል የሚታወቀው ክስተት አሁን በእኛ አገር ላይ እየገነነ ያለበት ጊዜ ነው። በባልና ሚስት መካከል ያሉ በትዕግሥትና በፈሪሃ እግዚአብሔር፣ በቅዱሳንም ምክር ሊፈቱ የሚገባቸው ችግሮች ወደ ፍርድ ቤቶች እየተጐተቱ ነው፤ ያለንበት ሁኔታ አሳሳቢ ነው፤ ጸሎት፣ ምክርና ምክክር የተጠናከረ ትምህርትም ያሻል።

## V. ተዝናኖት

ሰው አካላዊ ማንነት ስላለው ዕረፍት፣ ዘና ማለትና መጫወትን ይሻል። እነዚህ ሁሉ ጠቃሚና ለተጨማሪ ሥራና ውጤታማነት የሚያድሱ ነገሮች ናቸው። ሰው ማኅበራዊ ስለ ሆነም ፈታ ማለትንና መዝናናትን ከሌሎች መሰሎቹ ጋር በመሆን እውን ያደርጋል። በጋራ ደስ የሚያሰኙ ነገሮችንም ማድረግ ለሰውነት ፈውስ ለኅብረትም ጥሩ ማያያዢያ ነው። ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን በጊዜው፣ በአግባቡና ከመለኪያው ሳይወርዱ መሆን ይኖርበታል።

በዘመነ ቴክኖሎጂ የተዝናኖት አድማስ ሰፍቷል። አንድ ሰው ከሌላው ጋር መቀመጥ ወይም አብሮ መሆን ሳያስፈልገው ራሱን ዘና ሊያደርግ ይችላል። ቴሌቪዥን አንዱ ሲሆን ኮምፒውተርና ስማርት ስልኮች ሌሎቹ መንገዶች ናቸው። እነዚህ የሰው ረቂቅ ሥራዎች ሌላውን ዓለም ወደ ጉያችን ወይም ጓዳችን በማቅረብ ትውውቅ ሳያስፈልግና ሩቅ ሳንሄድ ዘና እንድንል ሊያደርጉን ይችላሉ። ችግሩ ሁሉን፣ ድብልቅልቅ ያለውን ማቅረባቸው ነው።

በምስሉ ላይ ጥሩ መዝሙር የሚመጣውን ያህል በዚያው ምስል ላይ ዋልጌ የሆነ ሙዚቃ ይናኛል። የሚያንጽ መልእክት በቀረበበት በዚያው ገጽ ላይ ተጻራሪና አፍራሽ ሐሳብ ይንጸባረቃል። ሌላም ሌላም። ተደራሲው ለይቶ ለመምረጥ ዝግጁ ካልሆነ በተዝናኖት ሰበብ የክፉ ሐሳብና ምኞት መራገፊያ ይሆናል። ዘና እንዲል የተፈለገውም ሰውነት ይቆሽሻል።

ክርስቲያን በፍጥረታዊ ማንነቱ እንደ ሌሎች ሁሉ ዘና ማለት ቢገባውም ቅደም ተከተሉን ግን ሁሉጊዜ ሳያዛባ መሆን አለበት። መንፈሳዊው ማንነት ላይ ጥላ የሚያጠላ ብሎም ተጽእኖ የሚያሳድር ተዝናኖት ጠቃሚ ሳይሆን ጎጂ ነው። እውነት ነው "ሁሉ ተፈቅዷል"፣ ሁሉ ሲል ግን ጥሩ ወይም ጽድቅ ያልሆነውን እንደማይጨምር እሙን ነው። የተፈቀደው ሁሉ ደግሞ አይጠቅምም። የሚደረገውም ጊዜውን ሲጠብቅ ውብ ይሆናል። "አንተ ጐበዝ፣ በጕብዝናህ ደስ ይበልህ፥ በጕብዝናህም ወራት ልብህን ደስ ይበለው፥ በልብህም መንገድ ዐይኖችህም በሚያዩት ሂድ ዳሩ ግን ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንዲያመጣህ ዕወቅ።" (መክ. 11፥9)።

## VI. የሕይወት ጥራት - በቤተ ክርስቲያን ሕይወት

የክርስትና ሕይወት የግል ብቻ ሳይሆን የጋራ ሕይወትም ነው፤ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በዚህም እምነት መሠረትነት ላይ የቆመው ይህ የወል ሕይወት መውደቁም መነሣቱም የሚታየው ቤተ ክርስቲያን በተባለችው የክርስቶስ አካል ውስጥ ነው። ይህም ማኅበር ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን መንግሥት አኗኗር የሚገልጥባት ሠርቶ ማሳያ ቤት ናት። የሰላምና የፍቅር፣ የጽድቅና የፍትሕ፣ የምሕረትና የሐሴት፣ የኅብረትና የአንድነት፣ የርኅራኄና የቸርነት መከሰቻ መደብ ናት።

የሐዋርያት ሥራ እና ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉት የአዲስ ኪዳን መልእክቶች በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት የክርስትና ሕይወት ምን እንደሚመስል ያሳያሉ። አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበራቸውን ሕይወት ሲናገሩ ትኩረት የሚያደርጉት በአካል በተመሰለችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እርስ በርስ በነበራቸው ግንኙነት ላይ ነው። በኢየሩሳሌም የነበሩት የመጀመሪያዎቹ አማኞች ለእርስ በርስ ኅብረት ራሳቸውን የሰጡ ነበሩ (ሐዋ. 2፥4)። አብረው ቃሉን ሲማሩ፣ ሲጸልዩና በማዕድ ሲካፈሉ፣ እርስ በርሳቸውም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ትርጒም ያለው ኅብረት ሲያደርጉ ነበር። የተቆረሰውን የክርስቶስን ሥጋና የፈሰሰውን ደሙን ያስባሉ፤ አንዱ ለሌላው ይጸልያል፤ ለእግዚአብሔርም ምሥጋናና ውዳሴን በማቅረብ ያመልኩታል። በንጹሕ አኗኗር ሲኖሩ ይህ ኅብረት ይጠበቃል፣ ይለማል፣ የቆሸሸም ይጸዳል። "እርሱ በብርሃን እንዳለ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ በርሳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል።" (1ዮሐ. 1፥7)።

### 1. የክርስቶስን ሕይወት መካፈል

ኅብረት (Fellowship) በጋራ የመካፈል ሕይወት ነው። በክርስቶስ አንድ የሆኑት አማኞች የክርስቶስን ሕይወት በጋራ በመካፈል አብረው በአንድነት እየታነጹ ያድጋሉ።

ኅብረት በስብሰባ ከመገኘት የላቀ ነገር ነው። በዕብ. 10፥25 "በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደሆነው፣ መሰብሰባችንን አንተው ..." የሚለው ምንባብ በቤተ ክርስቲያን ስብሰባ ስለ መገኘት ብቻ የሚናገር አይደለም። የምንሰበሰበው ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ ነው በውስጣዊ ሕይወት እየታደስን፣ በሠናያት ባሕርያት እየተገነባን ወደ ክርስቶስ ለማደግ ነው።

#### 1.1 ተሳትፏዊ ሕይወት

በብልቶች መጠናቀር፣ መያያዝና በጤና መንቀሳቀስ በትጋት የሚሠራ አካል ምሳሌ ሆና የቀረበ ችው ቅድስት ማኅበር ቤተ ክርስቲያን ሁነኛ መለያዋ እያንዳንዱ አማኝ ከሌላው እየተቀበለ፣ ለሌላውም እየሰጠ የሚያድግባት ሕያውት ማኅበር መሆኗ ነው። ጥቂት ደማቅ ተዋንያንና እልፍ ትርኢት ተመልካቾች ያለበት የጨዋታ አደባባይ የቤተ ክርስቲያን ሞዴል አይደለም። "የተከፋፈሉ የእሳት ልሳኖች በእያንዳንዳቸው ላይ ተቀመጡባቸው" (ሐዋ. 2)፤ "ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል [ወይም ይሰጣል] (1ቆሮ. 12፥11)። "እርስ በርሳቸው በትክክል ይተሳሰቡ ዘንድ ... እግዚአብሔር አካልን አገጣጠመው" አንዱ ሲሠቃይ አብሮ መሠቃየት፣ አንዱ ሲከብር አብሮ መደሰት (1ቆሮ. 1፥26) የሚሉና ሌሎችም ጥቅሶች

እንደሚያስረዱን ጥልቅ ተሳትፎና ተደጋጋፊነት የአዲሱ ማኅበረ ሰብ የወትሮ መልክ ነው።

በጸጋ ስጦታና በአገልግሎት እንደተቆራኘን ሁሉ የየዕለት መሰጠታችን፣ ትጋታችን፣ ተጠያቂነታችንም ከሁሉ የሚጠበቅ ኀላፊነት ነው። እንግዲያው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመደብ ልዩነት፣ የተራና የክቡር ዜግነት ልዩነት ወይም የዝምድና ርቀት ቅርበት ከቶ የለም። ከፊሉ እጅግ ከፍ ያለ የሕይወት ጥራት የሚጠበቅበት የተቀረው በአልባሌ ሕይወት ቢኖርም የሚፈቀድለት ቅይጥ ሚዛን ያለበት ቤት የለም። አንድ ሠራዊት ሆኖ ዘምቷልና ትጥቁም ትጋቱም የሁሉ ነው። የቤተ ክርስቲያን የሕይወት ጥራት አንዱ ማሳያ እንግዲያው እያንዳንዱ ምእመን አስፈላጊነቱ ግልጽ የሆነበት፣ ፈላጊነቱም ተደጋፊነቱም የተረጋገጠበት ምሉእ ሱታፌ ነው።

1.2 የእርስ በርስ የኑሮ ዘዬ

ቤተ ሰብ፣ ቤተ መቅደስና ቤተ ብልት (አካል) ሆና የተሠራችው የአማኞች ማኅበር የአባሎቿ ጤናና ዕድገት ማረጋገጫ የኑሮ ስልቷ "እርስ በርስ" የሚል ዘይቤ ነው። በአዲስ ኪዳን ገጾች በሰፊው የተሠራጨው ይህ ቃል በአዎንታዊም በአሉታዊም አካሄድ ቀርቦልናል።

1.3 እርስ በርስ - አዎንታዊ

እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፣ እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፣ እርስ በርሳችሁ አስተምሩ፣ እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፣ እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ፣ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ፣ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፣ እርስ በርሳችሁ እንደ ባርያዎች አገልግሉ፣ ወዘተ.።

1.4 እርስ በርስ - አሉታዊ

እርስ በርሳችሁ አትወነጃጀሉ/አትፈራረዱ፣ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፣ እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ፣ እርስ በርሳቸሁ አትበላሉ/አትነካከሱ፣ እርስ በርሳችሁ አትጐነታተሉ/አትቀናኑ ወዘተ.።

እዚህ ላይ ሁለት ነጥቦች ብቻ እናንሣ፦- የሕይወት ጥራታችን አንድ መለኪያ እርስ በርስ ለመናዘዝ ያለን ዝግጁነት ነው። ይህ ታላቅ ፍቅርና መተማመን ጥልቅ ትሕትናና ወንድማዊ መተሳሰብን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደዚህ ልቀት ገና እንዳልደረሰች ይታወቃል። የወልድ የጋራ ኑዛዜ የእርስ በርስ ንስሓ የልማት ጐዳና ነው። "ትፈወሱም ዘንድ አንዱ ስለሌላው ይጸልይ" ተብሏልና የፈውስ ኀይል በጋራ ጸሎትና ፍቅር ጌታ ብቻ በሚደምቅበት የኅብረት አምልኮ ውስጥ ሊካሄድ መቻሉ ታላቅ ተስፋ ነው። ይህ ልምምድ የሥርክ ተግባር እንዲሆን የልብ መሰናዶ ይጠይቃል።

1.5 አንድነትን መጠበቅና የተበላሸ ግንኙነትን ማስተካከል

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎት (ዮሐ. 17) ዋና ትኵረት የሆነው የእኛ አንድነት ጒዳይ የሕይወት ጥራታችንን መለኪያ አንዱ ጉልሕ ምስክር ነው። እኛ አንድ ካልሆንን ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛነት ለማመን ይከብዳታል። አንዱን ስም እየጠራን በ0ሥራ ሦስት ልብ ስንጠላለፍ ለዓለም የምናሳየው ሥዕል የአንድ መቅደስ ሥዕል ሳይሆን መቶ አንድ መሹለኪያ ያለው የሌቦች ዋሻ ነው። ሰዎች እኛን ባያምኑን አይገርምም ይሆናል፤ ጌታችን እንዳይታመን እንቅፋት ስንሆንበት ግን እጅግ አሳዛኝ ነው።

የአማኞች አንድነት የሚናጋባቸው አያሌ ምክንያቶች ቢኖሩም ዐበይት ከሆኑት መካከል እነዚህ ይገኙባቸዋል። አንዱ የአንድነት እንቅፋት ከልክ ያለፈ ግለኝነት ነው። ሁልጊዜ ስለ ራስ የግል ስጦታ፣ ስለ እኔ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ እኛ ቡድን፣ ስለ እኛ ብሔር፣ ስለ እኛ ራእይ የምናስብ የምናወራ ከሆነ አየሩ ይታፈናል። ባልንጀሮቻችንን በብረት አጥር ውስጥ እናስራቸዋለን። አንድነት የሚፋፋው የሌሎችን ስጦታ፣ የሌሎች ቤተ ክርስቲያን፣ የሌሎች ሰዎችን ብሔር የሌሎች ራእይ ለማወቅና ለማክበር ስንጥር ለማበልጸግም ስንሰናዳ ነው። "እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር" ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ።

ዘረኝነት፣ የብሔርና የቋንቋ ትምክህት፣ ያለአግባብ የተኮፈሰ የራስ ማንነት ወይም እጅጉን የደቀቀ የራስ ግምት እውነተኛ አንድነት እንዳይኖረን እንቅፋት ይሆናሉ። የክርስቲያን ማንነት መሠረት የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የትምህርት፣ የኑሮ ደረጃ መደብ ሳይሆን በመለኮት ጸጋ ምክንያት ያገኘነው የእግዚአብሔር ልጅነት ነው። ከዚህ የተደላደለ ማንነት ላይ ስንቆም የተቀሩትን መለያዎች ሁሉ አነስተኛ እናደርጋለን፤ እኛም በሰማያዊ የክብር መንፈስ ውስጥ እንሆናለን። ያን ጊዜ ሁሉን ለማቀፍ፣ አብሮም ለመብረር የሚችሉ ክንፎች እናበጃለን።

አንድነታችንን የሚያናጋ ሌላው በሽታ ከሌሎች በላይ ለመሆን ያለን ጠማማ ጉጉት፣ ከፍተኛውን ወንበር ለመያዝ የምናደርገው ሽኩቻ የሚያስነሣው የጥላቻና የፉክክር አቧራ ነው። "ጠብና ጦር ከወዴት ይመጣሉ..." (ያዕ. 4፥1)።

ሌላው የአንድነት ደንቃራ አገልጋዮቻችንን፣ መሪዎቻችንን እንደ ሰዎች ማየት ትተን የሰማይ ከዋክብት ስናደርጋቸው ነው። እነርሱ ደማቅ መብራት ከሆኑ እኛ በዙሪያቸው እያጨበጨብን የምንዞር የእሳት እራቶች ልንሆን ነው። ስማቸውን ጠርተን 'ዘራፍ የእገሌ አሽከር' እንዳንል የሚያሰጋበት አካሄድ ይታያል። መሪዎቻችንን ከማክበርና ከመታዘዝ በላይ ወደ ልዕለ ሰብእ ደረጃ ካሸጋገርናቸው በጤና የማሰብ ሥራችን ተጓጒለ ማለት ነው። የእነርሱን ጒድለት አንሥቶ የሚናገር ሰው ቢያጋጥመን ወይም ከእነርሱ የተሻለ አሠራር ቢገኝ ልንጣላቸው ነው። ይህ "ጭፍን ሎሌነት" ትልቁን አንድነት ያጠፋብናል።

ነቅተን ልንጠብቀው የሚገባን ይህ አንድነት አንዳንድ ጊዜ ሲታመም ምን እናድርግ? የአንድነት ሕመም ታክሞ ይድናል። አስታማሚ ከተገኘ፣ በሰዓቱ እየተጠበቀ መድኀኒት ከተሰጠው። ለምሳሌ አንዱ ኪኒን ይቅርታ ነው፤ አንዱ መርፌ እውነተኛ መወቃቀስ ነው፤ አንዱ መታሻ የጥሞና ውይይት ነው። ከታከመ ይድናል፣ እንኳን ከሰው ጋር ከመለኮት ጋርም ያለ ጠብ መድኀኒት አለው፤ "አዳም በበደለ መድኀኒዓለም ክሶ ..." እንዲል። እንደ ሰማይ አምላክ የምሕረት ዐውድማ ስንሆን፣ ቀረብ ብለን ስንተዋወቅ፣ ስንደማመጥ የተወላገደ አንድነት ወደ አቅሉ ይመለሳል።

2. ጽድቅ፣ ፍትሕና ምሕረት

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የማስታረቅ ሲሆን ማምለክና መጸለይ፣ የመንፈስን አንድነት መጠበቅና ኅብረትን ማራመድ ወንጌልን ማሰራጨት፣ ደቀ መዛሙርት ማፍራት ዐይነተኛ ተግባሮቿ ናቸው፤ ከዚያም ባሻገር ከኅብረተ ሰቡ አኗኗር ጋር በተያያዘ ሁኔታም ምግባረ ሠናይ ወይም የምሕረት አገልግሎት መፈጸም እንዲሁም የጽድቅ፣ የፍትሕና የሰላም ምሳሌ ሆኖ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ጽድቅን ፍትሕንና ሰላምን ማስረጽ ጥሪዋ ነው።

እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ፣ ጌታ ኢየሱስ ራሱ እንደተናገረው መንገዱ እውነተኛ ሕይወት የእውነትም ምስክር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የእውነት መንፈስ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራ መንፈስ ነው።

ቤተ ክርስቲያንም የእውነት ዓምድና መሠረት የክርስቶስ ኢየሱስ መግለጫ አካል ናት። ከቃሉ እንደምንመለከተው፣ እግዚአብሔር የጽድቅ የፍትሕና የምሕረት አምላክ ነው በምድር ላይም ጽድቅና ፍትሕ ሲሰፍን ምሕረት ሲኖኙ ደስ ይሰኛል።

> *ጽድቅና ፍትሕ የዙፋንህ መሠረቶች ናቸው ምሕረትና ታማኝነትም በፊትህ ይሄዳሉ (መዝ. 89፥14)፤*
>
> *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል "ጥበበኛ በጥበቡ አይመካ ኀያል በኀይሉ አይመካ ሀብታም በሀብቱ አይመካ" የሚመካ ግን "እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ በማወቁና በምድር ላይ ምሕረትን ፍትሕንና ጽድቅን የማደርግ መሆኔን በመረዳቱ በዚህ ይመካ፣ እኔ በእነዚህ ነገሮች እደሰታለሁና" (ኤር. 9፥23-24)፤*
>
> *"ሰው ሆይ መልካም የሆነውን አሳይቶሃል እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድን ነው? ፍትሕን ታደርግ ዘንድ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ በአምላክህም ፊት በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን" (ሚክ. 6፥8)።*

እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ ነው። ፍትሕ ከእርሱ ባሕርይ የሚመነጭ ሲሆን፣ ፍትሕ በምድር ላይ የሚሰፍነው በሰዎች መካከል ኀይልና ሥልጣን በአግባቡ ማለትም የእግዚአብሔርን መመርያ በጠበቀ መልኩ ሥራ ላይ ሲውል ነው።

በሰዎች ዘንድ ጽድቅ ሲታይ፣ በመካከላቸው ፍትሕ ሲካሄድ፣ በምሕረት መተሳሰብ ሲኖር እግዚአብሔር ይደሰታል። እነዚህ ነገሮች ደግሞ ለሰላም መስፈን መሠረቶች ናቸው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ሲያደርግ እርስ በእርሱም በሰላም ይኖራል። የእግዚአብሔርን መመሪያ አለማክበር ከእግዚአብሔር ጋር ጠብ መጀመር ነው። የእግዚአብሔር መመሪያዎች ደግሞ የራሳችን ሕይወት የሚለመልምበት፣ የግልም ሆነ የማኅበረ ሰብ ሰላማችን የሚንሰራፋበት መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን መመሪያ መተላለፍ፣ ቸል ማለት፣ በገዛ ሕይወታችንና በሰላማችን ላይ አሉታዊ ርምጃ መውሰድ ነው። በእግዚአብሔር ሥርዐት አለመሄድ ሕይወታችንና ሰላማችንን ራሳችን በራሳችን መጠናወታችን ነው። ጽድቅና ፍትሕ በሌለበት ሰላም አይኖርም፤ ሰላም ቢኖርም ጽድቅና ፍትሕ ሲጓደል ሰላሙ መልሶ ይደፈርሳል።

እግዚአብሔር በኅብረተ ሰቡ መካከል ያሉ፣ ኑሮ ያልደላቸው "አናሳ ክፍሎች" ፍትሕ እንዳይጓደልባቸው፣ የዕለት ጉርስና ልብስ እንዳያጡ፣ እንዳይገፉና እንዳይጨቆኑ ጥንቃቄ እንዲደረግላቸው የኪዳኑን ሕዝብ ሲያሳስብ እናያለን።

በዚህ አኳያ እግዚአብሔር፡-

1. ለመበለቶች
2. ለወላጅ አጦች ድኻ አደጎች
3. ለመጻተኞች
4. ለሙያተኞች በአጠቃላይ ለተናቁና ለሌላቸው ሲገደው ይታያል።

እግዚአብሔር ሰው ተፈጥሮን ይንከባከብና ይጠብቃት ዘንድ የሥራ ባለ ዐደራ ሠራተኛ አደረገው። ይልቁንም ሰው ለሌላው ሰው በጎነት የበለጠ ኀላፊነት እንዳለው ከዚሁ እንረዳለን። የተፈጥሮን ወይም የምድርን በረከት እያንዳንዱ ሰው የራሱ ድርሻ እንዲኖረው እግዚአብሔር በፍጥረት አባትነቱ ፈቅዷል። ለቀደመው የኪዳኑ ሕዝብ የደነገገው የኢዮቤልዩ ሥርዐት (ዘሌ. 25) ይህንኑ እውነት ያረጋግጣል።

በአንድ ቤት ውስጥ እንዳሉ በወላጆችና ልጆች ዘንድ እንደሚታይ ወይም መገኘት እንደሚኖርበት ዐይነት መተሳሰብ፣ አንዱ ለሌላው መጠንቀቅ፣ የአንዱን ደስታ ወይም ሐዘን ሌላው እንደራሱ አድርጐ ደስታውን መደሰት ሐዘኑንም መካፈል፣ ሸክሙን መሸከም ማለት ነው።

እግዚአብሔር የኪዳኑን ሕዝብ እንደ አንድ አባት ልጆች፣ እንደ ወንድማማቾች አድርጐ እንደሚቈጥራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስገነዝበናል። ይህም ቤተ ሰባዊ መተሳሰብ በዚሁ እውነት ላይ የሚመሠረት ነው።

በኪዳኑ ማኅበረ ሰብ መካከል በዝቅተኛ ደረጃ ለሚቈጠሩ ክፍሎች ጥንቃቄ እንዲያደርግ እግዚአብሔር አበክሮ ያስገነዝባቸዋል።

> *ለመጻተኛ ወይም አባት ለሌለው ልጅ ፍትሕ አትንፈገው፤ የመበለቲቱንም መደረቢያ መያዣ አታድርግ። አንተም በግብፅ ባሪያ እንደ ነበርህና አምላክህ እግዚአብሔር ከዚያ እንደ ተቤዠህ አስታውስ፤ ይህን እንድታደርግ ያዘዝሁህ ለዚህ ነው፤ የዕርሻህን ሰብል በምታጭድበት ጊዜ፣ ተረስቶ የቀረ ነዶ ቢኖር፣ ያን ለመውሰድ ተመልሰህ አትሂድ። አምላክህ እግዚአብሔር በእጅህ ሥራ ሁሉ እንዲባርክህ ነዶውን ለመጻተኛው፣ አባት ለሌለውና ለመበለቲቱ ተወው። የወይራ ዛፍን ፍሬ በምታራግፍበት ጊዜም ቅርንጫፉ ላይ የቀረውን ለመቃረም ተመልሰህ አትሂድ፤ ለመጻተኛው አባት ለሌለውና ለመበለቲቱ ተወው።" ዘዳ. 24፥14-15፤ 19-21*

በሰዎች መካከል በአንድ ወቅት ሚዛናዊ የሆነ የተደላደለ የኑሮ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ሁኔታው ተቀይሮ በሥራ እንቅስቃሴ ሂደት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ጉልሕ የይዞታ መበላለጥ ቢከሰትና የተወሰነ ክፍል ሲጐድልበት፣ ሲያጣ ሲነጣ በሕይወት መኖር መቻሉ ሲያጠያይቅ የተሳካለቱ በምሕረት ሌላውን ሊያስበው ደግሞ ይገባል።

የፍትሕና የምሕረት እንቅስቃሴ ማኅበራዊ የመተሳሰብና የጽድቅ ኑሮ ነው። እግዚአብሔር በንግድ እንቅስቃሴ፣ በዳኝነት አሰጣጥ፣ በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት፣ በማኅበራዊ መስተጋብር፣ በሕዝብ አስተዳደር፣ በሃይማኖታዊ ሥርዐት አፈጻጸም ሁሉ ጽድቅና ፍትሕ እንዲኖር ሕዝቡን ሲያሳስብ መመሪያ ሲሰጥ እናያለን። ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ማሳሰቢያ ቸል ሲል፣ መመሪያውን ጥሶ በመሄድ ፍትሕ ሲጓደልና ግፍ ሲፈጸም እግዚአብሔርን በነቢያቱ ያስጠነቅቃል፤ ዐሳቡን ሲቃወሙና ኪዳኑን አሌ ሲሉም አርጩሜውን ሲያነሣና ሲቀጣ በብሉይ ኪዳን ታሪክ እንመለከታለን።

> ጻድቁን ትጨቁናላችሁ ጉቦም ትቀበላላችሁ፤ በፍርድ አደባባይም ከድኻው ፍትሕ ትነጥቃላችሁ። ስለዚህ አስተዋይ ሰው በእንዲህ ያለ ጊዜ ዝም ይላል፤ ቀኖቹ ክፉች ናቸውና። በሕይወት እናንተ በፍርድ አደባባይ የሚገስጻችሁን ትጠላላችሁ እውነት የሚናገረውን ትንቃላችሁ። እናንተ ድኻውን ትረግጣላችሁ፤ እህል እንዲሰጣችሁም ታስገድዱታላችሁ፤ ስለዚህ ግን አትጠጡም፤ ኀጢአታችሁ ምንኛ ታላቅ እንደሆነ በደላችሁም የቱን ያህል እንደ በዛ በእኔ ትኖሩ ዘንድ መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ፤ ከዚያ በኋላ እንደተናገራችሁት፣ የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል። ክፉውን ጥሉ መልካሙንም ወደዱ፤ በፍርድ አደባባይም ፍትሕን አታጓድሉ ምናልባት የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ትሩፍ ይራራ ይሆናል። (አሞ. 5፥10-12፡15)

የንግድ እንቀስቃሴን በተመለከተ ማጭበርበር፣ ማታለል እንዳይኖር የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ያስጠነቅቃል። መለኪያው፣ መስፈሪያው፣ ሚዛኑ ሁሉ ሐቀኛ እንዲሆን ግድ ይላል። በዘመናችን በዓለም ዙሪያ ደረጃ መዳቢ የሚባለው መሥሪያ ቤት የአሠራር መነሻው በዚሁ መመሪያ ጽንሰ ሐሳብ ላይ የመሠረተ ነው።

> “በመስፈሪያ ወይም በሚዛን አታጭበርብሩ። እውነተኛ መለኪያ፣ እውነተኛ መመዘኛ፣ እውነተኛ የኢፍ መመዘኛ፣ እውነተኛ የኢን መስፈሪያ ይኑራችሁ። ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ። ሥርዐቴንና ሕጌን ሁሉ ጠብቁ፤ ተከተሏቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ” (ዘሌ. 19፥35-37)

> “የክፉት ቤት ሆይ፤ በግፍ የተገኘ ሀብታችሁን፣ በሐሰት መስፈሪያ የሰበሰባችሁትን አስጸያፊ ነገር እረሳዋለሁን? አባይ ሚዛን የያዘውን ሰው፣ ሐሰተኛ መመዘኛ ከረጢት የቋጠረውን ንጹሕ ላድርገውን? ባለጠጎቿ ግፈኞች፣ ሰዎችዋ ሐሰተኞች ናቸው፤ ምላሳቸውም አታላይ ናት።” (ሚክ. 6፥10-12)

በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኙ የሕዝብ አለቆች ኀይላቸውን ወይም ሥልጣናቸውን ፍትሓዊ ባልሆነ መንገድ ተጠቅመው የራሳቸውን ምኞት ለማርካትና ብልጥግና ለማሳደግ ቢጥሩ ሕዝብ ይሠቃያል፣ የኅብረተ ሰቡ አናሳ ክፍሎች ይጐሳቈላሉ፣ ይህም ፍጅትንና ኹከትን የሚጠራ እኩይ ተግባር ይሆናል። እንዲህ ዐይነቱን አካሄድ እግዚአብሔር ያወግዘዋል፤ ቁጣውን፣ ፍርዱን ያውጅበታል።

ሕግ የበላይ ሆኖ ሁሉም ሊያከብረው ይገባል፤ ይሁንና ሕግን ማስከበር ፍትሕ እንደ ሆነ ቢታሰብም እንዲከበሩ የሚወጡ ሕጐች ራሳቸው ፍትሐዊ ላይሆኑ ይችላሉ። የሚወጡት ሕጐች ለመላው ሕዝብ በጎነት ለማስገኘት ሳይሆን፣ አንድን የተለየ ክፍል ፍላጐት ለማሟላት ወይም ለመጉዳት ሆን ተብለው የሚወጡ ከሆነ ፍትሐዊ አይሆኑም። በዚህን ወቅት ሕግ አውጭውም፣ ሕጉም ኢፍትሐዊ ይሆናል። እንደነዚህ ዐይነት ሕጐች አምባገነናዊነትን፣ አጓጉል ሥርዐትን ሕጋዊ ለማድረግ የሚደነገጉ የሚታወጁ ይሆናሉ። ኢፍትሐዊ ሥርዐቶች ወይም ሕጐች በመንግሥትም፣ በሃይማኖት ክፍሎችም ሲወጡ፣ ሲደነገጉ መኖራቸው የታሪክ ሐቅ ነው። በዚህ ዐይነት አሠራር ግፍ ባለሥልጣን ይሆናል። በሐማ ቀስቃሽነት አይሁድ እንዲጠፉ የታወጀው ሕግ አስቴር 3 እንዲሁም በነቢዩ ዳንኤል (ዳን. 6) ላይ ቅናት ያደረባቸው የንጉሥ ዳርዮስ ሹማምንት ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ እንዲጣል ለማድረግ ከንጉሡ በስተቀር ማንም ወደ አምላኩ እንዳይጸልይ ወይም እንዳይለምን ሕግ ማሳወጃቸው እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው። የአይሁድ ሃይማኖታዊ ሸንጎ፣ ሐዋርያቱ በኢየሱስ ስም ፈጽሞ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ ትእዛዝ ማውጣታቸው ሐዋ. 4 ተጨማሪ ምሳሌ ነው።

> ፍትሕ የጐደለውን ሕግ ለሚያወጡ፣
> 　　ጭቆና የሞላበትን ሥርዐት ለሚደነግጉ ወዮላቸው
> የድኾችን መብት ለሚጋፉ፣
> 　　የተጨቆነውን ሕዝቤን ፍትሕ ለሚያዛቡ፣
> መበለቶችን ለሚበዘብዙ፣
> 　　ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ለሚመዘብሩ ወዮላቸው” (ኢሳ. 10፥1-2)

እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢያት ስለ ጽድቅ መጓደል፣ ስለ ፍትሕ መታጣት በእግዚአብሔር ስም ይናገሩ ነበር። ወደ ጽድቅና ፍትሕ የሕዝቡ መሪዎች አለቆች ሕዝቦችም እንዲመለሱ ጥሪ ያደርጉ ነበር ነቢያት። መሪዎችን፣ ነገሥታትን ስለ ጽድቅና ስለ ፍትሕ መጓደል ነቅፈው ሲናገሩ የመሪዎችን ቦታ የነገሥታቱን ዙፋን ለሥልጣን ጓግተው ከቶ አልነበረም። በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸው ሥልጣን ከፖለቲካ ሥልጣን ይልቅ እጅግ የከበረ መሆኑን ተገንዝበው ነበርና። ቤተ ክርስቲያን የነቢያትን አገልግሎት ስትወጣ በምንም መልኩ የፖለቲካ ሥልጣን ፍለጋ ከጅላ አይደለም፤ ሊሆንም ከቶ አይገባም።

ራሳችንን እንይ፣ እንፈትሽ። ራሳቸው ፍትሕ እንዳጓዳሉና ፍትሕ በተጓደለበት ዓለም እንደ ሚኖሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ምን ይጠበቅብናል? የትምህርትና የኑሮ ደረጃችን የተለያየ ቢሆንም እንደ እግዚአብሔር ሰዎች ወይም እንደ ቤተ ክርስቲያን ራሳችንን እየተቈጣጠርን ዙሪያ ገባችን እንዲጠራና መልካም እንዲሆን የጽድቅን፣ የፍትሕንና የምሕረትን መንገድ እንድንከተልና እንድናሳይ ታዘናል።

## 3. ፍትሕን የረገጠ አምልኮም ተቀባይነት አይኖረውም

እግዚአብሔር ሕዝቡ ጽድቅንና ፍትሕን ረግጦ የአምልኮ ሥርዐቱን ቢያደምቅ፣ የመሥዋዕት ጋጋታ ቢያቀርብ፣ ጸሎትና ዝማሬ ቢያበዛ፣ ምንም ስፍራ እንደማይሰጠው ደጋግሞ በነቢያቱ ተናግሯል።

"ዓመት በዓላችሁን ተጸይፌአለሁ፤
ጠልቼውማለሁ፤
ጉባኤዎቻችሁ ደስ አያሰኙኝም
የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል
ቁርባን ብታቀርቡልኝም፣
እኔ አልቀበለውም፤
ከሰቡ እንስሶቻችሁ የኅብረት መሥዋዕት ብታቀርቡልኝም፣
እኔ አልመለከተውም።
የዝማሬህን ጩኸት ከእኔ አርቅ፤
የበገናህንም ዜማ አልሰማም።
ነገር ግን ፍትሕ እንደ ወንዝ፣
ጽድቅም እንደማይደርቅ ምንጭ ይፍሰስ። (አሞ. 5፥21-14)

የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምኔ ነው? ይላል እግዚአብሔር ... በፊቴ ለመቅረብ ስትመጡ ይህን ሁሉ እንድታመጡ የመቅደሴን ደጅ እንድትረግጡ ማን ጠየቃችሁ? ... እጣናችሁን እጸየፋለሁ፤ የወር ማባቻ በዐላችሁን፣ ሰንበቶቻችሁን፣ ጉባኤያችሁን እና በክፋት የተሞላ ስብሰባችሁን መታገስ አልቻልኩም። የወር መባቻችሁንና የተደነገጉ በዓሎቻችሁን ነፍሴ ጠልታለች ሸክም ሆነውብኛል፤ መታገስም አልቻልሁም፤ እጆቻችሁን ለጸሎት ወደ እኔ ስትዘረጉ ዐይኖቼን ከእናንተ እሰውራለሁ አብዝታችሁ ብትጸልዩ እንኳን አልሰማችሁም ... ታጠቡ ራሳችሁንም አንጹ ክፉ ስራችሁን ከፊቴ አርቁ ክፉ ማድረጋችሁን ተዉ መልካም ማድረግን ተማሩ ፍትሕን እሹ የተገፉትን አጽናኑ አባት ለሌላቸው ቁሙላቸው ለመበለቶችም ተሟገቱ" (ኢሳ. 1፥11-17)

እናንት ግብዞች የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፤ ወዮላችሁ! ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት እየሰጣችሁ በሕጉ ውስጥ ዋነኛ የሆኑትን ማለትም ፍትሕን፣ ምሕረትንና ታማኝነትን ግን ንቃችኋልና፤ እነዚያን ሳትተዉ እነዚህን ማድረግ በተገባችሁ ነበር፤ እናንት የታወራችሁ መሪዎች፤ ትንኝን አጥርታችሁ ትጥላላችሁ ግመልን ግን ትውጣላችሁ" (ማቴ. 23፥23-24)

## 4. ለመልካም ሥራና ለፍትሕ እንነሣ

ያለፍንበትን የራሳችንና የኅብረተ ሰቡን ፍትሕ አልባ አኗኗር ተመልክተንና 'ፍትሕ መቼም አሸንፎ አይወጣም፤ እኔም አይሆንልኝም' በሚል ተስፋ አጥነት ተሸመድምደን በአዎንታዊ አቅጣጫ በመንቀሳቀስ ፈንታ ራሳችንም ጭልጥ ብለን እንዳንጠፋ፣ ሌሎችንም እንዳናጠፋ በተስፋ ልንነቃ በዚሁም ልንቆም፣ ልንራመድም ይገባናል። ጨለማውን ማውገዝ ብቻ ምንም ፋይዳ አይኖረውም፤ ብርሃን እንዲሆን መብራትን መለኮስ ወይም ባለንበት ራሳችን መብራት መሆን እንጂ፣ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በኅብረተ ሰቡ መካከል በተሰማሩበት መስክ ሁሉ የጨውነትንና የብርሃንነትን ሚና ቢጫወቱ የቤተ ክርስቲያን ተጽእኖ በመልካም አመራር አኳያ እውን ይሆናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ዮሴፍን፣ ሙሴን፣ ነህምያን፣ ኤርምያስ፣ ዳንኤልን፣ ሲድራቅ፣ ሚሳቅ አብድናጎን፣ መጥምቁ ዮሐንስን፣ ወዘተ. ማስታወስ ይጠቅማል።

ተስፋችን እንዲለመልም በጽድቅ፣ በፍትሕና በምሕረት ጐዳና እንድንጓዝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን አጥርቶ ማየት፣ ማሰላሰል፣ በእምነትም አንግቦ መነሣት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

በኑሮው የተደላደለ ሰው ለተቸገረው ሰው፣ ጉዳት ለደረሰበት እንክብካቤ እንዲያደርግ እግዚአብሔር ያዛል። የእግዚአብሔር ወገንነት የሚገለጠው በዚሁ ምግባረ ሠናይ የተሞላ አኗኗር ነው። በኢሳ. 58 ላይ እውነተኛ መንፈሳዊነት የጾምም ይዘት፣

- የጭቆና ሰንሰለት መበጠስ - የተጨቈኑትን ነጻ ማወጣት፣
- የቀንበርን ገመድ መፍታት - ቀንበርን መስበር፣
- ምግብን ለተራብ ማካፈል፣ ለተንከራታቾቹ ድኻ መጠለያ መስጠት፣
- የተራቆተውን ማልበስ፣
- ችግረኛውን የሥጋ ዘመድን ፊት አለመንሣት፣ የመሳሰሉት ትሩፋት መሆናቸውን አበክሮ ያስረዳናል።

ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻው የፍርድ ቀን ለሰው ልጆች የሚያቀርበው ጥያቄ፣ እንዴት የምድርን ኑሮ ተጓዛችሁ በሚል ረገድ የሚታዩት የግምገማ ጥያቄዎች:-

- ተርቤ - አበላችሁኝ?
- ተጠምቼ - አጠጣችሁኝ?
- እንግዳ ሆኜ - ተቀበላችሁኝ?
- ታርዤ - አለበሳችሁኝ?
- ታምሜ - ጠየቃችሁኝ?

- ታስሬ - ጠየቃችሁኝ?

በሌላ አነጋገር በእነዚህ ርእስ ጉዳዮች አንጻር ምን ምግባረ ሠናይ አከናወናችሁ? ምን የምሕረት አገልግሎት ፈጸማችሁ? የሚል ነው። ይህም በጎ አድራጐት በጌታ ዘንድ ታላቅ ቦታ እንዳለው ያስገነዝባል።

በተራራው ስብከት እንደተጠቀሰው "ሰዎች መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰዎች ፊት ይብራ" የሚለው የጌታችን ትእዛዝ የሚያተኩረው ተከታዮቹ በኅብረተ ሰብ ውስጥ በሚያሳዩት ቀና አመለካከትና ምግባረ ሠናይ ላይ ነው።

እንግዶችን መቀበል (ዕብ. 13፥2)፣ ታማኝ መሆን (ማቴ. 22፥21)፣ ሥራን አክብሮ በትጋት ማከናወን (1ጢሞ. 6፥6-9፤ 2ተሰ. 3፥6-12)፣ ማኅበራዊና አስተዳደራዊ ኀላፊነትን ለመቀበል ዝግጁ መሆንና በቅንነትና በርትዕነት ኀላፊነትን መወጣት ግዴታችን ነው።

ቤተ ክርስቲያን

- የመንፈስ አንድነቷን ጠብቃ፣
- የማስታረቅ ተልእኮዋን አንግባ ተስፋን እያበሰረች፣
- ዓለምን መድረሻዋ እግሯ በብትውና ሳይሰናከል፣ ገለልተኛ ሳትሆን ወይም በሌላው አጽናፍ በዓለሜዋነት ሳትበረዝ፣ ሳትከለስ፣ ሳትወሰድ፣
- በምድር መጻተኝነን ሳትረሳ፣
- "ኢየሱስ ጌታ ነው" "ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" የሚለው ማተቧን አጽንታ ይዛ፣
- የመንፈስ ቅዱስን እና የትንሣኤውን ኀይል ለብሳ፣
- የመስቀሉን ድል፣ የስሙን ሥልጣን ተጎናጽፋ፣
- የሞትና የትንሣኤ ሕይወት አካሄድን ዘይቤ ዘይቤዋ መሆኑን ሳትዘነጋ፣
- የፍትሕና የሰላም አብነት ሆና፣ ፍትሕንና ሰላምን በኅብረተ ሰቡ ዘንድ የማስረጽ ጨውነቷን አክብራ፣
- "በሰማይ ያለውን አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት እን ዲሁ ይብራ" በሚለው መርሕ መሠረት ከምግባረ ሠናይ፣ ከምሕረት አገልግሎት ሳትርቅ ልትኖር የተጠራች፣ በጨለማው ዓለም ውስጥ ብርሃን ፈንጣቂ ደማቅ ኮከብ ናት።

በዚህ ጸንታ ቤተ ክርስቲያን

- ከዓለም የተለየች መሆኗን ቀርቶ በዓለም የተዘፈቀች የተደፈቀች ብትሆን፣
- በምድር መጻተኝነቷን ረስታ ከዓለም ጋር ብትቈራኝ፣ በስግብግብነት መንፈስ ከዓለም ጋር ምድራዊ ትርፍን ለመቀራመት የምትራኮት የምትናጠቅ ብትሆን፣
- የጽድቅን የፍትሕን መለኪያ፣ ማንጸሪያ፣ ማነጣጠሪያ፣ እውነትን ብትጥል ወይም የእውነትን ማስመሪያ ብታቈላምም፣
- በዓለም ዋጋ አሰጣጥና ልማድ ብትለከፍ፣ ብትወረር
  - ዓለም በምታነፍስበት ሰፌድ ብታነፍስ
  - ዓለም በምትሰፍርበት ቁና ብትሰፍር
  - ዓለም በምትጠጣበት ጽዋ ብትጠጣ
  - ዓለም የምትደልቀውን ከበሮ ብትደልቅ

ረሷ ጥፋት ሆነች። የእውነት ዐምድና መሠረት የመሆን ጥሪዋን ጥላ በክፉ ተያዘች፤ ከዓለምም የባሰች ለመሆን ተሰለፈች ማለት ነው። "ከለማበት የተጋባበት" እንዲሉ፤ "ከከሃዲዋ ከዳተኛይቱ" እንዲሉ።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ይህን መሰል ብርቱ ግፊት በየአቅጣጫው አለባት። ሲሆን፣ ሲሆን ዓለምን ሙሉ በሙሉ እንድትመስል፣ ካልሆነም እንድትሸቃቅጥ የሚያስደርግ ግፊት አለባት። ፍሬው ከፍሬ ፈርስኪው ጋር፣ ጠቃሚው ከአቲሆ ባቲሆው፣ ምርጡ ከአርቲ ቡርቲው ጋር፣ የከበረውን ከተዋረደው ጋር እንዲቀያየጥ የሚያደርግ ከፍተኛ ተጽእኖ አለባት።

## VII. የሕይወት ጥራት መጓደል ሰበቦች

አሁን አሳሳቢ ሆኖ እያስጨነቀን ያለው የሕይወታችን ብልሽት እንዲሁ ሳይዘራ የበቀለ አይደ ለም። መነሻ ሰበቦች ያሉትና በጊዜው ባለመነቀላቸው ምክንያት ሥር እየሰደዱ የመጡ አጥፊ አራሙቻ ናቸው። ሰበቦቹ ብዙ ቢሆኑም ጥቂቱን ማንሣት ተገቢ ነው።

1. የግልና የጥሞና ጊዜ:- የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና ጸሎት ችላ እየተባለና እየተተወ መምጣቱ ለመንፈሳዊ ሕይወት ባዶነትና ብልሹነት ዋነኛ ሰበብ ሆኗል። በአንዳንድ ስፍራ እንዲያውም 'ጸሎት ምን ያደርጋል? ሁሉን ነገር በእምነት መቀበል ብቻ ነው' የሚል የድፍረት አባባል እስኪሰማ ድረስ በጥሞና፣ በንስሓና በጸሎት ልምምዶች ላይ የሚሰነዘሩ እኩያን አስተሳሰቦች የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት ክፉኛ ጎድተዋል።

   "ከአፉ ከወጣው ትእዛዝ አልራቅሁም፤ የአንደበቱንም ቃል ከዕለት እንጀራዬ አብልጬ ይዣለሁ" (ኢዮ. 23፥12)፤

   "ቃልህን አሰላስል ዘንድ ዐይኔ ሌሊቱን ሁሉ ሳይከደን ያድራል" (መዝ. 119፥148)

2. የኅብረት የጸሎት ሕይወት መኮሰስ፡- በኅብረት የጸሎት ጊዜ አሁን ልማድ ሆኖ የመጣው አካሄድ ጸሎትን የማምከን አዝማሚያ አሳይቷል። በጋራ የጸሎት ጊዜ፣ ጸሎት መሪ የተባለው ብዙ በመናገር፣ አሁንም አሁንም በመናገር የጸሎቱ ተሳታፊዎች በሰቂለ ኅሊና (concentration) መጸለይ እንዳይችሉ ከአምላካቸው ጋራ ተራክቦ እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ጸሎት መሪው ራሱ በጸሎት መትጋት ሲገባው 'በእንጸልይ' ስም አግባብነት የሌለው ተደጋጋሚ ገለጻ በማድረግ የጸሎቱ ወቅት ይዋገዳል፤ የብዙኀኑም የየግል ጸሎት ሲደናቀፍ ይስተዋላል። ስብከት አይሉት ትምህርት የጸሎት መሪው ንግግር ጸሎትን የሚያጨናግፍ እየሆነ ነው። ጸሎት መሪ የማኅበሩን ጸሎት ገፍታሪ ወይም ጠፋሪ ሊሆን አይገባም።

3. በአማኞች መካከል በቅርብ ዓመታት ውስጥ ለሕይወት ለውጥና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት ከሚሰጥ ክብርና አድናቆት ይልቅ ለታምራትና ለውጫዊ ስኬት የሚታየው ናፍቆትነት እየተስፋፋ መምጣቱ የሕይወት ዕድገትንና ጥራትን እጅግ የጎዳ ነገር ነው። የሰው ልብ መሻት ከጌታ ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ማጠንከር ላይ ሳይሆን ምልክትና ተኣምር ማሳደድ ላይ እንዲሆን አድርጓል። ይህም ጌታችን "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ሁሉ ምልክት ይሻል" (ማቴ. 16፥4) ሲል የተናገረውን ቃል ያሳስበናል።

ምልክቶችና ተኣምራት ሁሉ ወደ ፈሪሃ እግዚአብሔርና ተአምኖ እግዚአብሔር ሊወስዱን ሲገባ የበለጠ ታምራት የማየት ጥማት እንደ ጨው ውሃ የሚቀሰቅሱብን ከሆነ ቆም ብለን ራሳችንን መጠየቅ ግድ ነው።

4. በቀድሞ ዘመን የነበሩት ንዑሳን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች የጸሎትና የምክክር ጉባኤዎች ከየቦታው እየጠፉ መሄዳቸው ማንም ለማንም ተጠያቂ እንዳይሆን ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ በእርስ በርስ መተናነጽ ይገኝ የነበረውን ጸጋም አሳጥቶናል። ንጹሕ የኅብረት ሕይወትም ቀስ እያለች ተሰለመለመች።

5. ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ባሁኑ ዘመን ካለንበት ሉል አቀፋዊ ዐውድ የነተሣ እየተስፋፉ የመጡ ባዕድ አስተሳሰቦች እንደ ድኅረ ዘመናዊነትና ሴኩላሪዝም (ሃይማኖት ወገድ ሥርዐት) ያሉ ፍልስፍናዎች እምነትንና የሞራላዊ ሕይወትን አቋም ብስክስክ እያደረጉት ነው። ሥነ ምግባርን በአንጻራዊነት የሚያዩ፣ ቋሚ እውነት ቋሚ የሞራል መለኪያ መኖራቸውን የሚክዱ፣ ቁስ አምላካዊነትን የሚያራግቡ እነዚህ አስተሳሰቦች የውስጥ ጥንካሬያችንን እየበሉት ነው።

6. ሌላው ዋና ነገር አማኙ ግለ ሰብም ሆንን ቤተ ክርስቲያን በትልቅ መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ እንዳለን መዘንጋታችን ነው። ዲያቢሎስና ርኵሳን መናፍስቱ ዋና ሥራቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት ልጆች በፍርሃት፣ በግዴለሽነት፣ በታችኛይቱ ጥበብ፣ በእብሪትና በስግብግብነት፣ ወዘተ. እየሸነገሉና እየነዱ ከእውነት መንገድ እንድንወጣ፣ ሕይወታችን በኀጢአት እንዲበከል ዐቅማችን እንዲላሽቅ የማያቋርጥ ዘመቻ የሚያደርጉ ናቸው።

እንግዲህ እነዚህ ምክንያቶች ሕይወታችን በከፍተኛ ደረጃ እያሽቆለቆለ እንዲመጣ ሰበብ ሆነዋል።

## VIII. የመፍትሔ ዐሳቦች

ከትምህርት ጉድለት ለሚታየው የሕይወት ጥራት ችግር የሚከተሉት ተግባሮች በመሪዎችና በአገልጋዮች በቁርጠኝነት መተግበር ይኖርባቸዋል፡-

- የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ወንጌል እንደገና ለወንጌላውያን ማኅበረ ምእመናን ማስተማር፤
- የደቀ መዝሙርነት ትምህርት በስፋት ማከናወን፤
- አገልጋዮችን ወደ መስክ ከመላክ በፊት የአገልግሎትን ምንነት ማስተማር፤
- በንዑሳን ቡድኖች በየቤቱ እና ቤተ ክርስቲያን የሚኖሩን ስብሰባዎች ይዘትና አካሄድ እውነተኛ መንፈሳዊነትን እንዲያዳብሩ በቃሉና በጸሎት መቃኘት፣ ለኑዛዜ፣ ለንስሓ፣ ለምስጋና፣ ለምስክርነት፣ ለምክክርም የተመቹ ማድረግ፤ በቅድሚያም እነዚህ ቡድኖች መመሥረታቸውን ማረጋገጥ፤
- ሆን ተብሎ ከእንቢተኝነትና ከልበ ደንዳንነት ለሚነሡ የሥነ ምግባር ችግሮች በማኅበረ ምእመናን ደረጃ በመቀጠልም በቤተ እምነት ደረጃ የሚከተሉትን ርምጃዎች በቁርጠኝነት መውሰድ አማራጭ የላቸውም፤
- የጸሎት መሪዎች ምእመናን ከእግዚአብሔር ከአምላካቸው ጋር እንዲገናኙ፣ በእውነት እንዲጸልዩ ማገዝ እንጂ በመግለጫ ብዛትና ንግግር የጸሎት ጊዜውን እንዳይፈጁ፣ ጸሎቱንም እንዳያመክኑ አስፈላጊውን የጥንቃቄ ርምጃ መውሰድ፤
- ቃሉ እንደሚያዘው የምክር፣ የተግሳጽ፤ የማቅናት አገልግሎት በግል ማከናወን፤
- ከዚህም ሲያልፍ በምስክሮች ፊት መምከር፣ ለማቅናት መሞከር፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተመክሮ ለመስማት አሻፈረኝ ባዩ ላይ የእርምት (የዲሲፕሊን) ወይም የማግለል ርምጃ በቅንነትና በትሕትና መውሰድ።

## ማጠቃለያ

ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ፊት በውስጥ ማንነቷ ቆሽሾ ፊቷ ተጨማትሮ ቈዳዋ ሹብሽቦ መልከ ጥፉ እንዳትሆን፣ ዐይኗ አጥርቶ ማየት እንዳይሳናት፣ አቅመ ቢስ ኮሳሳ፣ ቀሰስተኛ፣ ከንፈሯም የደረቀ፣ ምላሷ ያረረ ድምፅ አልባ ዲዳ እንዳትሆን፣ በጨለማ ኀይላት ፊት የምትፈታ እንዳትሆን፣ በክርስቶስ መስቀል አንባ ዘንድ መገኘት ይገባታል። ከላይ የሚወርደውን ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን የትንሣኤ ኀይል መልበስ፣ መቀደስ ያስፈልጋታል።

‘በዚህ ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ፤ እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይቋቋሟትም አይችሏትም’ የተባለው እውነት በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ጥንትም ዛሬም ነገም የሚሠራ ነው። ጸጋው በዘመን ሁሉ ጽኑ ነውና፡ ጸጋው ለድነት፣ ለመቀደስ፣ በክርስቶስ መገለጥ የተዋረደውን ሰውነት በከበረው የትንሣኤው አካል ለመለወጥ የሚያበቃ ነው። ዋስትናችን፣ ተስፋችንም ይኼው በክርስቶስ ኢየሱስ የሚገኘው ጸጋ ነው።

“እነሆ እስከ ዓለም ፍፃሜ፣ ከእናንተ ጋር ነኝ” ያለ ጌታ አብሮን ይሆናል። ለእኛ መንገድም እውነትም ሕይወትም ድልም ክብርም ብልጽግናም እርሱ ነው።

እንዲህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ትወጣለች። ለደከሙት ማረፊያ፣ ለባዘኑት አምባ፣ ለተሠበሩት መጠገኛ፣ የሕይወት ትርጒም ላጡ ትርጒም ማግኛ፣ ለተራቡ ምግብ፣ ለተጠሙ የሕይወት ውሃ መመንጫ ትሆናለች። የተፈራች የተከበረች በችግር ጊዜ በኅብረተ ሰቡ ዘንድ ለመፍትሔ የምትፈለግ ተናፋቂ ትሆናለች።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ያድስልን፤ በቤተ ክርስቲያን ፈሪሃ እግዚአብሔርን ያስፍንልን። መላውን ማኅበር በእውነት ቃል በጠራ ሕይወት የታነጸ ያድርግልን።

በልዩ ልዩ ዘርፍ የሚያገለግሉትን ኀልማሶችንና ወጣት አገልጋይ መሪዎችን በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያስታጥቅልን፤ በጥበብ በማስተዋልና በፍቅር የተሞሉ ተተኪ መሪዎችን ያስነሣልን።

ክብር ለእግዚአብሔር አብ

ክብር ለእግዚአብሔር ወልድ

ክብር ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሁን!

## የሕይወት ጥራት ዙሪያ የቀረቡ የውይይት ጥያቄዎች

1) የግል፣ የቤተ ሰብና የማኅበር የጸሎትና የቃል ትኩረት መዳከሙ ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩት ይችላሉ። እንዴት ወደ ብርቱ ጥሞናዊ ሕይወት መመለስ እንችላለን?

2) ከጊዜ ወደ ጊዜ በባልና በሚስት፣ በወላጆችና በልጆች መካከል ያለው ግንኙነት መሠረቱ እየተነቃነቀ በቤተ ሰብ ላይ ብዙ ጉዳቶች እየደረሱ እንደ ሆነ ይታወቃል፡፡ ይህንን ጉልሕ ችግር ለመፍታት ልንወስደው የምንችለው የመፍትሔ ዐሳብ ምንድን ነው?

3) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩትን በዘር፣ በጎሣና በብሔር ልዩነት እየታከኩ የሚመጡ የቡድናዊነት የጥላቻና የቂም ፈተናዎች ለማለፍ ከእያንዳንዳችን ምን ይጠበቃል? የቤተ ክርስቲያን ድርሻና ኀላፊነትስ ምን ሊሆን ይገባል?

4) በመልካም ሥራ ብርሃናችን እንዲታይ ተጠርተናል። ወንጌላዊው አማኝ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ብርሃንና ጨው እንዲሆን ምን እናድርግ? በምን መንገድ መተጋገዝ እንችላለን።

5) ለብዙ የሥነ ምግባር ችግሮች መነሻ የሆኑትን ሰበቦች አውጡና ተነጋገሩ። እንዴት ከዚህ አደጋ ማምለጥ እንችላለን?

6) ከላይ በተነሡ ችግሮች አኳያ፣ ራሳችንን ስንመረምር በግልም ሆነ በጋራ ንስሓ ልንገባባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ምንስ የንስሓ ፍሬ እናሳይ?

## በሕይወት ጥራት አንጻር ከተሳታፊዎች የተሰጡ የመፍትሔ ነጥቦች

1. የጥሞና ሕይወትን፣ የጸሎትንና ቃሉን የማጥናት ልምምድን ሳያቋርጡ ማስተማርና መሪዎች ምሳሌ በመሆን ማሳየት፤
2. በየቤተ ክርስቲያኑ በየማለዳው የሚደረገውን ጸሎት አጠናክሮ መቀጠል፤
3. በቤተ ክርስቲያን መድረኮች የሚቀርበው ስብከትና ትምህርት አዳማጩን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዲያተኩር የሚያደርግ መሆኑን ማረጋገጥ፤ አቅራቢዎቹንም ለዚሁ ማሠልጠን፤
4. ለጥሞና የሚረዱ መመሪያዎችና መጻሕፍት ማዘጋጀት፣ ለቤተ ሰብም፣ ለቤተ ክርስቲያንም ተከታታይ የሆነ ሥርዐተ ትምህርት ማበጀት፤
5. በእውነተኛ መንገድ የጸጋ ስጦታዎችን የሚለማመዱትን ማበረታታት፤ ብስለት የጐደላቸውንም በትዕግሥትና በጥንቃቄ ማረም፤
6. በቤተ ሰብና በጋብቻ ዙሪያ ሥርዐት ያለው፣ ነባራዊ ሁኔታውንም ያገናዘበ ተከታታይ ትምህርት በጽኑ መስጠት፤
7. ወላጆች ልጆቻቸውን ማወቅ፣ ጓደኛም ማድረግ፣ ጥሩ ምሳሌም ሆኖ ራስን ማቅረብ፤
8. ሕጻናትና ልጆች ሰው እና ሀገር ወዳጆች እንዲሆኑ ማስተማር፤ የሚዲያውን ጐጂ ገጽታ እንዲጠነቀቁና መርጠው እንዲጠቀሙ ማሳሰብ፤ ራሳቸው በግላቸው ጸሎትን፣ ጾምንና የቃሉን ጥናት እንዲለማመዱ ማበረታታት፤
9. በአብያተ ክርስቲያናት መካከል መቀባበልና መከባበርን እያጐለበትን የተሳሳተ ሥነ ምግባር አካሄድን በጋራ በመቃወም ተጠያቂነትን ማዳበርና ቤተ ክርስቲያን የክፉዎች መደበቂያ እንዳትሆን መጠንቀቅ፤
10. የአገልጋዮችን የኢኮኖሚ ሁኔታ በማሻሻል ከእጦት የሚነሡ የሥነ ምግባር ጉድለቶችን ለመቅረፍ መጣር፤
11. በቤተ ክርስቲያን ለትንንሽ ቡድኖች ሁነኛ ስፍራ ሰጥቶ፣ በሚጠቅም መንገድም አደራጅቶ የመንፈሳዊ ዕድገት ማእከል ማድረግ፤
12. ቤተ ክርስቲያን ኅብረተ ሰብን በሚመለከት በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ጽሑፎች፣ መጻሕፍት እያዘጋጁ ውይይትንና ጥናትን ማድረግ፤
13. በየሙያ መስኩ ለተሠማሩ ክርስቲያን ወንድሞችና እኅቶች አካባቢያቸውን ባገናዘበ ሁኔታ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እንዲያዳብሩ ሥልጠና መስጠት፣ እገዛም ማድረግ፤

# የተሐድሶ ጥሪ

መመርመር - መመለስ - መታደስ
በግልም በቤተ ክርስቲያንም ደረጃ

*“እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን፤
ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ” ሰቆ. 5÷21*

# የአስተምህሮ ጥሪት

# I. መግቢያ

እውነተኛውን ወንጌል የሚሰብኩ ለመጽሐፍ ቅዱስ ዐሳብ በታማኝነት የሚቆሙ፣ ቃለ እግዚአብሔርን በሕይወትም፣ በትምህርታቸውም የሚያከብሩ አገልጋዮች መኖራቸው እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ምክንያት ነው። አሳሳቹን የዘመኑን ነፋስ እየተቋቋሙ እውነተኛይቱን መንገድ ለመጠበቅ የሚጥሩ ቅን ምእመናንም በየስፍራው አሉ። ይህ እንዳለ ሆኖ በአጠቃላይ ሲታይ ግን የቀናና የጠራ ትምህርት እጦት እየተባባሰ መጥቷል።

የክርስቶስ ተከታዮች የተባልን እኛ ይብዛም ይነስም እንጂ በብዙ ረገድ ከመሥመር የወጣን፣ ከደረጃ የወረድን፣ አሳሳች ወለብላባ መልክ ያበጀን እንደ ሆነ ከገባን ቆይቷል። ይህ ብልሽት ሁለንተናችንን ያዳረሰ ቢሆንም የሚጀምረውና የሚጎለብተው በአስተሳሰብና በአስተምህሮ መደብ ላይ መሆኑ ብዙ የሚያነጋግር አይደለም።

ትምህርታችን ከተጣመመ የሕይወት ጉዟችን እንደሚሰነካከል ግልጽ ነው፤ ብልሹ ሕይወትም ተመልሶ አስተምህሮን ይበራረርዛል፤ አስተምህሮ ሲበረዝ ወይም ሲሸቃቀጥ ወይም ባዕድ አስተሳሰብ ሲጫነው ኑሯችን ውልግድግድ ይላል። ሕይወታችንንና አገልግሎታችንን በማነጽ ፈንታ የተገነባውን እየናደ እየፈረካከሰ ይሄዳል ወይም የማያለማ የማያሰማ ከጽድቅ የራቀ ፋይዳ ቢስ እየሆነ ይመጣል፤ አንድነታችን ይናጋል፤ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን ስም ያሰድባል፤ ለክብሩ ወንጌል መስፋፋት እንቅፋት ይሆናል።

ባለፉት ሁለት ዐሥርት (ዓመታት) በእኛ በወንጌላውያን መካከል የተከሰተው የእውነት ቃል መንሸራተት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደሷል:: በቤት፣ በቤተ ክርስቲያን ምስባክ፣ በመገናኛ ብዙኀን፣ ይህም ማለት በኅትመት፣ በኤሌክትሮኒክ መገናኛ፣ በኢንተርኔት፣ በስብከት ቃል፣ በትንቢት ቃል፣ በጸሎት አንደበት፣ በመዝሙር ቃል፣ የሚተላለፈው በየመስኩ ሁሉ ላይ የተዘራው፣ የበቀለውና የሚሰበሰበው መከር በርጋታ መበጠር፣ መፈተሽና መጤን አለበት።

ሜዳውን የሞላው እንክርዳድ፣ ‘የትከብራለህ’ ሰበካ፣ ሤርና ሥራ ሥር አብዛኛው ገዳይ መርዝ ነው፤ ያልገደለም እንደ ሆነ፣ ዐቅም እያሟሸሸ አጥመልምሎ ቤት የሚያውል ወይም ልቦናን እያነሆለለ የሚያስቀባዥር ክፉ ሥራይ (መርዝ) ነው።

መስኩን የሞሉት የግል ገድላ ገድል ትረካ፣ አልፎ አልፎ መስቀሉም ቢነሣ የክርስቶስን መስቀል ትሩፋቱን እንጂ አርአያውን፣ ማለትም መስቀል ተሸክሞ ጉዞን የማይዳስሱ ትምህርቶች ናቸው። ስሙን እያነሡ፣ ያስገኘልንን ጥቅም እየዘከሩ ነገር ግን መስቀሉ የሕይወት ዘይቤ የአካሄድ ፋና የሌለው ይመስል በረከቱን ዘርፎ የራሱን ሩጫ ሰው ሁሉ በየፊናው በመሰለው እንዲሮጥ የሚያበረታቱ አስተሳሰቦች ናቸው። ‘እርሱ መስቀሉን ተሸከመ’ እንልና ‘እኛ መስቀሉን እንሸከም’ የሚለውን እንዘለዋለን፤ ‘እርሱ ስለ እኛ ሞተ’ እንልና ‘እንግዲያስ እኛም ሞትን’ የሚለውን እንዘለዋለን:: መስቀሉ ማትረፊያ ብቻ እንጂ መኖሪያ መሆኑን አናወሳውም።

የእግዚአብሔርን መንግሥት አስቀድሞ ከመሻት ከመስበክ ይልቅ የእኛኑ መንግሥት ማስፋፋት፣ ያሁኑንና የዚህን ዕለታዊ ኑሮ ምቾት ምድራዊ ምኞትና ጥማት ለማሟላት ገንዘብ ንብረታዊ ብልጽግናን እንደ ባንዲራ እያውለበለብን ነን። ይሄው እንግዳ ዘር በየመስኩ ላይ በቅሎ እየተኮተኮተለትም ያለ ነው። በክርስቶስ ተከታዮች ልቦና ፍቅረ ንዋይን መዝራት፣ ሃይማኖትን የስግብግብነት ችግኝ ማፍያ መደብ ማድረግ እንዴት አያስጠይቀንም ትላላችሁ? ለጌታ አገልግሎት በራስ ፈቃድና በደስታ ገንዘብ የመስጠትን የልግስና ጥሪን በአጸፋው በሚገኝ አማላይ የደለበ ኪስ ተስፋ እንቁልልጩ እንዴት እንቀሰቅሳለን? የዕለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ እያጡ ወንጌል በሰበኩት ቀዳሚዎቻችን ላይ የምንሳለቀውስ በምን ድፍረት ነው?

“ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው” የሚለው ክቡር ዐዋጅ የፌዝ ቃል እስኪመስል ድረስ ያለ ውስጣዊ ልቡና ተገዥነት ይለፈፋል፤ የእርሱን ጌትነት ከእኛ ሎሌነት ለምን እናፋታዋለን? ይልቁን ይባስብለን በእርሱ ፈንታ ሰዎችን አጌተየን (አነገሥን)፣ ሥጋ ለባሾችን አደመቅን። በየስብከቱ የሚደመጠው የሥጋ ለባሽ ልዕልና፣ መለኮት አከል ግርማና የነገር ሁሉ ማእከል እስኪመስል ድረስ ማንቆለጳጶስ ምን ይባላል? ምንስ ጸጋ ቢሰጠው፣ ምንስ ችሎታ ቢኖረው፣ ምንስ የደለበ ልምድ ቢያካብት ሰው አምላክ የሆነ ይመስል በግለ ሰቡ ፊት ማደግደግና የዝና ማራገቢያ ይዞ ዙሪያውን መሽከርከር ማሸርገድስ ምን ይባላል?

በየተረተሩ፣ በየጉብታው አጀፍጅፎ የበቀለው ሽለቆውን ሁሉ የሞላው ነገር ደግሞ ሽለላን ፉከራን የተከናነበ ባዶ ጬኸት ነው። በውጫዊ ድምፅ ብርታት የሚያምን፣ በአምላኩ ፊት ጥሞናን ግን እጅግ የሚፈራ በጸጥታ የሚፈሰውን ሰማያዊ ኅብረ ዜማ ለመስማት የልብ ጆሮው ያልተቃኘ፣ የራሱን ድምፅ በመስማት ግን ጮቤ የሚረግጥ፣ የሚቦርቅ፣ የሁካታ እንቅስቃሴ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ አለ።

መጽሐፉ ‘ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል’ አለ፤ ‘የመንፈሱ ማደሪያ ለመሆን አብረን የምንሠራ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነን’ ተባልን፤ ይህን ሁሉ እየሰማንና እኛም እያወራን ርግጡን ስንጠይቅ ግን ቤቱ በብዙ ቦታ የሸማችና የሻጭ የገበያ አዳራሽ መሆኑን መካድ አልቻልንም። እኛ አገልጋዮቹ ገበያ እንዳናጣ የማናጤሰው የጢስ ዐይነት የለም። ሸማችነት የተጠናወተው አማኝ ማኅበረ ሰብም እንደ ሱቅ በሚያያት ጸሎት ቤት አዳዲስ ዕቃ ካልገባ ጥሎ ለመሄድ አያመነታም። “ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያንን ለራሱ ሊያቀርብ” ሙሽራው ዋጋ ከፍሎ ሳለ የእኛ ውሎ ግን በሌላ ሌላ ጉዳይ ላይ መሆኑ እጅግ እንግዳ ነገር ነው፤ ከክፉ ዱር ነፋስ ያመጣው ባዕድ ዘር ነው። ቅዱስ ደሙን አፍስሶ የገነባውን የቤቱን ባለቤት ከቤቱ አስወጣነው፤ ከደጃፉ ሆኖ ቢያንኳኳም አልከፈትንለትም፤ አላከበርነውም (የሎዶቅያን ቤተ ክርስቲያን ያስታውሷል)::

በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ቆመን ዕንቅብ ሙሉ የሰው ዐሳብ እየነዛን፣ እያዘራን የዕንቅቡን ክፈፍ በቃሉ ሥሥ ቆዳ ብንለጉም የቃሉን ባለቤት እግዚአብሔርን ያሳዝናል። ከየጎዳናው ላገኘነው ሐሳብ መንደርደሪያ፣ ከየማድጋው ለምንቀዳው ውሃ ማጣፈጫ ብናደርገው፣ ቃሉን ሰበክነው ሳይሆን ታከክነው ማለት ይቀላል። ለቃሉ ታላቅነት ከአንገት በላይ የከንፈር አክብሮት እየቸርን በዕለት ኑሯችን ግን እያቀለልነው እንታያለን። ጽላቱን ተሸክመን ትእዛዛቱን ግን እንረግጣለን:: መምህሩም፣ ደቀ መዝሙሩም፣ ንግግሩም፣ መናገሪያውም በብዙም ይሁን በጥቂቱ ከተሰነካከለ ቆይቷል።

በተቃና ጐዳና ለመሄድ ከፈለግን አበሳችንን እየዘረዘርን ብቻ መዘግየት እጅግም አይረዳንም። ከሰፈሩ የተፈናቀለ፣ መንገድ የሳተ፣ አስተምህሮና የትምህርት ማኅበረ ሰብ ለመመለስ ቢሻ ቀዳሚውን የቃሉን ካርታ መዘርጋትና ማየት አለበት። የጠራውና የሰከነው ትምህርት የቱ ነው? በቃሉ

የተገራው የተሞላው መምህርስ ምን ዐይነት ነው? ንጹሑን ሰማያዊ መልእክት ማቅረቢያውስ መንገድ ምንድነው? ብለን መጠየቅና ትክክለኛው መሥመር ውስጥ መግባት ያለብን አሁን ነው። የአስተምህሮ ጥራት ማለትም ይሄው ነው።

## II. የአስተምህሮ ምንነት እና ሂደት

በእምነት ቤተ ሰቦች ዘንድ አስተምህሮ ማለት በአጭሩ የአማኞች የወል መሠረተ እምነት እና የኑሮ አካሄድ የሚቃኝበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብያኔ ነው።

በዚህ ጽሑፍ አስተምህሮን በተግባቦት መርሕ አቅጣጫ ለመመልከት እንሞክራለን። አስተምህሮ የመልእክት አስተላለፍን ይመለከታል፤ የመልእክት አስተላለፍ ሂደት ደግሞ መልእክት ላኪውን፣ መልእክቱን፣ መልእክተኛውን፣ መልእክት ተቀባዩን እና የመልእክት መስተላልፉን ያካትታል። በዚሁ ረገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተያያዘ መልኩ ወንጌላዊ አስተምህሮን በመጠኑ እንቃኛለን።

1. የመልእክቱ ባለቤት - መልእክት ላኪው

መልእክት ላኪው የፍጥረት ሁሉ ምንጭና ባለቤት፣ ፍጥረቱን በሥርዐት የሚመራና የሚጠብቅ፣ የሕያዋን ፍጡራኑ መጋቢ፣ የታሪክ ባለቤት፣ የጌቶች ሁሉ ጌታ፣ ጊዜያትንና ዘመናትን የሚለውጥ እርሱ ግን የማይለወጥ ነገሥታትን የሚያነሣ፣ የሚያፈልስ የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ፣ የሰው ልጆች አዳኝ የዘላለምን መንግሥት አውራሽ ነው። እርሱ የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር፣ አልፋና ኦሜጋ የዘላለም አምላክ ነው።

አብ ቃልን በሥጋ ወደ ምድር እንደላከው፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ዓለም ሁሉ ላከ፤ ይልካልም፤ እስከ ፍጻሜም አብሯቸው ይሆናል። ደቀ መዛሙርቱ በእርሱ ሆነው፣ ከእርሱ ጋር ሆነው፣ ለእርሱም ሆነው፣ ስለ እርሱ ይመሰክራሉ። የእርሱን አዳኝነትና ጌትነት በኀይልም ያውጃሉ። ሰዎችን የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው ወደ እርሱ ይጠራሉ። ጥሪውም ሕያው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ፣ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ፣ ደግሞም የመንግሥቱ ዜጋ ለመሆን እንዲበቁ፣ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲትረፈረፍላቸውም ነው።

2. መልእክተኛው

መልእክተኛው ላኪ አለው፤ ላኪውም እግዚአብሔር አምላክ ነው። እውነተኛ መልእክተኛ የሚያደርሰው የላኪውን መልእክት ነው፤ መልእክቱን ማድረስ ያለበትም በተላከበት ሰዓት፣ ወደ ተላከበት ስፍራ ወደተላከላቸው ሁሉ ነው።

መልእክተኛው መልእክቱን የማሻሻል፣ የመቀነስ ወይም የመጨመር ሙብት የለውም። ተደራስያኑንም የመቀየር ሆነ የማሳነስ ሙብት የለውም። መልእክቱ የሚተላለፍበትን ስፍራም ሆነ ጊዜ አይወስንም።

መልእክተኛው በዋናነት ደስ የሚያሰኘው ላኪውን ነው፤ ተደራስያኑን ወይም ራሱን እንዲያስደስት ወይም እንዲያዝናና አይደለም። "አሁን እኔ ጐሽ ለመባል የምሻው በሰዎች ዘንድ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ዘንድ? ወይስ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት እየተጣጣርሁ ነው? ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የምጥር ብሆን ኖሮ፣ የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንሁ ነበር" (ገላ. 1፥10)፤ "እነርሱ ዐመፀኛ ቤት ስለሆኑ፣ ቢሰሙም ባይሰሙም አንተ ቃሌን ንገራቸው" (ሕዝ. 2፥7)።

ከተደራስያኑ ተሰሚነት ቢያገኝም ባያገኝም የተላከውን ሁሉ ምንም ሳያስቀር መልእክቱን እንዳለ በትክክል የሚያስተላልፍ ነው፤ ደግሞም መልእክቱ እንዳይዛባበትና ተዛብቶ እንዳይቀርብ ጠንቅቆ የመያዝ ኀላፊነት የተጫነበት ነው። የላኪውን ሐሳብ ከራሱ ሰዋዊ ሐሳብ ወይም አስተያየት ለይቶ አስረግጦ የሚያቀርብ ነው (1ቆሮ. 7፥10-12)።

በተጨማሪም መልእክተኛው ተደራስያኑን ማክበር ይኖርበታል። መልእክቱ እንዲደርስላቸው የታሰቡትን፣ ላኪው ጌታ ራሱ አክብሯቸዋልና መልእክት ልኮላቸዋልና። መልእክተኛው ተደራስያኑን እንደ ግል ዕቃ ወደ ፈለገበት ማንከባለል ሊዳዳው አይገባም፤ ተደራስያኑን ማንገላታት ከፈቃዳቸውና ከፍላጎታቸው ውጭ 'ይህን በሉ ይህን አድርጉ' ብሎ ጫና ማሳደር አይገባውም። መልእክተኛ መሆኑ እርሱን ሊያስኮፍሰው አያስፈልግም። በተደራስያኑ ላይ ሊሠለጥንባቸው መሞከር ነውር ነው። 'አክብሩኝ'፣ 'እጠኑልኝ' ማለትም እጅግ አስጸያፊ ነው። መልእክተኛው ተደራስያኑን ሲንቅ እግዚአብሔርን ንቋል፡ 'እኔን አክብሩኝ' ሲል ደግሞ የእግዚአብሔርን ክብር ተጋፍቷል።

3. ተደራስያኑ

ተደራስያኑ በሁለት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው፤ ወደ እምነት የመጡና ገና ያልመጡ። ወደ እምነት ገና ካልመጡት ብዙ አይጠበቅም፤ ባህል ካስታጠቃቸው ወይም ከማኀበራዊ የሞራል ሥርዐት አገራር ውጪ ከእነርሱ የሚጠበቅ ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ትሩፋት ላይኖር ይችላል። አማኞች ግን እግዚአብሔርን እንዲፈሩ፣ ቃሉን እንዲወዱ፣ ለቃሉ የከበረ ስፍራ እንዲሰጡ፣ ጨዋነትን እንዲገልጡ ይጠበቃል። ከሌላ ከሌላው ይልቅ ለቃሉ ቅድሚያ እንዲሰጡ፣ ቃሉን እንዲጠሙ፣ ቃሉን እንዲያጤኑ፣ ራሳቸውን መስጠት ይኖርባቸዋል። የሚሰጠውን ስብከት ወይም አስተምህሮ በመጽሐፍ ቅዱስ መለኪያነት መለየት መመዘን ይገባቸዋል። ሁሉን እንዲፈትኑ መልካሙን እንዲይዙ ከማንኛውም ክፉ ነገር እንዲርቁ ታዘዋልና (1ተሰ. 5፥21-22)።

አንዳንዶች ወደ ጌታ የሚመጡት የሕይወት ዐላማና ትርጕም ሽተው፣ የዘላለምን ሕይወት ናፍቀው ነው። ሌሎች የኀጢአት ሸክም ከብዷቸው፣ በደል ተጭኗቸው፣ ከሸክማቸው እንዲያርፉ ከበደለኛነት ግዞት አርነት እንዲወጡ ነው። ደግሞ ሌሎች በዚህ በአጸደ ሥጋ ሕይወታቸው ማርና ወተት እንዲፈስላቸው ነው። ሌሎችም ደግሞ ሰይጣንን ጠልተው፣ እርሱ እንዳይደርስባቸው ፈልገው በምትኩ እግዚአብሔርን ሽተው ከእርሱ ዘንድ ለመሆን ናፍቀው ነው። ሌላው በሌላ በጎ ናፍቆት የመጣ ነው። ይሁን እንጂ ሁሉም እውነተኛ ደቀ መዛሙርት በመሆን የቀኑ የተቃኑ ለመሆን ይበቃሉ፤ ሕይወትን በሙላት ሊጎናጸፉ ይችላሉ።

## III. የመልእክቱ ይዘት አንኳሮች

የመልእክቱ ቅኝት በሚከተሉት ዐበይት ጕዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ሊሆን ይገባ፡-

- የቃሉ ባለ ሥልጣንነት እና ማእከልነት
- የክርስቶስ ኢየሱስ ማእከልነት፣ ሉዐላዊነትና ልዩነት

- የመስቀሉ ማእከልነት
- የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ አስቀዳሚነት እና የመንፈስ ፍሬ አስፈላጊነት
- ትምህርተ ሥላሴን አክባሪነት

1. የቃሉ ባለ ሥልጣንነት እና ማእከልነት

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ካሳደረበት ችሎታ ወይም አቅም መካከል ማስተዋለ ቃል አበጅቶ፣ ስም ሰይሞ ቋንቋ ቀምሮ መናገር ነው። በቋንቋ ዐሳብን መለዋወጥ መግባባትን ማራመድ ነው። እግዚአብሔርም በሰዎች ቋንቋ በሰዎች አማካይነት ዐሳቡን ለሰው አስተላልፏል፣ ቃሉን ሰጥቶናል፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፈውልናል። መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጕሞ ዛሬ ቀርቦልናል።

ቃሉ እውነታን ያሳየናል፤ እውነትን ያሳውቀናል፣ ማስተዋልን ያላብሰናል። መልካሙንና ክፉውን ይለይልናል፤ ስለ ፍጥረት፣ ስለ ፈጣሪ፣ ፈጣሪ ከፍጥረቱ ጋር ስላለው መስተጋብር፣ ስለ ስፍነ ተክል እና እንስሳ፣ ስለ ሰው አበጃጀት ወይም አፈጣጠር፣ ስለ ሰማይ ሠራዊት፣ ስለ መንፈሳዊ አካላት ይነግረናል፤ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ስላለው አምላካዊ ኪዳን ይተርክልናል። ሰው ከእግዚአብሔር ጋርና ሰው ከሰው ጋር ሊኖረው ስለሚገባ አኗኗር መመሪያ መመርመርያ ይሰጠናል። ስለ ውድቀት ያስረዳናል፣ ስለ ድነት መንገድ ይገልጥልናል፤ ስለ ዘላለም ሕይወትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እውነታ ያወሳልናል መግቢያ መንገዱንም ያሳየናል።

ቅዱስ ቃሉ የእምነትና የአስተምህሮ መርሕ፣ የሞራል ሕይወት መለኪያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት መሠረት፣ የመንፈሳዊ ሕይወት ምንነት፣ ዕውቀት መገብያ የትክክለኛና የጠራ አስተምህሮ ምንጭና ሚዛን፣ የፍትሐዊ አመራር ጥበብ መመንጫ፣ ለተሰጠ መሪነት ልብ መታነጫ እንዲሁም የሕያው እምነት መሠረትና መገንቢያ ነው።

እንግዲያስ ቃሉ

- የነባራዊ እውነታ መሠረት፣
- የእውነትና የሥርዐተ እምነታችን መገንቢያ
- የሥርዐተ እሤታችን መዋቀሪያ
- የልቡናችን መታደሻ፣ የአደራረጋችን፣ የአካሄዳችን፣ የአኗኗራችን መመሪያ ነው፤ በጥቅሉ የርዕዮተ ዓለማችን መታነጫ ነው።

ቃሉ እስትንፋሰ መለኮት ያደረበት በመሆኑ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡ ትእዛዛትን፣ መመሪያዎችንና መርሖዎችን የያዘ መጽሐፍ ነው። ስለሆነም ከወጋችን፣ ከልማዳችን ከዕሳቤዎቻችንና ከባህላችን ጋር ባይስማማም ፍጹም ሥልጣናዊነቱ አይሻርም።

መጽሐፍ ቅዱስ በቂ መገለጥ ነው፤ ይህም ማለት የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን ለማወቅ፤ ለድነትና ለእርሱ ክብር ለመኖር የሚያስችል የተሟላ መልእክት ያለው ነው።

ባህል፣ የግል ልምምድ (ተሞክሮ) ስሜታዊ ማንነታችን፣ የወቅቱ ሁኔታ ሁሉ በጎም ክፉም ተጽእኖ ሊያሳድሩብን ቢችሉም እነዚህ ሁሉ ለቃሉ መገዛት ለሥልጣኑም ማደር ይኖርባቸዋል።

ነገሩ እንዲህ ሆኖ እያለ ግን ዛሬ በአብዛኛው ምእመናንና አገልጋዮች ዘንድ ያለው እምነት ከቃሉ ይልቅ በልምምድና በስሜታዊነት ላይ የተመሠረተ ሆኗል። በትምህርትም ሆነ በዕለታዊው ኑሮ 'ምን ታየህ?'፣ 'ምን ተሰማህ?' ማለት እጅግ ይበዛል፣ ይዘወተራል። ከእግዚአብሔር ቃል ዳኝነት ይልቅ ተሞክሮና ልምምድ የብዙኀንም ድምፅ ይገኝናል። ለአስተምህሮ ትክክለኛነት ከተጨባጭና ከነባራዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች ይልቅ ልምምዳዊ የሆኑ ማስረጃዎች ስፍራ ይሰጣቸዋል። ቃሉን ማሰብ፣ ማጤን፣ ማስተዋልን መጥላት፣ ገሸሽ ማድረግ ይታያል። ጸረ ተምህሮት (anti-intellect) እና ጥራዝ ነጠቅ (quasi-intellect) የሆነ አቋም በእጅጉ እየተንጸባረቀ እውነትን ለማስተዋል የማሰብ ተግባር ቀስ በቀስ እየተኮላሸ፣ እንዲጨፈለቅ እየተደረገ ነው።

ዛሬ በሚያስደነግጥና በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ይህ የከበረው የአምላካችን ቃል የማይለውን 'ይላል' የሚለውን 'አይልም' ብሎ ተርጕሞ ማስተማር እጅግ እየተበራከተ መጥቷል። አንዳንዶቻችን ግልጽ ከሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ይልቅ፣ ከቀጥተኛው ትምህርት (መልእክት) በስተ ጀርባ ፈልፈልን ብለን የምናወጣውን ትርጕም እናከብራለን። ከዐውዱ ጋር ወይም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ተመርተው መጽሐፍ ቅዱስን ከጻፉት ሰዎች መልእክት ይዘት ጋር ባይጣጣምም አይገደንም። ይህ ያለንበት ጊዜ በሰዎች ምናባዊ ዓለም የተወለደ ትርጕም፣ ከእግዚአብሔር የመጣ መገለጥ እየተባለ የሚሰበክበት፣ አዳማጩም 'አሜን አሜን' እያለ ያለ ምንም ፍተሻ፣ ያለ ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛን እንዲወስድ የሚደረግበት ጊዜ ሆኗል። ከዚህም የተነሣ ብዙዎቻችን የዘመኑ ሰባኪያንና አስተማሪዎች ራሳችንን ከመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ተመርተው ከጻፉት ነቢያትና ሐዋርያት በላይ በማድረጋችን ከእውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ጋር ተጣልተናል፤ ለሐሰተኛ ትምህርት በሩን ወለል አድርገን አስከፍተናል።

ጊዜ ወስደን የእግዚአብሔርን ቃል ከማጥናት ይልቅ፣ ሁሉን ነገር መንፈስ ቅዱስ ይገልጥልኛል የሚለውን አባባል ለስንፍናችን መመከቻ እያደረግን ቃሉን ከፍተን ሳናነብ፣ ሳናጤን በመድረክ ላይ የምንቆም ብዙዎች አለን። አንዳንዶቻችን ደግሞ አንድን ጥቅስ ወይም አንድን ምንባብ ዐውዱን ባላገናዘበ ሁኔታ ዘንጥለን በማውጣት፣ የራሳችንን ፍላጎት ሐሳብና አእምሯችን የወለደውን ትርጕም መደገፊያ፣ እንደ መዋኛ ስፍራ መወናጨፊያ ማማ አድርገን እንጠቀምበታለን። ያነበብነውን ክፍል ገልጦ ማብራራት ይቅርና ዳግመኛ ወደ ክፍሉ ሳንመለስ እንዳሻን ጋልበን እንደ ወጣን እንቀራለን።

ለዚህ ዐይነት ፈሩን ለለቀቀና የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጕም አዛብቶ ለመስበክና ለማስተማር የዳረገን አንደኛው ምክንያት ሰባኪዎችና አስተማሪዎች የሆንነው የመጽሐፍ ቅዱስን ምንነት በአግባቡ ረጋ ብለን ያለመረዳትና እንዴት አድርገን በትክክለኛው መንገድ መተርጐም እንዳለብን ያለማወቅ

ወይም ያለመፈለግ ነው። እግዚአብሔር የማዳን ታሪኩን የሰዎችን ባህልና ቋንቋም ተጠቅሞ ስለ ገለጠው መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና የቋንቋ፣ የታሪክ፣ የመልክዓ ምድራዊና ባህላዊ ዳራውን እንዲሁም ሥነ ጽሑፋዊ ዐውዱን፣ ሥነ ቃላቱንና ሰዋሰዉን ባስተዋለ ሁኔታ ልንተረጕመው ይገባል፤ የጽሑፉን ጾታና የአነጋገር ዘይቤውንም ልናጤን ያስፈልጋል። ዛሬ ብዙዎቻችንን የሥነ መለኮት ትምህርት ወይም የሥነ አፈታት ትምህርት ባንማርም፣ በቀላሉ የአስተውሎት ሕግ (common sense) ብቻ በቀጥተኛ ሁኔታ ሊተረጐሙ የሚችሉትን ክፍሎች እንኳ አዛብተን እንገዳ ትርጒም ስንስጥ እንገኛለን።

በኤፌሶን 6 ላይ እንደ ተጻፈው የመንፈስ ሰይፍ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነውና ሁለቱን ማለትም መንፈሱንና ቃሉን ማፋታት የማይገባና ለስሕተት የሚዳርግ ነው። እኛን የሞላ/የሚሞላ መንፈስ ቅዱስ፣ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው/የደረሰው ያው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ዘወትር አበክረን ማስተዋል አለብን። 'ጌታ ተናገረኝ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው የሚያን ቀሳቅሰኝ' እያልን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚሰጠን መመሪያ ውጭ ብንመላለስ ልምምዳችን በጥያቄ ውስጥ ይወድቃል እንጂ ቃሉ አይወድቅም። ልምምዳችን ከመንፈስ ቅዱስ ከሆነ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማል፤ አለበለዚያ ልምምዳችን ከራሳችን ስሜት ወይም ከክፉ አስመሳይ መንፈስ ወይም የሆነ ጥቅምን በመፈለግ ከሽንገላ ወይም ከአእምሮ ጤና ቀውስ ወይም ከዕውቀት ማነስ ሆኖ ይገኛል፤ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ራሱን አይቃረንምና።

"... እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሠከረለት ሠራተኛ፣ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።" (2ጢሞ. 2፥15፡-)

"የመዳንን ራስ ቍር አድርጉ፤ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።" (ኤፌ. 6፥17)

የእውነት መንፈስ የሆነው፣ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራው መንፈስ ቅዱስ የቃሉ ደራሲ ነው። ስለሆነም ቃሉ የሕይወት፣ የእምነት፣ የአስተምህሮና የአምልኮ ማእከል መሆኑ በሁሉ ሁኔታ መረጋገጥ አለበት።

2. የክርስቶስ ኢየሱስ ማእከልነት፣ ሉዐላዊነትና ልይትነት (**Uniqueness**)

ጊዜና ስፍራ ምጡቅ የሆነው ቃል የፍጥረት ሁሉ ምንጭ ነው፤ ሁሉ ነገር በእርሱ ሆኗልና፤ ያለ እርሱ የሆነ ወይም የተፈጠረ አንዳች የለም። "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ" (ዮሐ. 1፥1-3)። ሁሉንም መፍጠር ማበጀት ብቻ ሳይሆን ሁሉም የሚንቀሳቀሰው ሁሉም ተያይዞ ያለውና የሚኖረው በእርሱ ነው፤ እርሱ የሚመስለው የሚስተካከለው የሌለ አሃዜ ኵሉ ነው።

"ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሯ፤ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለ ሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሯል። እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው (ቈላ. 1፥16-17)። እርሱ የእውነታ ሁሉ ሙላት የሕልውና ሰበብ ነው።

ደግሞም በሰማይና በምድር በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ መካከለኛ ነው። ፍጥረት ከፈጣሪው ጋር መታረቂያው በእርሱ ነው። የተሰወረው እግዚአብሔር የተገለጠው በእርሱ ነው፣ ፍጹም መለኮትነቱ የተንጸባረቀው በእርሱ ነው፤ እርሱ የድነት መሠረት የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው።

አዲሱ ማኅበረ ሰብ የተመሠረተው በእርሱ ነው። የሚኖረውና የሚገዛውም በእርሱ ነው፤ እርሱ ሁሉ በሁሉ የሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሠረትና ራስ ሁለንተናዋንም የሚሞላ ነው። በፍጻሜውም ሁሉ የሚጠቃለለው በእርሱ ነው፤ ኀይላትና ሥልጣናት ሁሉ ጸጥ ለጥ ብለው ተደፍተው የሚገዙት ለእርሱ ነው። እርሱ የፍጥረት ሁሉ ዳኛ፣ የታሪክ ሁሉ ጌታ ነው። ነቢያት ከሩቅ ሆነው ስለ መሲሑ መምጣት ተነበዩ፣ ቃል ሥጋ መሆኑን፣ መወለዱን መላእክት አበሰሩ። በእርሱ ደስ የሚሰኝበት፣ የሚወደው ልጁ መሆኑን እግዚአብሔር ከሰማይ ተናገረ። ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ኅብረት የጠራንም እግዚአብሔር ነው። እኛም መስበክ ያለብን ሁሉ በሁሉ የሆነውን ክርስቶስ ኢየሱስን ብቻ ነው። "በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኗል።" (1ቆሮ. 1፥30)።

3. የመስቀሉ ማእከልነት

የቃል ሥጋ መሆንና በመካከላችን ማደሩ ያነጣጠረው መስቀሉና የመስቀሉ ክስተት ላይ ነበር። "ልጆቹ በሥጋና በደም እንደሚካፈሉ እርሱ ራሱ ደግሞ ያንኑ ተካፈለ፤ ይኸውም በሞት ላይ ኀይል ያለውን ዲያብሎስን በሞቱ ኀይል እንዲደመስስ ነው። እንዲሁም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በሞት ፍርሀት የታሰሩትን ነጻ እንዲያወጣ ነው" (ዕብ. 2፥14-15)።

ሐዋርያቱ የመስቀል መሥዋዕትነቱን የድነታችን መሠረት መሆኑን በይፋ አጠንክረው ዐውጀዋል። በራእይ መጽሐፍም እንደምንመለከተው አራቱ ሕያዋን ፍጡራን፣ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ለታረደው በግ ቅኔ ተቀኝተው፣ ተደፍተው መስገዳቸው የመስቀሉን ሥራ ክቡርነት ከፍ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

> እንዲህም እያሉ አዲስ መዝሙር ዘመሩ፤
> "መጽሐፉን ልትወስድ፣
> ማኅተሞቹንም ልትፈታ ይገባሃል፤
> ምክንያቱም ታርደሃል፤
> በደምህም ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋ ሁሉ፣
> ከወገን ሁሉ፣ ከሕዝብ ሁሉ

ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃል።
ለአምላካችንም መንግሥትና ካህናት አድርገሃቸዋል፤
እነርሱም በምድር ላይ ይነግሣሉ።"
በታላቅ ድምፅም እንዲህ ብለው ዘመሩ፤
"የታረደው በግ ኀይልና ባለ ጠግነት፣ ጥበብና ብርታት፣
ክብርና ሞገስ፣ ምስጋናም ሊቀበል ይገባዋል።" (ራእ. 5፥9፡10፡12)

መስቀል የሰውን ስቃይ እግዚአብሔር አምላክ የተካፈለበት፣ "አንተ የሥጋ ዐይን አለህን?" የሚለው የኢዮብ ጥያቄ ፍንትው ያለ ምላሽ ያገኘበት፤ ስቃይ ለእግዚአብሔር ባዕድ አለመሆኑ የተመሰከረበት፣ 'የእግዚአብሔር ፍቅር ስፋቱ፣ ከፍታው፣ ጥልቀቱ ከመታወቅ ያለፈ ነው' የሚለው በገሃድ የተገለጠበት ታሪካዊ እውነታ ነው። የመለኮት ጥምር ባሕርያት በአንድ ሁኔታ የተገለጠበት፣ ማለትም ምሕረቱና ፍርዱ፣ ሰው አፍቃሪነቱ እና ኀጢአት ጠልነቱ የታየበት፣ ጥበቡ የተንጸባረቀበት፣ ሞትና ሕይወት የተገናኙበት፣ ሽንፈትና ድል የተራከቡበት፣ ውርደትና ክብር፣ መፍረስና መታነጽ የተተካኩበት ነው።

ትላንት እና ነገ የተሸረቡበት፣ ምድርና ሰማይ የተጋጠሙበት፣ ሰማይ የተከፈተበት፣ "ምድር" ወደ "ሰማይ የወጣበት"፣ "ሰማይ" ወደ "ምድር" የወረደበት፣ የጥል ግድግዳ የፈረሰበት የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነው የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ነው።

ከአምልኮተ ባዕድ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ዘወር የሚባልበት፣ ከአምላክ ጠልነት ወደ አምላክ ቤተ ሰብነት፣ ከጨለማው አገዛዝ ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር፣ ወደ ሰማያዊ ዜግነት መፍለስ የተቻለበት ነው። ለክህነት፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ዜግነትና ለእግዚአብሔር ልጅነት የበቃንበት ክስተት ነው።

በመስቀሉ ላይ የፈሰሰው ደም የኀጢአትና የበደል ስርየት መቀበያ፣ ጽድቅን መታደያ፣ ከሕግ ርግማንና ከከንቱ ኑሮ መዋጃ፣ በኀጢአት ጉልበት፣ በሞት ኀይልና በጨለማው ሥርዐት ላይ ድል መጎናጸፊያ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቂያ ነው። መስቀሉ የወንጌል እምብርት ነው፤ የመስቀሉም መንገድ የኑሯችን መርሕና ዘይቤ ነው፤ ማለትም በመስጠት ማግኘት የሚስተናገድበት፣ ከሁሉ ኋላ በመሆን ፊተኛ የሚኮንበት፣ በድካም ብርታት የሚታፈስበት፣ በውርደት ክብር የሚለበስበት ጣይ አንሽ (paradoxical) ቅኝት ነው።

1ቆሮ. 1፥22-23 "መቼም አይሁድ ታምራዊ ምልክትን ይፈልጋሉ፤ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፤ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን"

ገላ. 3፥1 "እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ ለመሆኑ ማን መተት አደረገባችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ በፊት ለፊታችሁ በግልጥ ተሥሎ ነበር"

ሰይጣን ቀደም ሲል ኢየሱስ ወደ መስቀሉ እንዳይወጣ ሲከላከል ቆየ፤ 'ወድቀህ ብትሰግድልኝ' አለው፤ ይህ አልሳካለት ሲል አሁን ደግሞ አማኞች ትኩረታቸው በመስቀል ላይ እንዳይሆን የተሰቀለው ክርስቶስ ከዐይናቸው እንዲሰወር በመጣር ላይ መሆኑን ልብ ልንል ይገባናል።

4. የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ አስቀዳሚነት እንዲሁም የመንፈስ ፍሬ አስፈላጊነት

መንግሥት ስንል ሉዓላዊነትን፣ ግዛትን፣ አገዛዝን፣ ሕግን፣ ዳኝነትን ያመለክታል። የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በፈጣሪነቱ፣ በአጎዜ ኵሉ አምላክነቱ ሁሉን የሚገዛበት ነው። ለችሎቱ ወሰን የሌለው በተፈጥሮና በታሪክ ሁሉ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው አምላክ ነው (ኢሳ. 45፥9-19፤ ሮሜ 18፥39)። ሰዎችንም ወደዚህ መንግሥት የሚያፈልሰው እርሱ ነው። ቃሉ እንደሚለው፣ *"እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፥ ቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን።"* (ቈላ. 1፥13-14)።

ሰዎች የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሽ የሚሆኑት ክርስቶስ ኢየሱስ በፈጸመው *ሥራ* ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመጣ *"የእግዚአብሔርን መንግሥት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ"* እያለ የመንግሥቱን ወንጌል ሰበከ (ማር. 1፥14)። ክርስቶስ ወደ ምድር በመምጣቱ እንዲሁም በሞቱና በትንሣኤው በዚች የጠፉች ዓለም የተገለጠ ገዥነቱን አምነው በመቀበል ሰዎች የመንግሥቱ ወራሽ ይሆናሉ። አልፎ ተርፎም የእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም መምጣት ክፉውን የጨለማ አገዛዝ በማስወገድ በሙላት የሚገለጥ የዘላለም ሕይወት፣ የዘላለም ክብር መንግሥት ነው። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ነው። ይህም መንግሥት የገባንበትና ገና የምንገባበት፣ የመጣ እና ገና የሚመጣ፣ ያየነው እና ገና የምናየው እንዲሁም ያዳነን እና የሚያድነን መንግሥት ነው።

የመንግሥቱ ትሩፋት የሆነው የመንፈስ ፍሬ መታየት ታላቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። የጸጋ ስጦታዎችንም የምንናፍቅ፣ የመንፈስንም ፍሬ (ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋሐት፣ ራስን መግዛት) አጥብቀን የምንሻ ልንሆን ይገባናል። እንዲያውም የመንፈስ ፍሬ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ መታየቱ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ነው። ስጦታው ያው ራሱ ባለቤቱ መንፈስ ቅዱስ እያካፈለ የሚያድለው ነው፤ ለግለ ሰቦች ይሰጣል፤ ግን ለጋራ ጥቅም ይውላል (መዋል አለበት)፤ ማለትም በአግባብና በሥርዐት በአገልግሎት ላይ ስናውለው ጠቀሜታው በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር መላ ማኅበር መታነጽ ይሆናል። በአማኞች ዘንድ የመንፈስ ፍሬ መታየቱ ከመነመነ፣ በኅብረት ተስማምቶ መኖር፣ ተያይዞ በኅብረት ማገልገል፣ ይቅር መባባል፣ አንዱ የሌላውን ሸክም መጋራት የውሃ ሽታ ይሆናል፤ ራስ ወዳድነት ሥጋዊነት ይናኛል። የመንፈስ ቅዱስን የጸጋ ስጦታዎች ያለአግባብ ማዋል ይመጣል።

ልብ ልንል የሚገባው የጸጋ ስጦታ የታደለ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱም የበሰለ ነው ማለት አይቻልም። የጸጋ ስጦታ የተቀበልን አማኞች በመንፈስ ፍሬ እንድንበለጽግ መትጋት ይኖርብናል። ያን ጊዜ ነው በእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎቱ ከፍተኛ ውጤት የሚያ መጣው።

ፍቅር የመንፈስ ፍሬ ነው። ጳውሎስ በመልእክቱ 1ቆሮ. 13፥1-2 ላይ "በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሿሿ ጸናጽል ነኝ። የትንቢት ስጦታ ቢኖረኝ፣ ምስጢርን ሁሉና ዕውቀትን ሁሉ ባውቅ፣ ተራራንም ከቦታው የሚነቅል እምነት ቢኖረኝ፣ ፍቅር

ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ" ሲል፣ የምንረዳው ምንም ያህል የኀይል መገለጥ፣ የዕውቀት መፈልቀቅ ቢኖር የመንፈስ ፍሬ ካልታየበት የእግዚአብሔር ሰው መሆንን እንደማያመለክት ነው።

መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ወይም የጸጋ ስጦታዎች መገለጥ ከመንፈስ ፍሬ መታየት ለይቶ ማራመድ ስሕተት ነው፤ የኀይል ወይም የተሰወረ ዕውቀት መገለጥ ከሌላ ሊሆን ይችላል፤ ስለሆነም መፈተን ያስፈልጋዋል። በመንፈሳዊ እንቅስቃሴ መሪዎች ዘንድ የመንፈስ ፍሬ መታየቱ ከንውኑ ከሥጋ ወይም ከጨለማ አሠራር ውጭ መሆን አለመሆኑን ልናውቅ ከምንችልባቸው መለኪያዎች አንዱና ዐይነተኛው ነው።

ጌታ ኢየሱስ የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡብን በውስጣቸው ግን ነጣቂ ተኲላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት እንድንጠነቀቅ በማቴ. 7፥15-16 ሲያሳስበን፣ አሳሳች መሆናቸውን የምናውቅበት መንገድ ከፍሬያቸው (ከሕይወት ፍሬያቸው) መሆኑን ገልጾልናል። የሕይወት ፍሬያቸው፣ ይኸውም የመንፈስ ፍሬ በሕይወታቸው መታየት አለመታየቱ ዋና መለኪያ መሆኑን ያስገነዝበናል፤ ስለሆነም ከመንፈስ ፍሬ የራቀን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ አራማጅ መምህራንን መሸሽ ይገባናል።

5. የትምህርተ ሥላሴ አከባሪነት

የትምህርተ ሥላሴ አስተምህሮ በአንዳንድ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በጠለቀ መንገድ የነገረ መለኮት ጥናት ለማድረግ ለሚነሡ በኮርስ ደረጃ መሰጠቱ እየተበረታታ በአዳዲስ አማኞች ሥርዐተ ትምህርት ውስጥ ግን የመካተቱ ፋይዳ እምብዛም እንደ ሆነ ወይም 'ላይገባ ቸው ይችላል' የሚል ፍርሃትን ተላብሶ እየተገፋ ይስተዋላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሥሉሳዊነት እንጂ አሃዳዊ አስተምህሮም ሆነ ልምምድ በተግባር እየተገለጠ ባለመሆኑ እያንዳንዱ አማኝ ፍቅሩ ወዳየለበት የሥላሴ አካል የአምልኮም ሆነ ገንጣላ የስም አጠራር ትኩረት ይስተዋልበታል። ስለዚህም አንዳንዶች "ኢየሱሳውያን" ስንሆን፣ ሌሎቻችን ደግሞ "መንፈስ ቅዱሳውያን" በጣም ጥቂቶች ደግሞ "አብአውያን" ያደረገ አስተምህሮ እና ልምምድ ይስተዋላል። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሥሉስ አሃዱ አምላክ ትምህርት ለሕዝባችን በአግባቡ ለማስተማር አለመቻል፣ በአገልጋዮችም ዘንድ እንኳ ተገቢው ግንዛቤ አለመኖር በስፋት ይታያል።

## IV. የመልእክተኞቹና የተደራስያኑ የዛሬ ሁኔታ

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ትምህርት መሠረት የሕይወት ትልቁ ዓላማ የእግዚአብሔር ክብር ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው በኋላም ከውድቀቱ በክርስቶስ ሲዋጀው እርሱን እንዲያከብር ነው (1 ቆሮ. 10፥31፤ ሮሜ 11፥36፤ ኤፌ. 1፥3-14)። ከዚህም በመነሣት ስለ አገልግሎት ስናስብ የአገልግሎት ዓላማ እግዚአብሔርን ማከበር ሕዝቡን ማነጽ ነው።

በአንዳንድ ስፍራ በጸጋ ስጦታዎች ስም የሚታየው ውዥንብር ትኩረትን የሚጠይቅ ሆኗል። መንፈሳዊ ልምምድ ከሚሰፈር፣ ከሚለካ ነባራዊ እውነታ ክልል ወይም አጥር ውጭ ስለሆነ አንዳንዶቻችን በመዛኝ የለነት እንዳሻን ልንልበትና ልናደርግበት፣ ከፈር የወጣንበት፣ በማን አለብኝ አስተሳሰብ የምንለቀቅበት ሜዳ፣ የምንቦርቅበት መድረክ መስሏል።

እውነተኛውን የመንፈስን እሳት እንዳናዳፍን፣ ትንቢትንም እንዳንንቅ እንጂ ሁሉንም ነገር እንድንፈትንና መልካም የሆነውን እንድንይዝ፣ ከማናቸውም ዐይነት ክፉ ነገር እንድንርቅ ታዘናል።

ከመንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ከገዛ መንፈሳችን እንደ ምኞታችን እና እንደ ስሜታችን 'እንዲህ አለኝ'፣ 'እንዲህ ተናገረኝ'፣ 'እንዲህ ታየኝ'፣ ስለዚህ 'እንዲህ በሉ'፣ 'እንዲህ አድርጉ' ብለን ትእዛዝ የምንሰጥበት በዙሪያችን ላሉ እንደየሁኔታቸው (እንደየምኞታቸው) እያስተያየን የመከናወንን ተስፋ የምናርከፈክፍበትና በምላሹ ታላቅነትን፣ ተቀባይነትን፣ አጀብን፣ የጥቅም መጋበስን የምንጠብቅበት መስተጋብር፣ የሥነ ተረት ስንክሳር ሆኗል።

እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢያት እንደ ነበሩ ሁሉ የበዙ ሐሰተኛ ነቢያትም ነበሩ። እውነተኛ ነቢያት ስለ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ያስተላለፉትን መልእክት እናጢን።

> ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ አንዳች ነገር ሳያዩ የራሳቸውን መንፈስ ለሚከተሉ ሞኞች ነቢያት ወዮላቸው! እስራኤል ሆይ፤ ነቢያትሽ በፍርስራሽ መካከል እንደሚኖሩ ቀበሮዎች ናቸው። ... ራእያቸው ሐሰት፣ ትንቢታቸው ውሸት ነው፣ እግዚአብሔር ሳይልካቸው፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ይላሉ፤ ይህም ሆኖ የተናገሩት ይፈጸማል ብለው ይጠብቃሉ። እኔ ሳልናገር፣ እግዚአብሔር እንዲህ ይላሉ ስትሉ ሐሰተኛ ራእይ ማየታችሁ፣ ውሸተኛስ ትንቢት መናገራችሁ አይደለምን? (ሕዝ. 13፥3፡4፡6፡7)
>
> አሁንም የሰው ልጅ ሆይ፤ ከራሳቸው አመንጭተው ትንቢት ወደሚናገሩ ወደ ሕዝብህ ሴቶች ልጆች ፊትህን መልስ፤ ትንቢትም ተናገርባቸው፤ ... በውኑ የሕዝቤን ነፍስ እያጠመዳችሁ የራሳችሁን ነፍስ ታድናላችሁን? ዕፍኝ ለማይሞላ ገብስና ለቍራሽ እንጀራ ስትሉ ሐሰትን የሚያደምጥ ሕዝቤን እየዋሻችሁ መሞት የማይገባውን በመግደል፣ መኖር የማይገባውንም በማትረፍ በሕዝቤ መካከል አርክሳችሁኛል።" (ሕዝ. 13፥17-19)
>
> የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እነዚህ ነቢያት የሚተነብዩላችሁን አትስሙ፤ በባዶ ተስፋ ይሞላችኋል፤ ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የሆነውን ራእይ ይናገራሉ። እኔን ለሚንቁኝ እግዚአብሔር ሰላም ይሆንላችኋል ብሏል ይላሉ፤ የልባቸውን እልኸኝነት ለሚከተሉም ሁሉ፣ ክፉ ነገር አይነካችሁም ይሏቸዋል።
>
> እኔ እነዚህን ነቢያት አልላክኋቸውም፤ እነርሱ ግን ለራሳቸው መልእክታቸውን ይዘው ሮጡ፣ ሳልናገራቸውም ትንቢት ተናገሩ።
>
> 'ሕልም አለምሁ! ሕልም አለምሁ!' እያሉ በስሜ የሐሰት ትንቢት የሚናገሩትን የነቢያትን ቃል ሰምቻለሁ፤ ይህ ነገር፣ የገዛ ልባቸውን ሽንገላ በሚተነብዩ በሐሰተኞች ነቢያት ልብ ውስጥ የሚቈየው እስከ መቼ ነው? አባቶቻቸው በኣልን በማምለክ ስሜን እንደረሱ፣ እነርሱ በሚነጋገሩት

ሕልም፣ ሕዝቤ ስሜን እንዲረሳ ያደረጉ ይመስላቸዋል። ሕልመኛ ነቢይ ሕልሙን ያውራ፤ "ቃሌ ያለው ግን በታማኝነት ይናገር፤ ገለባና እህል ምን አንድ አድርጎአቸው!" ይላል እግዚአብሔር። "ቃሌ እንደ እሳት፣ ድንጋይንም እንደሚያደቅ መዶሻ አይደለምን?" ይላል እግዚአብሔር።

"አፈ ጮሌነታቸውን በመጠቀም፣ 'እግዚአብሔር እንዲህ ይላል' የሚሉትን ነቢያት እቃወማለሁ" ይላል እግዚአብሔር፤ "እነሆ፤ ሐሰተኛ ሕልም ተመርኵዘው ትንቢት የሚናገሩን ነቢያት እቃወማለሁ" ይላል እግዚአብሔር፤ "እኔ ሳልልካቸው ወይም ሳልሾማቸው ደፍረው ውሸት ይናገራሉ፤ ሕዝቤንም ያስታሉ፤ ለዚህም ሕዝብ አንዳች አይረቡትም" ይላል እግዚአብሔር (ኤር. 23፥16-17፣ 21፡25-32)።

... ራሳቸውን ብቻ የሚመግቡ እረኞች
በነፋስ የሚነግዱ ዝናብ የሌላቸው ደመናዎች
በመከር ወራት ፍሬ የማይገኝባቸው ከሥራቸው
ተነቅለው ሁለት ጊዜ የሞቱ ዛፎች
የነውራቸውን አረፋ የሚደፍቁ
የተቈጡ የባሕር ማዕበል ተንከራታች ከዋክብት ናቸው (ይሁ. 12-13)

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"ሕዝቤን የሚያስቱ ነቢያት፤
ሰው ሲያበላቸው፣ 'ሰላም አለ' ይላሉ፤
ሳያበላቸው ሲቀር ግን፣
ጦርነት ሊያውጁበት ይነሣሉ።
ስለዚህ ሌሊቱ ያለ ራእይ፣
ጨለማውም ያለ ነግርት ይመጣባችኋል፤
በነቢያት ላይ ፀሓይ ትጠልቅባቸዋለች፤
ቀኑም ይጨልምባቸዋል።
ባለ ራእዮች ያፍራሉ፤
ንግርተኞችም ይዋረዳሉ፤
ሁሉም ፊታቸውን ይሸፍናሉ፤
ከእግዚአብሔር መልስ የለምና። (ሚክ. 3፥5-7)

እኛኮ ትርፍ ለማግኘት ብለን የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር እንደተላኩ ሰዎች በክርስቶስ ሆነን በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን። (2ቆሮ. 2፥17)

የዛሬ ተደራስያን

የዛሬውን ተደራሲ (አድማጭ፣ አንባቢ፣ ተመልካች) በሌላ አንጻር ስናየው ከዚህ የሚከተሉት ገጽታዎች ይታዩበታል፡-

1. ተመሳሳይነት

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞችን የተለየ የሚያደርገን ነገር ቢኖር ተመሳሳይነታችን ነው። ምንም እንኳ እንደ ሌሎቹ አገሮች አብያተ ክርስቲያናት በቤተ እምነት ስም የተከፋፈልን ብንሆንም በእምነት አገላለጽና በልምምድ እጅግ ተመሳሳይ ነን ቢባል ማጋነን አይሆንም። መመሳሰሉ የተፈጠረው አንዱ ሌላውን ለመምሰል ባደረገው ጥረት ሳይሆን በንጉሡ፣ በተለይም በደርግ ዘመን በነበረው ስደት ሳቢያ የተፈጠረ ነው፤ ምንም እንኳ ይህ ከበጎ አቅጣጫ ሊወሳ የሚገባው መልካም ገጽታ ቢሆንም በውስጡ ያዘላቸው ተያይዞ መነዳት፣ ሕፀፆችና እያደር ያመጣቸው አሳሳቢ ቀውሶች ተነቅሰው ሊወጡ፣ በአግባቡም ሊታረሙ ይገባል።

2. ቤተ ክርስቲያን መራጭነት

የቤተ ክርስቲያን አባልነት የቤተ ሰብ አባል መሆኑ ቀርቶ ሱቅ እንደ ማማረጥ ሆኗል። ከፍተኛ ቍጥር ያላቸው አማኞች ባመኑበት ቤተ ክርስቲያን አባል አይደሉም። አባል መሆን ቢያስቡም እንኳ ከመወሰናቸው በፊት በምርጫ ሰንጠረዣቸው ውስጥ የገቡትን ቤተ ክርስቲያናት ዞረው ይቃኛሉ (ዊንዶ ሾፒንግ እንደሚባለው ዐይነት መሆኑ ነው)። በአብዛኛው ምርጫው የሚመሠረተው በሚገኝበት ስፍራ አመቺነት፣ በአባላቱ ገጽታ፣ በፓስተሩ ስጦታ፣ በመቀመጫው ምቾት፣ በድምፅ ሥርዐቱ ፍሰት፣ በሚጋበዙት ተናጋሪ እንግዶች ላይ በማተኮር ነው። ታዲያ በእነዚህ መስፈርቶች የተመረጠ ቤተ ክርስቲያን ጥቂት ቆይቶ ከተዘረዘሩት መኻል አንዳንዶቹ ቢጎድሉ አባሉ ሌላ ማማረጥ ይቀጥላል። አንድ ወቅት ሰው ሞልቶ ያየነውን ቤተ ክርስቲያን በሌላ ጊዜ ተራቁቶ ቢታይ አስደናቂ አይሆንም።

ከዚህ የተነሣ፣ ገበያተኛው አማኝ እንዳይርቅ "ሸማቹ ንጉሥ ነው" የሚለውን የምዕራቡን የንግድ ዓለም መፈክር በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ማስተናገድ ለብዙዎች ግድ ሆኖባቸዋል። ስለሆነም ዛሬ ታዳሚዎቻቸውን ለማስደሰትና ለማቆየት የቤተ ክርስቲያኒቱም ገቢ እንዳይቀንስ ለማድረግ እውነተኛውን መልእክት ከማስተላለፍ፣ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማር ይልቅ የሰሚዎችን ጆሮ የሚያከላቸውን ስብከትና ትምህርት ማስተላለፍ ደርቷል። ይህ እንግዳና አፍራሽ ልምምድ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊታረምና ፈጥኖም ሊገታ ይገባል። ዛሬም ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚደረግ የምእመናን ፍልሰት በመንገድ የሚጠፋው ቍጥር ቀላል አይደለም።

3. ስለ አገልጋዩ ባሕርይ ወይም የሕይወት ጤናማ አቋም ግዴለሽነት

በቤተ ክርስቲያን አሁን አሁን እየተስተዋለ ያለው ባሕርይ ስለ ጽድቅ እና ስለ ቅድስና ያለ ግዴለሽነት ነው። አገልጋይ የተባለው "“ጸጋ” እስካለው ድረስ፣ እግዚአብሔር እስከተጠቀመበት ድረስ፣ እኔ ከአገልግሎቱ እስካተረፍኩ ድረስ፣ ስለ ባሕርዩው፣ ስለ ቅድስና ሕይወቱ፣ ስለ ግንኙ ነቱ፣ ስለ ትዳሩ አያገባኝም፤ ይህ የእርሱ ወይም የእርሷ የግል ሕይወት ጉዳይ ነው፣ እግዚአብሔር ይጠይቀው፤ “የተቀቡትን አትንኩ” ተብሎ ተጽፏል! ደግሞም ማካበድ አያስፈልግም’ ወዘተ. የምንል ታዳሚዎች በርክተናል። ነገሩ እንዲህ ከሆነ ብያኔ ሰጭዎች እኛም ከአገልጋዩ ጋር በአንድ ጀልባ ውስጥ እየቀዘፍን ሳይሆን አይቀርም ያሰኛል። “ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ” የተባለው የጌታ ኢየሱስ ማስጠንቀቂያ ሰሚ አላገኘም ማለት ነው።

ይህ ግዴለሽነት አንድ የሚያመለክተው ነገር አለ፤ ያም የእኛን የግብረ ገብ፣ የሥነ ምግባር፣ የቅድስና የብቃት ደረጃ ማሽቆልቆል ነው። በቅድስና የማይኖር ሕዝብ መሪው በቅድስና ወደቀ ሲባል ጥያቄ ማንሣት በራሱ ላይ ጭምር ጥያቄ ማንሣት ስለሚሆንበት ከመማለድ ይልቅ ‘ያው እርሱም ቢሆን እንደ እኔው ሰው ነው፣ ሥጋ ለባሽ ነው’ በሚል ዝምታን ይመርጣል። ‘ደግሞም እስቲ ተመልከቱ የግል ሕይወቱ ይህንና ያንን ቢመስልም እግዚአብሔር አሁንም እየተጠቀመበት ነው፤ ታዲያ እግዚአብሔር የተቀበለውን እኔ ምን አገባኝ!’ እንላለን። ‘ዋናው ነገር መድረክ ላይ “ጥሩ” መስሎ ከታየን፣ እኔም “ከተባረኩኝ” ምን እፈልጋለሁ?’ የሚል አባዜ ተጠናውቶናል። ታዲያ ይህ የግዴለሽነት አውሬ እያደፈጠና እያደባ ውስጥ ውስጡን ተሽሎክልኮ ቀረጣጥፎ እንዳይጨርሰን ያሰጋል።

ቤተ ክርስቲያን ድኅረ ዘመናዊነት ተጠናውቷት የሞራል መለኪያዋን ብትሰባብርና መለኪያ አልባ፣ ሁሉም እንደየመንገዱ ደስ እንዳለው፤ አለል ዘለል፣ ቦለል ፎለል ይበል ብትል የእውነት ዐምድና መሠረት መሆኗ ቀርቶ የዓለም ገደል ማሚቶ፣ የዓለም ጽዋ ማኅበርተኛ ሆነች ማለት ነው።

በዚያ ቀን ብዙዎች ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? አጋንንት አላወጣንምን? በስምህ ብዙ ታምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። በዚያ ጊዜ፣ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ክፉዎች፣ ከእኔ ራቁ! ብዬ በግልጽ እነግራችኋለሁ። (ማቴ 7፥22-23)

4. ለትምህርት ግዴለሽነት

ሌላው የግዴለሽነት አባዜ ትምህርትን ይመለከታል። የዘመናችን አያሌ ታዳሚዎች ከመድረክ ተዋንያኑን ማየት መስማትም የምንፈልገው ለምኞታችን ተስማሚ ጆሮን አካኪ፣ በውስጣችን ላለው ዓለመኛነት የሚመች ቅኝትን እንጂ ለመስቀሉ ቃል፣ በተለይም ለመስቀሉ መንገድ ደንታ የለንም። ከእኛ ብዙዎቻችን ዋጋ መክፈልን የሚጠይቅ የጽድቅ ወይም የ“ተመለሱ” ጥሪን በኤርምያስ ዘመን እንደ ነበሩት የይሁዳ ሕዝቦች ፈጽሞ መስማት አንፈልግም፤ ነገር ግን እንዴት “እንደምንጥስ” እና “እንደምንጠረምስ”፣ “እንደምንበርም” የማያቋርጥ ተስፋ እንዲነገረን እንሻለን። ጸጋ ነጻ ቢሆንም ተራ፣ ርካሽ ይመስል ጸጋን እየዘመርንና ተራ ሕይወት እንድንመራ የሚያነሣሣንን ትምህርት እንደሚያሰክር መጠጥ እንጨልጣለን። የተቀደሰ መንፈስ አልባ በሆነ የሥጋ ድምፅ ሥርዐት በሥነ ልቦናዊ ረቂቅ ስልት፣ በገበያ መር ዘዴ፣ ከቅዱስ ቃሉ በፈለቀ ብርሃን ሳይሆን እንደ ሸቀጥ ከውጭ በተጋዘ የሰዎች ሥጋዊ ትምህርትና ጩኸት ጆሯችን ከተጠቀጠቀ፣ ልቡናችን ከተደፈነ፣ መንፈሳችንም ከፈዘዘ በክርስቶስ ያለውን እውነት ለመስማት ይሳነናል። ከዚህ የተነሣ፣ እውነትን የሚናገሩ ጥቂቶች በእግዚአብሔር ቤት በታማኝነት መድረክ ቆመው ቢናገሩ በባዕዳን አደባባይ እንደሚናገር ሰው ቃላቸው ነጥሮ ይመለሳል። ልባችን ለስላቅና ለስሜት ቀስቃሽ ንግግሮች ብቻ ወለል ብሎ ሲከፈት ለእውነትና ለጽድቅ ቃል በራችን ጥርቅም ተደርጎ ይዘጋል።

## V. ሙዚቃ እና መዝሙር

መልእክትንና አስተምህሮን ኪነ ጥበባዊ አቅል ሰጥቶ በዜማና በሙዚቃ አቀናብሮ ለሰሚዎች ማድረስ የቆየ የእግዚአብሔር ሕዝብ ልማድ ነው። የአምልኮአችንም ዐይነተኛ ክፍል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ “ለእግዚአብሔር ከልባችሁ ተቀኙ” እንደሚል ሁሉ “በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ” ይላል። እንግዲያው መልካም መዝሙር ምስጋና ውዳሴ ማቅረቢያ፣ የሚያንጽ መልእክት ማስተላለፊያ፣ የወንጌልንም ተስፋ ማወጃ ነው።

ባንጻሩ ሙዚቃ ሲነቅዝና ብልሽት ሲጀምር ለሥጋዊ ተድላ ደስታ፣ ለጣዖት አምልኮና ለርኩሰት እንዴት እንደሚጋለጥ የዘጸአቱ ታሪክ ይነግረናል። የእስራኤል ልጆች በእጃቸው ባበጁት ጣዖት ዙሪያ ሊዘፍኑ እንደ ተነሡ ሁሉ የእኛንም የሙዚቃ ቅስቃሴ መነሾ መመርመር ያስፈልጋል። የአሁኑ ዘመን ሙዚቃ ያዘለው መልእክት፣ የሚቀርብበት ምንነትና የአቀማመሩ ሥርዐት ሁሉ ተያይዞ መላ ጤንነቱን መፈተሽ ተገቢ ነገር ነው።

በየቤተ ክርስቲያኖቻችን የሚቀርቡት መዝሙሮች መልእክት ላይ በቂ ትኩረት የተሰጠ አይመስልም። “ማን ዘመረ? እንዴት ዘመረ?” የሚሉትን ጥያቄዎች ስናነሣ “ምን ተዘመረ?” የሚለው ጥያቄ ግን እጅግም አይዘወተርም። ይህም ለመልእክት ይዘት የሚሰጠው ትኩረት እየሳሳ መምጣቱን ያመለክታል።

የመዝሙሮቻችንን ይዘት በጥቅሉ ለመናገር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምናልባት ያለፉት ሁለት ዐሥርታት የሚዘመሩት መዝሙሮች በአብዛኛው ትኩረታቸው እግዚአብሔርን ማወደስ፣ አማኞችን ማነጽ፣ ለማያምኑም የድነት ጥሪ ማቅረብ ነው ለማለት አያስደፍርም።

ብዙ ዝማሬዎች የግል ሁኔታን ብቻ የሚያንጸባርቁ ልቡናዊ (ሰብጀክቲቭ) ከመሆናቸው የተነሣ የመጽሐፍ ቅዱስን አዕማድ እውነቶች የሚያስተላልፉ አይደሉም። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ እነዚያን መሠረታዊ እምነቶች የሚቃወሙ ወይም የሚያኮስሱ ይሆናሉ። ‘ተባርኬያለሁ፣ በእጥፍ ቅባት ተቀብቻለሁ፣ ብሶብኛል፣ ከፍታ ላይ ወጥቻለሁ፤ ለእኔ ጌታ አድልቶልኛል’ ወዘተ. የሚሉ መዝሙሮች ግላዊነታቸው ብቻ ሳይሆን የነገረ መለኮት ሚዛናቸውም እጅግ ዝቅ ያለ ነው። ይዘቱ እጅጉን ምድራዊ፣ ቁሳዊ፣ ገንዘብ ተኮር ነው፤ ከክርስቲያናዊ ኅብረት ይልቅ ግለ ሰቡ ላይ ማጠንጠኑ ሊገኝ የሚችለውን የማነጽ ጸጋ ያጎድላል።

ስለ ግላዊ ሕይወት መናገር በራሱ ጥፋትም ስሕተትም እንዳይደለ እናውቃለን፤ ስለ እግዚአብሔር ምድራዊ ባርኮትም ማንሣት ሊኮነን አይገባም። ነገር ግን ስለ ራስ የተነገሩት ነገሮችም እንኳ ያለንበትን ሁኔታ በትክክል ያሳያሉ ወይ? የሚለው ብርቱ ጥያቄ መመለስ አለበት። ቀደም ባሉት ዓመታት የነበሩት ዘማሪዎች ስለ ራሳቸው የዘመሯቸውን ስናይ የውስጥን ሕይወት መርማሪ እንደ ነበሩ መገንዘብ ይቻላል።

የቀደሙት ምዕተ ዓመታት ዝማሬዎች በአብዛኛው ስለ መቀደስ፣ ለጌታ ስለ መለየት፣ ተግቶ ስለ መጸለይ፣ መስቀሉን ተሸክሞ ስለ መከተል፣ ስለ ጌታ ልደት፣ ስለ ሕማማቱ፣ ስለ ሞቱ፣ ስለ ትንሣኤው፣ ስለ ዳግም ምጽአቱ ይናገራሉ፤ ደግሞም 'በጸሎት እንትጋ ቃሉን እንብላ፣ ክርስቲያናዊ ፍቅርና መቀባበል ይኑረን፣ ከዓለምና ከዓለማዊነት እንውጣ፣ እንሸሽ'፣ ወዘተ. በማለት ደፍረው ይመክራሉ፣ ይገሥጻሉ። በተለይ የንስሐ፣ የመመለስና እንመለስ ዝማሬ አንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ።

በዚህ ዘመን አልፎ አልፎ እንደሚታየው እንደዚያ ዐይነት ዝማሬን የሚዘምር ምናልባት በቅድሚያ ከመሠዊያው አካባቢ፣ ከዕለቱ ሰባኪ ወይም አምልኮ መሪ ተቃውሞ ሊገጥመው ይችላል፤ 'ሕዝቡን አወረድክብን፣ ጉባኤው ላይ ውሃ ቸለስክብን' በሚል ሊወቀስ ይችላል።

የቀድሞውን በድፍን ማመስገን የዛሬዎችንም ያለ አግባብ መውቀስ የትም ፈቀቅ አያደርገንም። የክርስቲያን ሕይወትን ሙሉ ገጽታ በመዝሙር ግጥሞቻችን ውስጥ ማሳየት ግን ይገባናል። ለስብከትና ለትምህርት ትክክለኛነት መጋደል እንዳለብን ለመዝሙር ቃልም መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ሳንታክት መሥራት ይጠበቅብናል።

በሌላ በኩል ደግሞ የመዝሙርንና የሙዚቃን መልእክት ከዘማሪው ማንነት መነጠል አይቻልም። ምክንያቱም ክርስቲያን ዘማሪ ሙዚቀኛ ከመሆኑ በፊትና በላይ ልዑል እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ የክርስቶስ ተከታይ ነው። የሙዚቃ ባለሙያ (ሙያዊ) ብቻ አይደለም። "እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ" የሚለው ቃል እግዚአብሔር አምልኮን የሚቀበለው አምላኪውን ሲቀበል መሆኑን ያሳየናል።

ዘማሪው ንጉሥ ዳዊትም በንስሓ መዝሙሩ ውስጥ:- "መሥዋዕት ብትወድስ በሰጠሁህ ነበር፤ የሚቃጠለው መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም፤ የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፤ የተሰበረውንና የተዋረ ደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም" (መዝ. 51፥16) ብሏል።

በአሞጽ 5፥21 ላይም እንዲሁ:- "የዝማሬህን ጩኸት ከእኔ አርቅ፤
የበገናህንም ዜማ አልሰማም።
ነገር ግን ፍትሕ እንደ ወንዝ፣
ጽድቅም እንደማይደርቅ ምንጭ ይፍሰስ" ይላል።

ቤተ ክርስቲያን የዘማሪዎችንና የሙዚቀኞችን የኑሮ አቋም፣ የመዝሙሮቻችንን መልእክት ይዘትና መንፈስ ጠጋ ብላ ለማጤን ሁነኛ እንቅስቃሴ ካላደረገች ሥጋዊነትና ዓለማዊነት፣ ባዶ ጩኸትና ግርግር፣ ግብዝነትና ታይታ በታላቅ ፍጥነት መራባቱ አይቀርም። ያልተፈቀደ እንግዳ እሳት ይዘው ወደ መገናኛው ድንኳን ሲገቡ እንደ ሞቱት አገልጋዮች መቅሰፍት እንዳይደርስብን መፍራት አለብን። የምእመናን ነፍስ እየከሳ፣ የወንጌል ቃልም እየሳሳ ሲሄድ ንብም ማርም የሌለበት ወና ቀፎ ሆነን እንዳንቀር ቶሎ መንቃት ያሻናል። በማስተዋል ከተያዘ እጅግ ትልቅ ጥቅም ሊሰጥ የሚችለውን መንፈሳዊ የመዝሙርና የሙዚቃ አገልግሎት ከዘቀጠበት መታደግ የጊዜው ዋና ጥሪ ነው።

## VI. የመልእክቱ መስተላልፍ

### 1. የብዙኀን መገናኛ ተጽእኖ

የክርስቲያን መገናኛ ብዙኀን በኢትዮጵያ መሰራጨት ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የወንጌል መልእክት ደራሽነት ጨምሯል። በሬዲዮ ይተላለፉ የነበሩ ትምህርቶችና መልእክቶች በሺህዎች (ምናልባትም በሚሊዮኖች) የሚቈጠሩ አድማጮችን ደርሷል። የሬዲዮ አገልግሎት በዋና ዋና ከተሞች ካለው አድማጭ ባልተናነሰ በገጠር አካባቢ ላሉ አማኞች መተኪያ ያልተገኘለት አገልግሎት ነበረ። በአንዳንድ የአገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች የሬዲዮ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን አዳራሽ ውስጥ ወይም ሰዎች በሚሰበሰቡባቸው አካባቢዎች ይደመጥ እንደ ነበር ምስክርነቶች አሉ።

የኅትመቱን ዘርፍ የተቀላቀሉ የሚዲያ አካላት በበኩላቸው የማይናቅ ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል። በተለይም፣ ከመንግሥት ለውጥ ጋር ተያይዞ በመጣው የአምልኮ ነጻነት መከበር ቊጥራቸው እጅግ የበዛ የኅትመት ውጤቶች ለአማኝ ማኅበረ ሰቡ ሲቀርቡ ነበር። በእነዚህ ሥራዎች ውስጥ እጅግ ብዙ የሚያንጹ ትምህርቶች ቀርበዋል፤ እግዚአብሔር በአማኞች ሕይወት ውስጥ ያደረ ጋቸው ድንቆችና ተአምራት ተተርከዋል፤ ሰዎች ከወንጌል ኀይል የተነሣ ያገኙትን የሕይወት ለውጥ መስክረዋል፤ የኑፋቄና የስሕተት ትምህርቶች እኩላቸው ተተንትኗል ደግሞም ተኮንነዋል፤ በዚህም አማኞች ራሳቸውን እንዲጠብቁ የማንቂያ ደውል ሆነው አገልግለዋል፣ ለብዙዎች የአገልግሎት መስክ ሆነዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሳተላይት ቴሌቪዥን ሥርጭት ከመጀመሩ ጋር ተያይዞ ሰዎች አማራጭ የመገልገያ መንገድ አግኝተዋል። አማኞች የሆኑም ያልሆኑም ቤታቸው ውስጥ ሆነው በቴሌቪ ዥን መስኮታቸው የሚተላለፉትን መልእክቶች ይከታተላሉ። ይህ የቴሌቪዥን አገልግሎት በምዕራባውያን በስፋት ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ የክርስትና አስተሳሰቦች እንዲስፋፉ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከቱ ይነገርለታል።

ዛሬ በቴሌቪዥንም ሆነ በሬዲዮ በሚተላለፉ ፕሮግራሞች እንዲሁም በመጽሔቶችና በድረ ገጾች በሚቀርቡ ሥራዎች ብዙዎች እየተጠቀሙ እንደ ሆነ የሚናገሩ አሉ። ምንም እንኳ የቴሌቪዥን አገልግሎቱ ጉራማይሌ መልኮች ያየሉ ቢሆንም፣ ከሚተላለፉት ዝግጅቶች መካከል ጠቃሚ ትምህርቶችና መልእክቶች የሚያገኙ ሰዎች ቊጥር ቀላል አይደለም። አማኒያን ብቻ ሳይሆኑ፣ ያላመኑም ወገኖች በሚተላለፉት መልእክቶችና ትምህርቶች ከወንጌል መልእክት ጋር የመተዋወቅ ከዚያም ሕይወታቸውን ለክርስቶስ መስጠት የሚችሉበት አጋጣሚ እንደ ተፈጠረ ይነገራል።

የሚዲያው አገልግሎት ሌላኛው ትሩፋት፣ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ወደ እርሷ እንዲመጡ ከምታደ ርገው ጥሪ ባንጻሩ ወንጌል ወደየቤቱ እንዲገባ ማድረግ መቻሉ ነው። በመሠረቱ፣ ቤተ ክርስቲያን "ወደ እኔ ኑ!" በሚለው ጥሪዋ ትክክለኝነት ላይ ሰፊ ውይይት እንዳለ ይታወቃል። "እንግዲህ ሂዱና..." (ማቴ. 28፥19) የሚለው የጌታ ትእዛዝ ግን ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰው ሁሉ ዘልቃ የመግባት ተልእኮ እንዳለበት የሚያሳይ ነው። ለዚህ ደግሞ የብዙኀን መገናኛዎች ተልእኮውን ቀልጣፋና ደራሽ አድርገውታል ማለት ይቻላል። በርግጥ፣ የቴሌቪዥኑም ሆነ የሌሎቹ የብዙኀን መገናኛ ዘዴዎች አማኞች በጋራ ሆነው የሚተገብሩትን የወንድማማች ኅብረት የሚተካ አይደለም፤ መሆንም የለበትም። የቴሌቪዥን አገልግሎቱን አሉታዊ ተጽእኖ

የሚያሄሱ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ትተው በቴሌቪዥን ወይም በኢንተርኔት (online) ብቻ መንፈሳዊ አገልግሎት አገኘን የሚሉ ሰዎች ቍጥር እየጨመረ ነው። ተገቢ ጥናት ቢጠይቅም በእኛም አገር ይህን መሰሉ አዝማሚያ እየተስተዋለ መሆኑ እውን ነው።

ይሁን እንጂ አሁን ያሉ የክርስቲያን መገናኛ ብዙኀን ሙሉ ገጽታ ከላይ በተጠቀሰው አዎንታዊ መልኩ ብቻ የሚታወቅ አይደለም። የጠቀሜታውን ያህል እየፈጸማቸው ያሉት ስሕተቶችና ጥፋቶች እጅግ የሚያሳስባቸው ወገኖች አሉ። ይህም ጭንቀትና ስጋት ተራ ስጋት ሳይሆን፣ በተጨባጭ ጉዳት እያስከተለ እንደ ሆነ በመገንዘብ ላይ የተመሠረተ ነው።

2. በአሁኑ ጊዜ የሚታዩ የሚዲያ ችግር ሰንኮፎች

'የኢትዮጵያ የወንጌላውያን አማኞችን በቀዳማይነት ትኩረት ባደረጉ የሚዲያ አካላት በኩል እየ ተፈጠሩ ያሉ ችግሮች ምንድን ናቸው?' የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። ለዚህ ማሳያ ሊሆኑ የሚችሉ ጥቂት አስረጆች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

2.1 የስሕተት ትምህርት እና ልምምድ ማስተላለፊያ መሆኑ

የክርስቶስን ወንጌል ሰባኪዎች እንዳሉ ሁሉ ልዩ ወንጌል ሰባኪዎችም አሉ፤ እውነተኛ ነቢያት እንዳሉ ሁሉ ሐሰተኛ ነቢያትም አሉ፤ እውነተኛ አስተማሪዎች እንዳሉ ሁሉ ሐሰተኛ አስተማሪዎችም አሉ። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ፈተና ከሆኑት መካከል የስሕተት ትምህርትና እንግዳ ልምምዶች መሆናቸው ተደጋግሞ በመነገር ላይ ያሉ አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው። ባለፉት ዓመታት የኑፋቄ ትምህርቶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት የጎደላቸው ልምምዶች የአብያተ ክርስቲያናት ደጆችን ሲያንኳኩ ከርመዋል። በአንዳንድ ቦታዎች ላይም ተሳክቶላቸው ደጅ አስከፍተው ወደ ውስጥ መዝለቅ ችለው ነበር። ይህም እንኳ ሆኖ ከሞላ ጎደል በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ተመሳሳይ የወንጌል መልእክት ይተላለፍ ነበር ማለት ይቻላል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን፣ በተለይም ከኤሌክትሮኒክ ሚዲያው መምጣት ጋር ተያይዞ የስሕተት ትምህርቶቹ የቤተ ክርስቲያንን ደጅ ከማንኳኳት ይልቅ በቴክኖሎጂው ድጋፍ በቀጥታ ወደ አማኞች ቤት መዝለቅ ችለዋል። በዚህም አማኞች የትም ሳይሄዱ፣ ቤታቸው ቁጭ ብለው ከትምህርቶቹ ጋር የመተዋወቅ "ዕድሉ" ተፈጠረላቸው።

እንግዲህ 'የአንድ ክርስቲያናዊ ሚዲያ ኀላፊነት የት ድረስ ነው?' የሚለው ጥያቄ የሚነሣው እዚህ ላይ ነው። ገንዘብ ለከፈለ ሁሉ ሽፋን የሚሰጡ የሚዲያ "ባለቤቶች" ባሉበት ሁኔታ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ የሚሆን ጤነኛ ትምህርት በወጥነት ይተላለፋል ማለት እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል። በኤሌክትሮኒክ ሚዲያው፣ በተለይም በቴሌቪዥን የሚተላለፉ ሥርጭቶች "የነጻ ገበያ መርሕን" የሚከተሉ ይመስል ራሳቸውን ያለ ገደብ ለሁሉ ክፍት አድርገው ማቅረባቸው ኀላፊነት የጎደላቸው ለመሆኑ ማሳያ ነው። ከዚያም በላይ ጉዳዩን ገፋ አድርገን የተመለከትነው እንደ ሆነ፣ 'ከቶውንስ ግለ ሰቦቹና የሚመሩት ድርጅት ጤነኛ የሆነ አስተምህሯዊ አቋም አላቸው ወይ?' ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን። የእምነት እንቅስቃሴ የወለዳቸውና ለመጽሐፍ ቅዱስ እንግዳ የሆኑ ትምህርቶች ያለ ገደብ የሚያስተናግዱ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እና የፕሬስ ውጤቶች እየናሩ ተቆጣጥረውታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ሥልጣናዊነት ላይ ታምኖ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሱን ለሚያስለምድ አማኝ ማኅበረ ሰብ፣ 'ኀጢአት የሚባል ነገር የለም፤ በሥጋህ ላይ የፈለግኸውን ማድረግ ትችላለህ' የሚል ጥንት መጣሽ እኩይ ትምህርት (ኖስቲሲዝም) ሕዝበ ክርስቲያኑን መረን ለማውጣት እየታገለ ነው።

አንድ የክርስቲያን ሚዲያ ነኝ የሚል አካል፣ ክፉውንም ደጉንም ትምህርት እንደ ቡፌ በአንድ ጠረጴዛ ላይ ዘርግቶ 'የፈለጋችሁትን ምረጡና ብሉ' ማለት ፈጽሞ አይገባውም፤ ባለ ዐደራነትንም መጣል ነው። ምንም እንኳ በወንጌላውያን ክርስትና እምነት (በተለይም በኢትዮጵያ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት) መካከል በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ በአመለካከት ደረጃ ያሉ መለስተኛ ልዩነቶችን በልበ ሰፊነት መቀባበሉ ተገቢ ቢሆንም፣ አስተምህሯዊ መናጋቶችን ለሚያመጡ ትምህርቶች የሚኖረን "ታጋሽነት" ግን ገደብ ሊኖረው ይገባል፤ አልያ ልናርመው ወይም ልንመልሰው ወደማን ችለው ጥፋት መሄዳችን አይቀሬ ይሆናል።

"ነገር ግን እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት ምናልባት የእናንተም ልቡና ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ።" (2ቆሮ. 11፥3)

"ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ነቢይ ነኝ የምትለዋን ሴት ኤልዛቤልን ችላ ብለሃታል፤ እርሷ አገልጋዮቼ እንዲሴስኑና ለጣዖት የተሠዋ ምግብ እንዲበሉ በትምህርቷ ታስታቸዋለች።" (ራእ. 2፥20)

2.2 የግለ ሰብ ልዕልና መድረክ መሆኑ

ግለ ሰቦችን ያለቅጥ የማግነን ችግር በእኛ አገር የተጀመረ አይደለም። እንዲያውም ትልቅ ወቀሳ የሚቀርበው በአሜሪካን እና በአንዳንድ የአፍሪካ አገራት ያሉ መንፈሳዊ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ላይ ነው። በአብዛኛው ጣቢያዎቹ በአንድ ሰው ሰብእና ወይም አገልግሎት ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርጉ ከመሆናቸው የተነሣ፣ የግለ ሰቡ ማንነት ከሚያስተላልፈው መልእክት ("የወንጌል ቃል") በላይ ገዝፎ ሊታይ ይችላል። ክርስቲያናዊ ትሕትና የማይታይባቸው ማለትም፣ ያለ እነርሱ እግዚአብሔር በምድር ላይ የማይሠራ የሚመስላቸው እና እነርሱ ወይም የእነርሱ አገልግሎት ከሌሎቹ የተሻለ ብቻ ሳይሆን፣ ብቸኛው እንደ ሆነ አድርገው የሚያምኑ ኢትዮጵያዊ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች በቴሌቪዥን ጣቢያዎች እያየን ነው።

ይህን የመሰለው አካሄድ ግለ ሰብን ጣዖት ወደ ማድረግ የሚመራ መሆኑ ግልጽ ነው። የየትኛውም የክርስቲያን ሚዲያ ትኩረት የምሥራቹ ቃል ለሕዝቦች መድረስ እና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መታነጽ መሆን አለበት። ሌሎች ግቦችና ዐላማዎች ከሞላ ጎደል በእነዚህ ውስጥ የሚወድቁ ይመስለናል። ከዚህ ባለፈ ሰዎችን ለማግነን ወይም የጥቂቶችን ጥቅም ለማስጠበቅ አገልግሎት ላይ የሚውል መንፈሳዊ ሚዲያ ክርስቲያናዊ መሠረቱን ያጣል። አማኝ ማኅበረ ሰቡ ምንም እንኳን ከዚህ በተቃራኒው የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕሴት ቢኖረውም፣ በብዙኀን መገናኛ ላይ የሚታዩ ሰዎች የወካይነት ሚና ሊጫወቱ የሚችሉበት አጋጣሚው ሰፊ ነው። ታዲያ ከላይ የተጠቀሱ ዐይነት ግለ ሰቦች የምናሳያቸው አሉታዊ ተግባራት አማኝ ማኅበረ ሰቡ በአጠቃላይ ከኅብረተ ሰቡ ጋር በሚኖረው መስተጋብር አሉታዊ መልክ መከሰቱ አይቀሬ ይሆናል። ከዚህ የተነሣ አማኞች ለኅብረተ ሰቡ በሚያበሥሩት የወንጌል እውነት ተአማኒነት ላይ የራሱን የሆነ ጥላ ያጠላል።

2.3 በብዙኅን መገናኛ ሊተላለፉ የማይገባቸው ኹነቶች/ክንውኖች መቅረባቸው

ምእመናን ለአምልኮ ሲሰበሰቡ ሥርዐት በተሞላው መልኩ ሊሆን እንደሚገባ ቃሉ ይመክራል፤ ያዛልም። አንዳንዶቹ መንፈሳዊ ልምምዶች ከሥርዐታማ የተግባቦት ይዘት ወጣ ያሉ በመሆናቸው ልዩ አትኩሮት ተሰጥቶባቸው እንዴት ባለ መንገድ ተግባራዊ መደረግ እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል። እነዚህ ልምምዶች በአብዛኛው "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች" የሚባሉትን በመተግበር ላይ የሚስተዋሉ ናቸው። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ግልጽ ቢሆንም፣ በመካከላችን ለልምምዶች የሚሰጠው ስፍራ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ መጽሐፍ ቅዱሳዊው መርሕ ብዙ ጊዜ ትኩረት ሲነፈገው ይስተዋላል።

በቤተ ክርስቲያን የምንታዘበው አጓጉል መንፈሳዊ ልምምድ ሚሊዮኖች ሊመለከቱት በሚችሉበት ቴሌቪዥን ጣቢያ ያለ በቂ ጥንቃቄና እርምት ሲተላለፍ ደጋግመን እያየን ነው። በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻችን ስንመለከት የምንደነግጥባቸው አባባሎችና ልምምዶች በብዙኀን መገናኛ ሲተላለፉ ማየት ምን ያህል የሚያሸማቅቅ መሆኑን መገመት አያዳግትም።

ጥንቃቄ፣ አግባብና ሥርዐት በጐደለበት ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ስም ሽፋን የጥንቈላና የአስማት አሠራር፣ ሥነ ልቡናዊ ዝየዳ ተግባር (manipulation) ሊስተናገዱ ይችላሉ፤ ሐሰተኛውና እውነተኛው ይደባለቃል፤ ይሸቀቀጣል፤ ለሁከት ለውዥንብርም ይዳርጋል። ቃሉ ግን፣ "የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ይታዘዛሉ፤ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም። በቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲሁ ነው" (፲ቆሮ. ፲፬፥32-33) ይላል።

ማጥለልና መለየት የጎደለው ሥርዐት አልባ ክንውን ቢያንስ ሁለት ጉዳቶች ያስከትላል። የመጀመሪያው፤ ሰዎች የከበሩትን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንዳያከብሩና ሁልጊዜም እንዲጠራጠሩ ያደርጋቸዋል። እውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳይከበር፣ ለጋራ ጥቅምም እንዳይውል በርን ይዘጋል። ሁለተኛው ከወንጌል ተልእኮ ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን፣ ይህም የማያምኑ ሰዎች ከሚታዩት ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊቶች ከመቀላመዶችም የተነሣ ለምሥራቹ ቃልም ሆነ ለአማኝ ማኅበረ ሰቡ እውነተኛነት የሚኖራቸው አመለካከት ጽዩፍና እጅግ አሉታዊ እንዲሆን ያደርጋል። በሌላ አገላለጽ፣ ይህን መሰል ልምምዶች በብዙኀን መገናኛ መተላለፋቸው የወንጌል እንቅፋት የመሆናቸው አጋጣሚ ሰፊ ይሆናል። የወንጌልን ቃል ላልሰሙ ዐይነተኛ መሣሪያ ነው የተባለለት የብዙኀን መገናኛ፣ በአግባቡ ካልተያዘ ያንኑ ያህል ጥፋቱ የበዛ ይሆናል።

2.4 የግል ገበና አለመጠበቅ

ይህ ጉዳይ በዋናነት የሚመለከተው የቴሌቪዥን አገልግሎት የሚሰጡትን ነው። በተደጋጋሚ እንደምናየው ሰዎች ፈቃደኛ ባልሆኑበት መንገድ ምስላቸው በቴሌቪዥን ይተላለፋል። የአንዳንዶቹ ምስል "ከአጋንንት እስራት ነጻ ሲወጡ" ወይም "በመንፈስ ኀይል" ተነክተው ወይም ተገፍተው ሲወድቁ (አንዳንድ ጊዜም ርቃናቸው ሳይሸፈን) ይታያል። ሰዎች 'እግዚአብሔር አደረገልን' ለሚሉት ተአምር ምስክርነታቸውን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም በመለስተኛ ኅብረቶች ደረጃ ሊሰጡ ይችላሉ። እነዚሁ ሰዎች ግን በተመሳሳይ ምስላቸው በቴሌቪዥን ቀርቦ፣ ድምፃቸው ተቀርጾ 'ምስጢሬ' ያሉት የግል ጉዳያቸው እንዲነገር ላይፈልጉ ይችላሉ። በመሠረቱ ይህ ተፈጥሯዊ፣ ሰብአዊና ሕጋዊ መብታቸው ነው። ከዚህም ባለፈ፣ በቴሌቪዥን መስኮት መቅረባቸው በማኅበራዊ መስተጋብራቸው ላይ ሊያሳድር የሚችለው ጫና ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል። ለዚህ ነው ሰዎች ለብዙኀን መገናኛ ከመቅረባቸው በፊት ፈቃደኝነታቸው መረጋገጥ የሚኖርበት።

በአንጻሩ ግን፣ ይህ የሰዎች መሠረታዊ መብት ሳይጠበቅ ለሌሎች "የአገልግሎት ተደናቂነት" ማሳያ ተደርጎ በቴሌቪዥን የሚቀርብበት አጋጣሚ ብዙ ነው። የአንድን አገልጋይ ገድል ለማሳየት የሌሎች ሰዎችን ገመና በአደባባይ ማቅረብ ከማስታወቂያ ሥራ የሚለይ አይሆንም። ይህ ደግሞ የሞራልም ሆነ የሕግ ተጠያቂነትን ያመጣል። ምስክርነታቸውን በአደባባይ የሰጡ ሰዎች ይቅርና በጉባኤ የተካፈሉ ሰዎች ምስል በቴሌቪዥን መተላለፉ ጥያቄ ሊያስነሣ ይችላል። ለዚህ ነው ፕሮግራሙ በቴሌቪዥን ከመተላለፉ በፊት ጉባኤውን ቀድሞ ማሳወቅ ተገቢና ትክክለኛ አካሄድ የሚሆነው።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆን እጅግ ብዙ የሚባሉ የብዙኀን መገናኛ ሥራ ዝንፈቶች በኅትመቱም ዘርፍ ይሁን በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው የሚስተዋሉ ናቸው። የተጠቀሱት ችግሮች ለውይይት ብሎም ለቀጣይ ጥናት መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ በሚል የተጠቀሱ ናቸው። እስካሁን ያስተዋልናቸው ጉድለቶች ያመጡት ጉዳት በቀላሉ የሚታዩ ባይሆንም፣ አሁንም አልረፈደም ማለት ይቻላል።

## VII. የመፍትሔ ሐሳቦች

በአጠቃላይ አስተምህሮን አስመልክቶ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የመፍትሔ ሐሳቦች ቀርበዋል።

1) ለእውነተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴና አስተምህሮ ተገቢ የሆነ መሰፈርት ላይ ማተኮር።

በየጊዜው የሚነሡ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ለአስተምህሮ መጎልበትም ወይም መሳከር ምክንያት ይሆናሉ። በእኛ መካከል የሚነሡትን እነዚህን እንቅስቃሴዎች መለኪያቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑ እጅግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በመለኪያነት ማዋል ይበጃል።

- የክርስቶስ ኢየሱስን ማእከልነት፣ ሉዐላዊነትና ልይትነትን የሚያከብርና የሚያበስር፤
- የመስቀሉን ማእከልነት ቸል የማይል፤ ይልቁን የመስቀሉን ትሩፋትና መስቀላዊውን የኑሮ ዘይቤ በግልጽ የሚያውጅ፤
- ለቃሉ ባለ ሥልጣንነት ያለ ምንም ድርድር የሚገዛ፤ ትምህርቱንም ልምምዱንም በቃሉ ብርሃን ለመፈተሽ/ለማስፈተሽ የሚተጋ፤ ቃሉን በአግባቡ ለመፍታትና ለመተርጐም የሚጠነቀቅ፤
- የአማኞችን ሁሉ ክህነት አክብሮ የመንፈስን ሥራ ሳያጠፋ መልካሙን ለመያዝ ከክፉ ለመራቅ ሁሉን ለመፈተን መቁረጥ፤ የመንፈስ ቅዱስ

የጸጋ ስጦታዎችን መገለጥ ለጋራ ጥቅም በአግባብና በሥርዐት የሚያስተናግድ፤

- የእግዚአብሔርን ክብር የማይሻማ፣ በክርስቶስ ልዕልና ላይ የማያጠላና በራስ የግል ክብርና ማንነት ያልተዋጠ፤
- የመንፍስ ፍሬ ጎልቶና ተዘውትሮ የሚታይበት፤
- አእምሮን/ልቡናን የማይነሣ፤
- ተውኔታዊነትና ማስመሰልን የተጠየፈ።

2) መዝሙሮቻችንና የሚቀርቡባቸው የሙዚቃ ሥራዎች ለእግዚአብሔር የተቀደሱ፣ ወንጌል ተኮር የሆኑ፣ ኪነ ጥበባዊ ልቀት ያላቸው፣ ርቱዕ አስተምህሮ የሚያስተላልፉ እንዲሆኑ በአገልግሎቱ ላይ ከሚሠማሩት ጋር በተከታታይና በጥንቃቄ የውይይት፣ የሥልጠና የማበረታታት ሥራ መሥራት፤

3) የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም አወቃቀራችን ደቀ መዝሙርነትን በማስፋፋትና እውነተኛ አስተምህሮ ለማስረግ የተመቸ እንዲሆን አዲስ ኪዳናዊ ሞዴል መከተል፤ በንዑሳን ኅብረቶች ላይ በበለጠ ትኩረት ማድረግ፣ የቡድን መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጸሎት ዋና የሆኑባቸውን ኅብረቶች በወሳኝነት ማጎልበት፤

4) የቤተ ክርስቲያን የመድረክ አገልጋዮች፣ በተለይም ቃሉን በመስበክና በማስተማር የሚያገለግሉ መደበኛም ይሁን ኢ-መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትና ሥልጠና የሚያገኙበትን መንገድ በትጋት መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ፤

5) የሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶች ኑፋቄያዊ ትምህርቶችን ለይቶ በማውጣትና አፋጣኝ ምላሽ ማዘጋጀት፣ ቤተ ክርስቲያንን ማገዝ፣ አቅኚ ትምህርቱ የበለጠ ደራሽ እንዲሆን ዐውደ ገብ በሆነ መልክ ለማቅረብ መጣር፣ ውጤት ለማስገኘትም ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ጋር ተቀራርቦ መሥራት፤

6) ጤናማ ያልሆነ ትምህርት በምእመናን ላይ እንዳይዘራ በምስባኮቻችን እንዲያስተምሩና እንዲሰብኩ፣ እንዲጸልዩና እንዲዘምሩ የምንጠራቸው ሰዎች በጥንቃቄ መምረጥ፤

7) እንደ አስፈላጊነቱ በኑፋቄ ትምህርትና አሠራር እንዲሁም አራማጆች ላይ የጋራ አቋም መያዝና በገሃድ ማሳወቅ፤ "ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻል የተመረጡትን ለማሳት ሲሉ ታላላቅ ምልክቶችንና ታምራትን ያደርጋሉ። እነሆ፤ አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ።" (ማቴ. 24፥24-25)፤

8) አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸውን ጠንካራ የሚዲያ ተቋማት መገንባት፣ እንዲሁም የክርስቲያን ሚዲያ መማክርት በማቋቋም የሥነ ምግባር ዝንፈት በሚከሰትበት ጊዜ አስቀድሞ የሚወቅስና የሚመክር ከዚያም የእርምት ርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ።

## ማጠቃለያ

ቃሉ የማይጠፋ ሕያው ዘር፣ ሕያው አድራጊና ሠሪ፣ የዕለት ምግብ የእምነታችን መሠረት፣ የመንገዳችን መብራት፣ የሕይወት ዐላማና ትርጕም፣ የእውነታና የእውነት ገላጭ፣ የጨለማን ኀይላት ደምሳሽ፣ ንጽረተ ዓላማችንን ቀራጭ፣ የአስተምህሯችን ሁሉ ሜዳ ነው።

መንፈስ ቅዱስ የቃሉን ጥማትና አክብሮት ፈቃዱንም የመታዘዝ ልብ ይስጠን። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳት መጽሐፍትን ያስተውሉ ዘንድ የደቀ መዛሙርቱን አእምሮ እንደከፈተላቸው አእምሯችንን ይክፈትልን፤ እርሱንም ማየት እንድንችል የልቡና ዐይኖቻችንን ያብራልን።

እግዚአብሔር አምላክ ከጸጋው የተነሣ በግል ሕይወታችንም ሆነ በቤተ ክርስቲያናችን እውነት ከፍቅር ጋር ያበረበትን፣ ዕውቀት ከትሕትና ጋር የተቃቀፈበትን፣ ኀይል በርኅራኄ የተቃኘበትን፣ ብልህነት ከየዋህነት ጋር የተሸረበበትን፣ ኀይለ መለኮት ከትምህርተ መለኮት ጋር የተጣመደበትን ማንነት ያሳድርብን።

ክብር ለእግዚአብሔር አብ

ክብር ለእግዚአብሔር ወልድ

ክብር ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሁን!

በአስተምህሮ ጥራት ዙሪያ የቀረቡ የውይይት ጥያቄዎች

1) የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተዛባ አተረጓጐም ከፍተኛ የአስተምህሮ መበላሸት እንደሚፈጥር የታወቀ ነው። ትክክለኛ አተረጓጐም እንዲኖርና እንዲዳብር ምን ልናደርግ ይገባል?
2) የስሕተት ትምህርትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልምምዶች የመስፋፋታቸው ሰበቡ ምንድነው? በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ይህንን በሚያራምዱ ላይ ምን አቋም እንያዝ?
3) አሁን ያለው የሚዲያ አገልግሎታችን ማለትም ሬዲዮ፣ ቲቪ፣ መጽሔት፣ መጻሕፍትና ኢንተርኔት እንዴት ይገመግሙታል? ለመንግሥቱ መስፋትና ቅዱሳንን ለማነጽ መጠቀም የሚቻለው ምን ብናደርግ ነው?
4) የቃሉን እውነት ከለቀቀ ስብከት፣ አስተምህሮና ልምምድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖቻችንን እንዴት ይጠበቁ? በየግላችንስ ምን ልናደርግ ይገባል?
5) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መገለጥ እንደ ቃሉ ጥቅም ላይ የሚውሉበትንና በቃሉ የሚመዘኑበትን መንገድ እንዴት እናብጅ?
6) ከላይ በተነሡ ችግሮች አኳያ፣ ራሳችንን ስንመረምር በግልም ሆነ በጋራ ንስሓ ልንገባባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ምንስ የንስሓ ፍሬ እናሳይ?

## በሕይወት ጥራት አንጻር ከተሳታፊዎች የተሰጡ የመፍትሔ ነጥቦች

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለውንና ተገቢውን ሥነ አፈታት የተከተለውን ትምህርት ለአማኞች፣ ለአገልጋዮች እንዲሁም ለመሪዎች መስጠት፤
2. የስሕተት ትምህርቶችንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ልምምዶችን በጥብቅ መከታተልና ሲከሰቱ የእርምት ርምጃ እንዲወስዱ ማድረግ፣ ይህ ካልሆነም በግልጽ/በአደባባይ ማውገዝ፤
3. የአገልግሎት መድረኮችን በአግባቡ መቈጣጠር፣ በተለይም የተጋባዥ አገልጋዮችን አስተምህሯዊና ግላዊ ሕይወት አስቀድሞ ማወቅ፤
4. በእግዚአብሔር ቃል የተቃኘና ሚዛናዊ የሆነ የመንፈሳዊ ስጦታ አገልግሎትን ተግባራዊ ማድረግ፤
5. በቤተ እምነት ደረጃ፣ ብሎም በአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት በኩል የአስተምህሮ ጉዳይን የሚከታተል ክፍል እንዲኖር ማድረግ፣ ካለም ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል፤
6. ምእመኑ ጥሎ ይሄዳል ከሚል ሥጋት ወጥቶ በአግባቡ ለማረም በሚያስችል መንገድ ለመገሠጽ ቁርጠኛ መሆን፤
7. በየአጥቢያው ያሉ አገልጋዮች ጥሪያቸውንና ጸጋቸውን በመለየት ተተኪዎች እንዲሆኑ በሩን መክፈት፤
8. አብያተ ክርስቲያናት የራሳቸውን ሚዲያ ተቋም በመገንባት ለምእመናን ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤
9. የሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶችን ጥራትና ደረጃ የሚቈጣጠር አካል እንዲኖር ማድረግ፤ ትክክለኛ ትምህርት የሚሰጡትንም ተቋማት በየጊዜው ማሳወቅ፤
10. ከጅማ ጉባኤዎች ይልቅ አነስተኛ ኅብረቶችን የቤተ ክርስቲያን ዋና የአገልግሎት ማእከል ማድረግ፡፡

# የተሐድሶ ጥሪ

## መመርመር - መመለስ - መታደስ
## በግልም በቤተ ክርስቲያንም ደረጃ

*"እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ መልሰን፤ እኛም እንመለሳለን፤*
*ዘመናችንን እንደ ቀድሞ አድስ" ሰቆ. 5÷21*

# የአመራር ጥራት

## I. መግቢያ

ዛሬ ያለንበት ወቅት ከወንጌል አገልግሎትና ከቤተ ክርስቲያን ዕድገት አኳያ ሲታይ በብዙ ሁኔታዎች እየተለወጠ መጥቷል። ክብሩ ለእግዚአብሔር ይሁንና፣ በምድራችን ከተከበረው የእምነት ነጻነት የተነሣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎት እየሰፋ መምጣት ብቻ ሳይሆን፣ ለበለጠ ዕድገትና ተሳትፎ ያለው ተስፋ እየጨመረም መጥቷል። እነዚህ አመቺ ሁኔታዎች ብዙዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲጨመሩ፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ቍጥር ከእጥፍ በላይ እንዲጨምር፣ በኅብረተ ሰቡም ውስጥ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እንቅስቃሴና ተሳትፎ የበለጠ ዕውቅና እንዲያገኝ ረድቷል። ከምንጊዜውም ይልቅ ዛሬ የአገልጋዮችና የአገልግሎቱም መንገድ ዐይነት እየበረከተ መጥቷል። እነዚህ በጐ ገጽታዎች የሚደነቁ ቢሆንም በዚህ ዕድገት ሂደት ያጋጠሙ የአመራር ችግሮችና ተግዳሮቶች ደግሞ ከሚታየው በጐ ተጽእኖ ጋር የማይተናነሱ ሆነዋል።

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰጠን ሰፊ የእምነት ነጻነት መከበርና የአገልግሎት ዕድል አኳያ ሲታይ እውነተኛ የዓለም ብርሃንና የምድር ጨው ለመሆን ችለናል ወይ? መልካም አስተዳዳርንስ በተመለከተ አካሄዳችን ጽድቅና ፍትሕን፣ መቀባበልንና መከባበርን ያሳያል ወይ? ችግሮቻችንን በሰከነ አመራር በመንፈሳዊ አካሄድና እግዚአብሔርን በመፍራት መንገድ መፍታት ችለናል ወይ? ይቅርታ ማድረግና እርቅን በማስፈን ረገድ በመካከላችን የሚታየው ገጽታ ምን ይመስላል? የቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር መርሓችን ምን ያህል መንፈሳዊና ሥነ ምግባራዊ ነው? የሚሉትና ሌሎችም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን አጠቃላይ የአመራር፣ የአስተምህሮና የአምልኮ አቅጣጫዎቹን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ተደጋግመው እየተነሡ ነው። ስለሆነም ዛሬ ያለንበትን ሁኔታ መልካሙንም ደካማውንም፣ በተለይ ከአመራር አቅጣጫ ያጋጠሙንን ቀውሶች በየፈርጁ ማስቀመጥና ማየት የወቅቱ ጥያቄ መሆን ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተጣለብን ዐደራ ነው። በአሁኑ ጊዜ በመካከላችን እየገዘፉ ለመጡት ተግዳሮቶች ወቅታዊ ምላሽ መስጠት ካልቻልን አገልግሎታችን ሁሉ አሳፋሪና አስከፊ፣ አንድነታችንና ኅብረታችን ደካማና ፍርክርክ እንደሚሆኑ ያገኘናቸውም የአገልግሎት ዕድሎች ሁሉ ሊባክኑና ሊመክኑ እንደሚችሉ አያጠራጥርም።

የችግሮቻችን አንዱና ዋነኛው ምክንያት የእኛ የአገልጋዮች፣ የመሪዎች የሕይወትና የአመራር ጥራት ጉድለት መሆኑ ብዙ አያከራክርም። ምክንያቱም ለቤተ ክርስቲያን ውድቀትም ሆነ መነሣት መሪዎች ወሳኝ ሚና አለን። በዚህ ጽሑፍ ለመዳሰስ የምንሞክረው ዛሬ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ የሚታየው የአመራር ጥራት በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን ምን እንደሚመስል ለማየትና ካለንበትም ውድቀት በመመለስ ከጌታ የተቀበልነውን ኀላፊነት እንድንወጣ ልንወስድ የሚገባንን ርምጃዎች ለመጠቆም ነው።

## II. መሪነት ምንድነው?

ለመሪነት የሚሰጡ ትርጕሞች በጣም ብዙ ናቸው። ከሚሰጡት የተለመዱ ትርጕሞች የምናገኘው ማእከላዊ ዐሳብ፣ "መሪነት ተጽእኖ ማሳደር ነው" የሚለው ነው። መሪነት ሰፋ ባለ መንገድ ሲገለጽ ደግሞ "ተጽእኖ የማሳደር ሂደት ነው። በማንኛውም ጊዜ በሌሎች ሰዎች የግል ሕይወት፣ በሥራ ሕይወታቸው፣ በአስተሳሰባቸው፣ በባሕርያቸው ወይም በዕድገታቸው ላይ ተጽእኖ ለማሳደር ስንሞክር የመሪነትን ሚና እየተጫወትን ነው።"

በዚህ ትርጕም መሠረት መሪ መሆን የግድ ሥልጣንን ወይም ልዩ ማዕረግን አይፈልግም። ሥልጣንና ሹመት ለመምራት የተመቸ ዕድል ቢሰጡንም በራሳቸው ግን መሪዎች ሊያደርጉን አይችሉም። አንድ ሰው ሥልጣን እያለው ተጽእኖ ማሳደር ካልቻለ እየመራ አይደለም። መሪ ለመሆን ተከታይ እንዲኖረን ግድ ይላል። መሪነት ተጽእኖ ማሳደር ነው ካልን መሪ የሚያሳድረው ተጽእኖ በጎ ወይም ክፉ ሊሆን ይችላል። የመሪ ተጽእኖ አፍራሽም ሆነ ገንቢ መሆኑን የሚወስኑት ሦስት ዋና ዋና ነገሮች፡- የመሪው ባሕርያት፣ የሚያነሣሣው ጉዳይና (motive) እና ይዞ የተነሣው አጀንዳ ናቸው። ይህ ጽሑፍ የሚያተኩረው በቤተ ክርስቲያን በተለያየ የመሪነት ኀላፊነት ላይ ያለን መሪዎች ላይ ቢሆንም፣ የተለየ ሹመት ባይኖራቸውም በተለያየ መንገድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጽእኖ የምናሳድረውን ሁሉ ይመለከታል።

## III. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪነት

'እኛን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሕይወትም ሆነ የአመራር ጥራት ለመመዘን መስፈርቱ ምንድን ነው?' ብሎ መጠየቁ አግባብነት አለው። ምክንያቱም አንዱ እንደ ድክመት የሚያየውን ሌላው ደግሞ እንደ ጥንካሬ ሊቈጥረው ስለሚችል፣ የጋራ የሆነ የመሪነትን ጥራት የምንለካበት መሥፈርት ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው።

ቤተ ክርስቲያን በሰው በጎ ፈቃድና ሥራ የተመሠረተች ምድራዊ ተቋም አይደለችም። የቤተ ክርስቲያን መሥራችና ባለቤት በገዛ ደሙ የዋጃት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተበትንም ዓላማ ሆነ የምትመራበትንም መርሕ በቅዱስ ቃሉ ስለገለጠልን ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታም ሆነ የመሪዎቿን የአመራርና የሕይወት ጥራት ለመገምገም መሥፈርቱ የጌታ ቃል መሆን እንዳለበት መገንዘብ ግድ ነው።

በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የአመራር ጥራት ለመለካት መሥፈሪያው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ነው ካልን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሪነት ያለውን አስተምህሮ በአጭሩ መቃኘት አስፈላጊ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሪነት የሚያስተምረውን ትምህርት ሁሉ በአንድ ምዕራፍ ወይም አንድ መጽሐፍ ላይ ተሰብስቦ አናገኝም። ግን ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ስናጠና ስለ መሪነት በቀጥታ የተጻፉትን መርሖዎች፣ በጎ ከሆኑ ምሳሌዎችና፣ በጎ ያልሆነ መሪነት ምን እንደሚመስል ከሚገልጹ ምሳሌዎች በመነሣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠውን ትምህርት መረዳት እንችላለን። በብሉይ ኪዳን የምናገኛቸውን የመሪነት ትምህርቶች በአጭሩ ከዳሰስን በኋላ ዋናው ትኩረታችን የሚሆነው አዲስ ኪዳን መርሖዎች ላይ ይሆናል።

## IV. መሪነት በብሉይ ኪዳን

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ሰው በኀጢአቱ ምክንያት ከወደቀበት ማንነትና ሁኔታ ለመታደግና አዲስ ሕይወት ለመስጠት እግዚአብሔር የጀመረውን የድነት ዕቅድና ሥራ ነው። እግዚአብሔር በአዳምና በሔዋን ላይ ርግማንን ቢያስተላልፍም ከርግማኑ ጋር የተስፋ ቃል ሰጥቷል። የሰው ልጅ ውድቀት ዘላለማዊ እንደማይሆንና ከሴቲቱ የሚወለደው በጠላት ላይ ድልን እንደሚቀዳጅ ተስፋ ገባ (ዘፍ. 3፥15)። ከሴቲቱም ዘር የሚመጣው

የሰው ልጅ ያጣውን ያንን ከእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ሆኖ የመግዛቱን የእግዚአብሔርን የቀደመ ዓላማ ተግባራዊ እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጠ። ይህ ተስፋ የሚያመለክተው ከሴት ተወልዶ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅና ወደ ክብር በመመለስ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ አገዛዝ የሚመሠርተውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው።

እግዚአብሔር የጀመረውን የድነት ዕቅዱን ሲያከናውን የተለያዩ ሰዎችን በብሉይ ኪዳን ተጠቅሟል። እንደ ኖህ፣ አብርሃም፣ ይሥሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ሙሴ፣ ዳዊትና የመሳሰሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማስፈጸም የተሰጡ ነበሩ። ከእግዚአብሔር ጋር ከነበራቸው ጤናማ ግንኙነት የተነሣ በትውልዳቸው ላይ በጎ ተጽእኖ ለማምጣት የቻሉ መሪዎች ነበሩ።

ከእነዚህ መሪዎች ሕይወት የምንረዳው ትልቅ ትምህርት፣ እውነተኛ መሪ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት የሚጠቀምበት ሰው መሆኑን ነው። በእግዚአብሔር የተጠራ መሪ ተልእኮውን በሚገባ መወጣት የሚችለው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠንቅቆ በመከተልና በመታዘዝ ነው (ኢያ. 1፥5-8)። እውነተኛ መሪ ከራሱ ጥቅም ይልቅ የሚመራውን ሕዝብ የሚያስቀድም፣ ሸክም የሚሰማውና ራእይ ያለው ነው፤ ይህም የእግዚአብሔር አጀንዳ የእርሱ አጀንዳ የሆነ ሰው ነው።

የእስራኤል የመጀመሪያ ንጉሥ ሆኖ የተሾመው ሳዖል፣ ሕዝቡን እንደ እግዚአብሔር ዐሳብ ከመምራት ይልቅ የራሱን መንገድ በመከተሉ፣ ንግሥናው በውድቀት ተጠናቀቀ። እግዚአብሔርም ንግሥናውን ከእርሱ ወስዶ “እንደ ልቤ” ላለው ለዳዊት ሰጠው። ምንም እንኳን ዳዊት ወደ መጨረሻው የንግሥና ዘመኑ በሠራቸው ኀጢአቶች የተነሣ ነገሮች ቢበላሹም፣ ከእርሱ በኋላ ለተነሡ ነገሥታት ሁሉ እንደ ምሳሌ እየተጠቀሰ የቀጠለ ንጉሥ ነበር። ዳዊት በዘመኑ የእግዚአብሔርን ዐሳብ ያገለገለ ሰው ነበር (ሐዋ. 13፥27)። እግዚአብሔርም ዘላለማዊ የሆነ መንግሥቱን ከዳዊት ዘር ከሚወጣ ንጉሥ እንዲመሠርት ቃል ኪዳን ገባለት (2ሳሙ. 7)።

በእስራኤልና በይሁዳ ከነገሡት ነገሥታት ብዙዎቹ ሕዝቡን እንደ እግዚአብሔር ዐሳብ አልመሩም። ስለ ነገሥታቱ (እረኞቹ) እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ነበር፦

የሰው ልጅ ሆይ ትንቢት ተናገር፣ በእስራኤል እረኞች ላይ ትንቢት ተናገር፣ እረኞችንም እንዲህ በላቸው። ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው! እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ ጠጕሩንም ትለብሳላችሁ፥ የወፈሩትን ታርዳላችሁ በጎቹን ግን አታሰማሩም። የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኀይልና በጭቈናም ገዛችኋቸው።

እረኛም በማጣት ተበተኑ፣ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፣ ተበተኑም። በጎቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዝብዘዋል፥ በጎቼም በምድር ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል የሚሻም የሚፈልግም አልነበረም።

ስለዚህ፣ እረኞች ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ሕያው ነኝና እረኛ ስለሌለ እረኞቼም በጎቼን ስላልፈለጉ እረኞችም ራሳቸውን እንጂ በጎቼን ስላላሰማሩ፣ በጎቼ ንጥቂያ ሆነዋልና፣ በጎቼም ለምድር አራዊት ሁሉ መብል ሆነዋልና ስለዚህ፣ እረኞች ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፣ በእረኞች ላይ ነኝ፣ በጎቼንም ከእጃቸው እፈልጋለሁ፤ በጎቼንም ከማሰማራት አስተዋቸዋለሁ። ከዚያም ወዲያ እረኞች ራሳቸውን አያሰማሩም በጎቼንም ከአፋቸው አድናለሁ፤ መብልም አይሆኑላቸውም። (ሕዝ. 34፥1-10)

ይህ ክፍል የሚያሳየን እግዚአብሔር ለመንጋው እንደሚገደውና መንጋውን መጠቀሚያ የሚያደርጉት “እረኞች” ከርሱ ፍርድ እንደማያመልጡ ነው።

በእነርሱም ክፋት ምክንያት እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ ለባቢሎናውያን አሳልፎ ሰጣቸው። ባቢሎናውያን ማረኳቸው፤ ቤተ መቅደሱን አፈረሱ፤ ከተሞቻቸውን በእሳት አቃጠሉ፤ ሕዝቡ ወደ ምርኮ ተጋዘ። ከእስራኤላውያን ታሪክ የምንማረው ትልቁ ነገር ለአገሪቱ ውድቀትም ሆነ መነሣት ዋናው ምክንያት የነበሩት ነገሥታቱና የሕዝብ አለቆች እንደ ነበሩ ነው።

ከነገሥታቱ በተጨማሪ የእግዚአብሔር ወኪል ሆነው ሕዝቡን በማስተማር፣ የእግዚአብሔርን መንገድ በማሳየት፣ ከክፉ መንገድ በመመለስ የመምራት ኀላፊነት የነበረባቸው ካህናቱና ነቢያቱ የተጣለባቸውን መለኮታዊ ዐደራ ባለመወጣታቸው፣ ለእግዚአብሔር ቃል ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሕዝቡ ለጥፋት ተዳረገ። ስለ ካህናቱ እግዚአብሔር የሚለውን ሚልክያስ ሲናገር፦

“ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከንፈሮቹ ዕውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፤ ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል። እናንተ ግን ከመንገዱ ፈቀቅ ብላችኋል በሕግም ብዙ ሰዎችን አሰናክላችኋል የሌዊንም ቃል ኪዳን አስነውራችኋል፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፦ ስለዚህ መንገዴን እንዳልጠበቃችሁ፣ በሕግም ለሰው ፊት እንዳዳላችሁ መጠን፣ እኔ ደግሞ በሕዝብ ሁሉ ፊት የተናቃችሁና የተዋረዳችሁ አድርጌአችኋለሁ።” (ሚል. 2፥7-9)

እንደ ካሕናቱ ሁሉ ነቢያቱም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የማይመላለሱ ነበሩ። ኤርምያስ በዘመኑ ስለነበሩ የሐሰት ነቢያት እንዲህ ነበር ያለው፦

“በኢየሩሳሌምም ነቢያት ላይ የሚያስደነግጥን ነገር አይቻለሁ፤ ያመነዝራሉ በሐሰትም ይሄዳሉ ማንም ከክፋቱ እንዳይመለስ የክፉ አድራጊዎችን እጅ ያበረታሉ ሁሉም እንደ ሰዶም የሚኖሩባትም እንደ ገሞራ ሆኑብኝ። ... የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ትንቢት የሚናገሩላችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ ከንቱነትን ያስተምሩአችኋል ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የወጣውን ራእይ ይናገራሉ። ለሚንቁኝ ሁልጊዜ እግዚአብሔር፦ ሰላም ይሆንላችኋል ብሎአል ይላሉ በልቡም እልከኝነት ለሚሄድ ሁሉ ክፉ ነገር አያገኛችሁም ይላሉ።” (ኤር. 23፥14-16)

እነዚህ ቃሎች የተነገሩባቸው ካህናትና ነቢያት ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ፍርድ አላስመለጡም፣ እነርሱም አላመለጡም። ለበረከት መሆን ሲገባቸው ለእስራኤል መውደቅ ምክንያት ሆኑ።

ምንም እንኳ ብዙዎቹ የእስራኤል መሪዎች ሕዝቡን ወደ ጥፋት በመምራት ለውድቀት ቢዳርጉትም እግዚአብሔርን ግን ለሕዝቡ የገባውን ቃል አላጠፈም። በምድሪቱ የነበሩ ነገሥታት፣ ካህናትና፣ ነቢያት የተሰጣቸውን ኀላፊነት ባይወጡም፣ እግዚአብሔርን ግን ፍጹም የሆነ ንጉሥ፣ ካህንና ነቢይን አዘጋጅቶ ነበር። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከዳዊት ወገን የሆነ ለዘላለም የሚነግሥ፣ ሕዝቡን የሚታደግ መሪ እንደሚመጣ ተንብየው ነበር። የእስራኤል ሕዝብም የዚህን መሢህ መምጣት ይጠባበቁ ነበር።

## V. መሪነት በአዲስ ኪዳን

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊከተሉ የሚገባቸውን መርሖዎች በቃልም በተግባርም ያስተማረው ጌታ ኢየሱስ ነው። እርሱ ወደ አብ ከማረጉ በፊት የሰጠውን ዐደራ የተቀበሉት ደቀ መዛሙርቱም በኖሩት ሕይወትና ባስተማሩት ትምህርት ዛሬ ላለችው ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቂ መመሪያ እናገኝበታለን። በአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልንከተለው የሚገባንን መርሖች ከተገለጹት ውስጥ ዋና ዋናዎቹን እንመልከት።

1. ራስን ለክርስቶስ ማስገዛት

የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ዛሬ በምድር ላይ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ነች። የቤተ ክርስቲያን ራስ ክርስቶስ፣ እርሷ ደግሞ አካሉ እንደ ሆነች መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል (ቈላ. 1፥18)። ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳችንን ለክርስቶስ በማስገዛት ሕዝቡን እርሱ ባሳየው ምሳሌነት ልንመራ ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ነች። ጌታ ለጴጥሮስ “በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም” (ማቴ. 16፥18) ነበር ያለው። “ቤተ ክርስቲያኔን” የሚለው ቃል ባለቤትነትን ያሳየናል። ጳውሎስም ለኤፌሶን ምእመናን እንዲህ ነበር ያላቸው፤ “በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ” (ሐዋ. 20፥28)። ስለ ሆነም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ነች፤ ቤተ ክርስቲያንን የምንመራ ሰዎች የክርስቶስ ወኪል ሆነን የምንመራ እረኞች ነን፤ እርሱ ደግሞ የእረኞች አለቃ ነው (1ጴጥ. 5፥4)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የያዝነው ቦታ በውክልና ከጌታ የተሰጠንና ዋናው ተጠያቂነታችንም ለእርሱ እንደ ሆነ ለአፍታም ልንዘነጋ አይገባንም። የምንመራው ሕዝብ ጌታ ኢየሱስ በገዛ ደሙ የዋጀው ሕዝብ ስለ ሆነ በገዛ ፈቃዳችን ልንመራውና ለራሳችን ጥቅም ማግኛ ልናደርገው አይገባም። የእግዚአብሔርን መንጋ መምራት በአደራ ከጌታ የምንቀበለው ኀላፊነት እንጂ በእግዚአብሔር መንጋ ላይ እንድንሠለጥንና ቤተ ክርስቲያንንም እንደ ራሳችን ንብረት ወይም ድርጅት እንድንቈጥር የሚያደርግ አይደለም።

2. የቤተ ክርስቲያንን ማንነት፣ ተልእኮና ተግባር መረዳት

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከዘላለም ጥፋት የዳኑ አማኞች ማኅበር ናት፤ በደሙና በሥጋው በተሠራው የማስታረቅ ሥራ አንድ አካል የሆነች ናት፤ ራስዋና አለቃዋ፣ የእምነቷ ጀማሪና ፍጹም አድራጊ ይኸው ያዳናት ክርስቶስ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ባለቤት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ከተገነዘብን፣ ቤተ ክርስቲያንን ለምን እንደመሠረታትና በምድርም ላይ ምን ተልእኮ እንድትፈጽም እንዳስቀመጣት በመረዳት ያንን ተልእኮ መፈጸም ዋና ትኩረታችን ሊሆን ይገባል። “ታላቁ ተልእኮ” ብለን በምንጠራው ክፍል ጌታ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ዋናው ተልእኮ ተገልጿል። “ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ” (ማቴ. 28፥18-20)። በዚህ ክፍል መሠረተ የቤተ ክርስቲያን ዋናው ተልእኮ ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው። ሰዎችን የጌታ ደቀ መዛሙርት (የተሰጡ የጌታ ተከታዮች) የማድረግ ሂደት ወደ አላመኑት መሄድ፣ ወንጌልን መስበክ፣ ማጥመቅና ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት መጨመር፣ ጌታ ያዘዘውን ትምህርት ሁሉ ማስተማርን ያካትታል።

በዚሁ ጥሪ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ለሕያው አምላክ ንጹሕ አምልኮና ጸሎት እንዲቀርብ፣ ኅብረትና አንድነት እንዲጠበቅ፣ ምግባረ ሠናይ እንዲስፋፋ፣ ለፍትሕና ለሰላም ዐይነተኛ ምሳሌ ሆና ራሷን እንድታቀርብ፣ በኅብረተ ሰቡም ውስጥ ፍትሕንና ሰላምን እንድታሰርጽ ዐደራ እንደተጣለባት ሊታወቅ ይገባል።

በኤፌ. 4፥11-13 እንደምንመለከተው መሪዎች/አገልጋዮች መሰጠታቸው አካሉ ይገነባ ዘንድ መላ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ለማዘጋጀትና ለማብቃት ነው። የመሪዎች መኖር የሚያተኩረው በራሳቸው በመሪዎች ላይ ሳይሆን፣ አካሉ በሆነው መላው ምእመን ላይ ነው።

3. ሎሌ መሪዎች መሆን

ከጌታ ከኢየሱስ መሪነት የምንማረው፣ በመጽሐፍ ቅዱስም ተጽፎ የምናገኘው የመሪነት ምሳሌ አገልጋይ (ሎሌ) መሪነትን ነው።

“ኢየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ የአሕዛብ አለቆች ተብሎ የምታስቡት እንዲገዟቸው ታላላቆቻቸውም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።” (ማር. 10፥42-45)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሎሌ መሪነትን በቃል ብቻ ሳይሆን በአኗኗሩም አሳያቸው። ጌታና መምህራቸው ሆኖ ሳለ፣ ዝቅ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ (ዮሐ. 13)። ከአብ ጋር እኩል ሳለ፣ ሁሉ ያለው ጌታ ሰማያዊ ክብሩን ትቶ ራሱን ባዶ አድርጎ፣ ሰው ሆኖ ወደ ምድር በመምጣት፣ የባሪያን መልክ በመያዝ፣ ለሞት ያውም ለመስቀል ሞት የታዘዘ ሆነ (ፊል. 2፥5-11)።

እኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምሳሌ አድርገን ልንከተለው የሚገባን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ የፊሊጵሲዩስ ምእመናንን “ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትህትና ቍጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ። እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተ ዘንድ ይሁን” (ፊል. 2፥3-5) በማለት ይመክራቸዋል። ይህ ራስን ዝቅ አድርጎ ሌሎችን በማስቀደም የማገልገል አስተሳሰብ ከአማኞች ሁሉ የሚጠበቅ ነው። ይህ ክፍል ራስ ወዳድነት፣ ለራስ ጥቅም ብቻ መኖር፣ ከንቱ ውዳሴ መፈለግ፣ የጌታን ፍቅርና ቸርነት ካየን ከክርስቶስ ተከታዮች እንደማይጠበቅ ያስተምረናል።

- ሎሌ መሪ የሚያገለግለው ራሱን ለመጥቀም ሳይሆን ሌሎችን ለመጥቀም ነው

ሐዋርያው ጴጥሮስም በተለያየ ቦታ ተበትነው ለነበሩ ቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት መሪ ለነበሩ ሽማግሌዎች ሲጽፍ እንዲህ አለ፡-

እንግዲህ እኔ፣ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፣ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፣ ... በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት (1ጴጥ. 5፥1-3)።

መሪዎች ከገንዘብ ወይም ከግል ክብርና ዝና በኋላ ልንሮጥ አይገባንም። መሪዎች የሚመሩትን ሕዝብ መጠቀሚያ የማድረግ ችግር በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የታየ ነበር። ሎሌ መሪ የሚያገልግለው ራሱን ሳይሆን የሚመራውን ሕዝብ ነው። ዛሬም ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው በምናገኘው ጥቅም ላይ ሳይሆን በምነሰጠው አገልግሎት ላይ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት ሲሉ የሐሰት ትምህርት ስለሚያስተምሩ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ለቲቶ ሲጽፍ፣ “እነዚህም ስለ ነውረኛ ረብ የማይገባውን እያስተማሩ ቤቶችን በሞላው ስለሚገለብጡ፣ አፋቸውን መዝጋት ይገባል” (ቲቶ 1፥11) ነበር ያለው።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ምሳሌነት ባለው ሕይወት በመካከላቸው እንዴት ያገለግል እንደ ነበረ በሐዋ. 20 ላይ እንዲህ ሲል ገልጿል፡-

ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ። አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ። ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤ እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ። (ሐዋ. 20፥31-34)

በሌላ ቦታ ደግሞ እርሱና አብረውት የሚያገለግሉት የተሰሎንቄ ምእመናንን በፍቅርና ራስን በመስጠት ስለራሳቸው ጥቅም ባለማሰብ እንዴት እንዳገለገሏቸው ሲናገር፡-

እንደምታውቁ፣ እያቈላመጥን ከቶ አልተናገርንም፣ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክር እያመካኘን በመጐምጀት አልሠራንም፤ የክርስቶስም ሐዋርያት እንደመሆናችን ልንከብድባችሁ ስንችል፣ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም። ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትከባከብ፣ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን፤ እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና። (1ተሰ. 2፥3-6)

- ሎሌ መሪ የእረኝነት ኀላፊነቱን የሚወጣ ነው

ጴጥሮስ “በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ” በማለት የሚመሩት ሕዝብ የእግዚአብሔር እንደሆነና መሪዎችም የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመጠበቅ ኀላፊነት እንዳለ ባቸው ያሳስባቸዋል። መሪነት የእረኝነት አገልግሎት ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ “መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል” (ዮሐ. 10፥11) ብሏል። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ስለሆነች እረኛዋ እርሱ ነው። እርሱ የእረኞች አለቃ ነው (1ጴጥ. 5፥4)። መሪዎችዋ ደግሞ የክርስቶስ ወኪል ሆነን የምንመራው እረኞች ነን። እውነተኛ እረኛ ለመንጋው የሚገደው ነው። መንጋውን ከሐሰተኛ አስተማሪዎች በመጠበቅ፣ ቅዱስ ቃሉን በመመገብ፣ በመንከባከብ ወደ ኋላ ከመመለስ፣ ተስፋ ከመቁረጥ በመጠበቅ በማሳደግ መሪዎች ኀላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል። እንደ እረኞች ሕዝቡን ከእነዚህ ዐይነት ተኩላዎች መጠበቅ ሲገባን፣ አጋልጠን ከሰጠን፣ ሕዝቡ ሲበተን ‘የት ደረሰ?’ የማንል ከሆነ፣ ሰው በሐሰት ትምህርት ተጠራርጎ ሲወሰድ፣ እውነትን በግልጽና በድፍረት በማስተማር መንጋውን ካልጠበቅን የእረኝነት አገልግሎታችንን እየተወጣን አይደለም።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የእረኝነት ኀላፊነታቸውን በሚገባ እንዲወጡ ሲያሳስባቸው በሐዋ. 20፥28-30 እንዲህ ብሏል፡-

በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ።

- ሎሌ መሪ የሚመራው ምሳሌነት ያለው ሕይወት በመኖር ነው

በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥3 ላይ ሐዋርያው ጴጥሮስ “ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኀይል አትግዙ” በማለት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሕዝባቸውን ሊመሩ የሚገባው መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በማስገደድ መሆን እንደሌለበት ያስተምራል። ሰዎች ምሳሌ አድርገው የሚከተሏቸው መሪዎች በሕይወታቸው መልካም ምስክርነት ያላቸውን ሰዎች ነው።

በአንደኛ ጢሞቴዎስ 3 እና በቲቶ 1 ላይ የተዘረዘሩት መሪ ለመሆን የሚያበቁ መሥፈርቶች ትኩረታቸው በባሕርይና መንፈሳዊ ሕይወት ጥራት ላይ ነው። ቲቶ 1፥6-9 እንዲህ ይላል፦

የማይነቀፍና የአንዲት ሚስት ባል የሚሆን፣ የሚያምኑም ልጆች ያሉት፣ ስለ መዳራትም ወይም ስለ አለ መታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር፣ ሹመው። ኤጲስ ቆጶስ፣ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ፣ የማይነ ቀፍ ሊሆን ይገባዋልና፤ የማይኮራ፣ የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ነውረኛ ረብ የማይወድ፣ ነገር ግን እንግዳ ተቀባይ፣ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፣ ጠንቃቃ፣ ጻድቅ፣ ቅዱስ፣ ራሱን የሚገዛ ይሁን፤ ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ፣ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና።

ጌታ ኢየሱስን በሕይወታችን ያላነገሥን መሪዎች የእርሱን ሕዝብ በእርሱ መንገድ መምራት አንችልም። ጌታን ለማገልገል የቆረጠ ልብ የሌለን መሪዎች፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደ አገልጋይ ሆኖ መምራት አንችልም። ‘እንደ መሪ ከጌታ ጋር ያለን ኅብረት ምን ይመስላል? ለጌታ ምን ያህል ራሳችንን ያስገዛን ነን?’ የሚሉት ጥያቄዎች የመሪነታችንን ብቃት ለመመዘን አስፈላጊዎች ናቸው። ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር ዓላማ መምራት የምንችለው ጌታችንን በሚገባ የምናውቅ መሪዎች ነን።

4. መሪው ቃሉን የሚያውቅና ሌሎችንም ለማስተማርና ለማቅናት የሚበቃ ሊሆን ይገባል

ቀደም ብለው በተገለጹት የሽማግሌዎች መመዘኛ መስፈርቶች፣ አገልግሎትን በተመለከተ የተሰጠው መመዘኛ “ለማስተማር የሚበቃ” የሚለው ነው። መሪ ሆነን የምናገለግል ሰዎች ቃሉን የምናውቅ፣ ለሌሎች ማስተማር የምንችል ልንሆን ይገባል። ቃሉን በሚገባ የማናውቅና ያልተማርን መሪዎች ሕዝቡን እንደ ቃሉ እንዴት ልንመራ እንችላለን? የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእረኝነት አገልግሎታችንን በሚገባ የምንወጣበት መንገድ አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ለሕዝባችን በመመገብ፣ እንደ ቃሉ የማይኖሩትን በመምከርና በመገሰጽ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ቃሉን ለሕዝቡ የመስበክ አደራውን ሲያሳስበው እንዲህ ነበር ያለው፦

ቃሉን ስበክ፣ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፣ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፣ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም። ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፣ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፣ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ። አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፣ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፣ አገልግሎትህን ፈጽም። (2ጢሞ. 4፥2-5)

እኛ መሪዎች ‘ሕዝቡ ምን መስማት ይወዳል? ምን ደስ ያሰኘዋል?’ እያልን ምእመኑ የሚፈልገውን እየሰበክንና እያሰበክን መምራት አይገባንም። ሙሉ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሐሳብ በማስተማር ፍጹምና ለበጎ ሥራ የተዘጋጁ መእምናንን ማፍራት ትልቁ ኀላፊነታችን ነው።

5. በሕያው እግዚአብሔር የሚመራ ተጠያቂነቱም በቅድሚያ ለእርሱ የሆነ ሊሆን ይገባል

መንፈሳዊ መሪነት የመሪነት ሁሉ ምንጭና መካተቻ የሆነውን አምላክ ፈቃድና ስልት ለመቀበል የነቃ መሪነት ነው።

በየማለዳው ያነቃኛል፤
በመማር ላይ እንዳለ ተማሪ ለመስማት፣
ጆሮዬን ያነቃዋል፤
ልዑል እግዚአብሔር ጆሮዬን ከፍቶታል፤
እኔም ዐመፀኛ አይደለሁም፤
ወደ ኋላም አላፈገፈግሁም። (ኢሳ. 50፥4-5)

ቃሉን ለማጥናትና በመንፈስ ቅዱስ ለመመራት ራሱን በጸሎት ያሠለጠነ ሆኖ መገኘት የብቁ ክርስቲያን መሪነት አንድ ገጽታ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ከመምረጡ በፊት በጸሎት ዐደረ። ስለዚህም “አንተ የሰጠኸኝ ሰዎች” ሊል ቻለ። ተጠያቂነቱም ከሁሉ በላይ ለአባቱ እንደ ሆነ ዐውቋልና “የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ አከበርሁህ” አለ።

6. መሪነት መሥዋዕት የሚያስከፍል መሆኑን ተረድቶ ራስን ለተገቢ መሥዋዕትነት ማዘጋጀት ያስፈልጋል

ስለ በጎቹ ራሱን የሰጠውን ጌታ የምንከተል መሪዎች ለመሥዋዕትነት ባይተዋሮች ልንሆን እንዴት ይቻለናል? እንደ ክርስቲያን መሪ በአገልግሎቱ ሂደት ውስጥ ቁርጠኛ ውሳኔ የሚጠይቁ በዚሁም ሳቢያ ምናልባት ዋጋ ሊያስከፍሉ የሚችሉ ወቅቶችን ልንሸሻቸው አይገባም። ይህ ሲባል መሥዋዕትነትን ለራስ ጀብዱ ሲባል የሚፈለግ ነገር አድርጎ መቍጠር ሳይሆን፣ ለምእመናን ጥቅም ሲባል በፍቅርና እውነትን ለመጠበቅ በጽኑነት የሚከፈል ክቡር ነገር እንደ ሆነ መረዳት ይጠቅመናል።

7. ከፍተኛ የሥራ ትጋት፣ ብርቱ ሸክምና ራእይ ያለው መሪነት ያሻል

እነዚህ ለእውነተኛ መሪነት ሁነኛ መለኪያ የሚሆኑ የተያያዙ ባሕርያት ናቸው። ጉዳይ ለማስፈጸም ብቻ የቆምን የሕዝብ መሪነትን ያለ በቂ ሸክምና ራእይ ከቦታ ወደ ቦታ የምናንከባልል ከሆንን የተከታዮቻችን ልብ ይወድቃል፤ ተባባሪነታቸውም ይቀንሳል፤ ተአማኒነታችንም እየደበዘዘ ይሄዳል።

ሐዋርያው ጳውሎስ "ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን ለመመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴ በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቈጥራለሁ" በማለቱ ይነዳው የነበረ ታላቅ ሸክምና ራእይ እንደ ነበረ ያመለክተናል። ሸክምና ራእይን በብርቱ ትጋት በሥራ ካልተረጐምን መሪነታችን ከግብ ደርሷል ማለት ያስቸግራል። ክርስቲያን መሪ ትጉሕ ሠራተኛ ነው።

8. ኅብረትን፣ አንድነትን መጠበቅ የክርስቲያን መሪ ኀላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል

ከአዲስ ኪዳን አጽማድ አስተሳሰቦች መካከል አንዱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጠራት አዲስ ማኅበረ ሰብ አንድነቷ መጠበቁ ነው። ለዚህም ብርቱ ማሳሰቢያዎች ተሰጥተዋል፤ "የመንፈስን አንድነት እንድንጠብቅ"፣ "በአንድ ሐሳብ እንድንስማማ"፣ "ተያይዘን እንድናድግ"፣ "አብረን እንድንሠራ፣ እንድንታነጽ" ተጠርተናል፤ ይህን የአንድነት ሂደትና የጥበቃውም ተግባር የሁሉ ኀላፊነት ቢሆንም የእኛ የመሪዎች ዋና ተግባር እንደ ሆነ ያስገነዝበናል።

9. መሪዎች ሌሎች መሪዎችን የሚያፈሩ ሊሆኑ ይገባል

ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ብዙ ጊዜውን ያጠፋው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበር። ብዙውን ሕዝብ ቢያገለግልም፣ እርሱ ሲሄድ ተልእኮውን የሚቀበሉትን ደቀ መዛሙርት ማዘጋጀት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ነበር። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳችንን በቃሉ ዕውቀትና በመሪነት ክኅሎቶች ከማሳደጋችን ጎን ለጎን ተተኪ የሚሆኑ መሪዎችን ማሠልጠንና ማዘጋጀትን እንደ ትልቅ ኀላፊነታችን ልናየው ይገባል። የወንጌል ሥራ እንዲሰፋ፣ ቤተ ክርስቲያን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየጠነከረችና እየሰፋች እንድትሄድ ተተኪ መሪዎች ባለማቋረጥ የማዘጋጀት ሥራን ማከናወን ይጠበቅብናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የምድር አገልግሎቱን ሊጨርስ በቀረበበት ወቅት ተተኪ አድርጎ ካዘጋጃቸው መሪዎች አንዱ ለነበረው ለጢሞቴዎስ እርሱም አደራ ተረካቢዎችን እንዲያዘጋጅ ሲያሳስበው እንዲህ ነበር ያለው:- "እንግዲህ ልጄ ሆይ፣ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" (2ጢሞ. 2፥1-2)

መሪዎች የያዝነውን ቦታ እንደያዝን ለረጅም ጊዜ ለመቆየት ከማሰብ ይልቅ፣ ሌሎች ተተኪ የሚሆኑ መሪዎችን በማዘጋጀትና በማብዛት ላይ ሊሆን ይገባል። ይህ ሲሆን ብቻችንን ሆነን ልንሠራ ከምንችለው ይልቅ እጅግ የላቀ ውጤታማ ሥራ እንድናከናውን መንገድ ይከፍታል፤ ለትውልዶች የሚተርፍ የበረከት ምክንያት እንሆናለን።

## VI. የወቅቱ ጉልሓን የአመራር ዝንፈቶች

1. ዋናውን የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ዋና አለማድረግ

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተመሠረተች የአማኞች ማኅበር ናት። የቤተ ክርስቲያን ራስም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም በሰጠን ትእዛዝ መሠረት ዋናው የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ሰዎችን ደቀ መዝሙር ማድረግ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማና ራእይዋ ይህንን ትኩረት ያደረገ ሊሆን ይገባል። ሌሎች ተግባሮችና እንቅስቃሴዎቿ ሁሉ ይህንን ተልእኮዋን እንድትፈጽም የሚያግዙ ሊሆኑ ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ሰዎችን ወደ ጌታ ኢየሱስ በማምጣት ደቀ መዛሙርት የማድረግ እና አካሉን ወደ አገልግሎት የማብቃት ላይ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል።

ዋናው ተልእኮ ሲዘነጋ ሌሎች ቀዳሚ ሆነው ይመጣሉ። ትልቅ ሕንጻ መገንባት፣ ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ፣ ኮንፈራንስ ማብዛት፣ የኀይል ኮንፈረንስ፣ የጥርመሳ ኮንፈረንስ፣ የከፍታ ኮንፈረንስ፣ የስኬት ኮንፈረንስ፣ ሰውን መሰብሰብ ብቻ ላይ ያለመ፣ ሰዎችን የተሰጡ የጌታ ተከታዮች፣ አገልጋዮች ከማድረግ ይልቅ፣ አድናቂዎች፣ ተሰብሳቢዎች ማድረግን ብቻ እንደ ግብ እየቈጠርን ነው። ስለዚህ ሕዝቡ በአንድ ቦታ ረግቶ መጽናትና ማገልገል ሳይሆን፣ ተሻሉ ወደ ተባሉ ኮንፈረንሶች ሲተም፣ ሲንከራተት፣ ሳይተክል፣ በእምነቱ ሳይጸና፣ ወደ አገልግሎትም ሳይደርስ ይቀራል።

2. የመሪዎች ጥሪና አመራረጥ ችግር

የአንድ አመራር ጥንካሬ የሚለካው በእያንዳንዱ አባል ችሎታና ጥንካሬ ነው። ስለ መሪዎችና አመራር ስናነሣ ጥንቃቄው መጀመር የሚኖርበት ከመሪዎች ጥቆማና አመራረጥ ወይም ጥሪ አለን ብለው የሚመጡትን ከመቀበል ላይ ነው። 'መሪዎች የምንመረጥበትና ወደ አመራር የምንመጣበት መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶችን አሟልቶ ነው?' ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። መስፈርቶቹም ቀደም ሲል ተዘርዝረዋል። ይህም ሆኖ ሳለ ዛሬ ወደ መሪነት ለማምጣት የምንጠቀምባቸው መለኪያዎች እጅግ አጠያያቂ እየሆኑ ነው። አንዳንዶቻችን ደፋር ስለሆንን፣ መናገር ስለምንችል፣ "ተፈላጊ ስጦታ" ስላለን፣ ገንዘብ መሰብሰብ ስለምንችል ብቻ ሕይወታችን ምንም ቢመስል ወደ መሪነት እንመጣለን። የሕይወት አቋማችን የማይመጥንም ቢሆን ባለንበት እንቀጥላለን። አንዳንዴ እንደ መሪ ግልጽ የሆነ የመንፈሳዊ ሕይወት ችግር እያለብን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛ ለመሪነት የማያበቃና የሚነቀፍ ሕይወት እየኖርንም በመሪነቱ እንቀጥላለን። ስለሆነም ሌሎችን ለማቅናት፣ ለመገሰጽ፣ በድፍረትም ቃሉን ለማስተማር አቅም እናጣለን።

ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ወደ መሪነት ከማምጣቷ በፊት እንደ ቃሉ ልትመዝናቸው ይገባል። ሰዎችን ገንዘብ ስለሚሰጡ፣ ወይም ብዙ ደጋፊና ወገን ስላላቸው፣ ወይም የተማሩ ስለሆኑ ብቻ የመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጥንካሬ ሳይታይ ወደ መሪነት ማምጣት ጉዳቱ ከፍተኛ ነው። የሕይወት ጥራት

መስፈርትን ቸል ያለው ይህ ዐይነቱ የመሪዎች አመራረጥ ቤተ ክርስቲያንን ሥጋዊ ወደሆነ አመራር እንድታጋድል አድርጓታል።

3. የአመራር ብቃት ችግር

ብቃት ያለው ክርስቲያናዊ አመራር ግብ ተኮር፣ ዓላማ መር፣ አሳታፊ፣ ተግባቦታዊ፣ ምሳሌያዊ እና የእግዚአብሔርን የተገለጠ ፈቃድ የተከተለ ነው። እነዚህ መሠረታውያን ከታጡ ወይም ከተዛነፉ መሪነት አደጋ ላይ ይወድቃል። በአሁኑ ጊዜ መስተካከል የሚገባቸው ትክክለኛ ያልሆኑ የሕይወት አካሄዶች፣ የአመራር ግድፈቶችና የአስተምህሮ ዝንፈቶች በመካከላችን በሰፊው ይታያሉ። የመጀመሪያው ጉዳይ በአመራር ላይ የሚታዩ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ በግልጽነትና በእውነት ልንወያይ እንደሚገባ አስፈላጊም አጣዳፊም ሆኖ መገኘቱ ነው። ብዙዎች እንደሚገልጹት ዛሬ በመካከላችን የሚታዩ ዐበይት የሕይወትም ሆነ የአስተምህሮ ችግሮች የመንፈሳዊነት፣ የአመራር ብቃትና በእውነት ላይ አቋም የማጣት ክፍተቶች ሆነው ይታያሉ። የእነዚህ ችግሮቻችን መሠረታቸው ደግሞ ትክክለኛ የሆነ የአገልጋይ መሪ አመራር መጥፋት ነው። የብዙዎቻችን ከጥሪያችን አንሥቶ የመሪነት ጸጋ ያለን የመሆኑና ያለመሆኑ፣ ዕውቀታችንና የመሪነት አቅማችን፣ የአመራር ችሎታችንና ደካማ ጎናችን የአገልግሎት ልምዳችንና አመራረጣችን ሳይቀር መፈተሽ የሚገባው ሆኖ ይገኛል። የአንዳንዶቻችን ለአገልግሎት አለመመጠንና አቅም ማነስ በአመራራችን ብቃት ማጣት የሚታየው ቀውስ የቤተ ክርስቲያንን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ሰንካላ ሲያደርገው ይታያል። ስለሆነም የዕውቀትና የልምድ ማነስ በእግዚአብሔር ቃልም ሆነ በሌላውም የትምህርት ዘርፍ ያሉብን ውስንነት በአመራሩ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማስከተሉ አይቀርም።

በቲቶ ምዕራፍ አንድም ሆነ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ሦስት ላይ እንደምናየው ለመሪዎች የተሰጠው መስፈርት ከመንፈሳዊ ሕይወት በተጨማሪ "ለማስተማር የሚበቃ" የሚል ነው። ለማስተማር የሚበቃ ለመሆን ቃሉን ማወቅና ቃሉንም በሕይወት መለማመድ ይጠይቃል። የመሪነት ብቃት የተሳሳተ አስተምህሮንና የተበላሸ ሕይወትን ከሩቅ የማስተዋል፣ የሚፈተሽና አስፈላጊ አቋም ላይ የመድረስ ርምጃም የመውሰድ ችሎታን ይጨምራል፤ ይህ በሌለበት ሁኔታ ምእመናን ለክፉ ትምህርትና ባሕርይ ይዳረጋሉ። ቃሉን በሚገባ የሚያውቁ፣ እንደ ቃሉ የሚኖሩ፣ ለሌሎችም በግልጽና በድፍረት የሚያስተምሩ መሪዎች እጥረት በአሁኑ ጊዜ ጎልቶ ለሚታየው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የአስተምህሮ ዝንፈት ዋና ምክንያት ነው።

ዛሬ አንዳንዶቻችን የእግዚአብሔርን እውነት በአግባቡ ሳንረዳ ወይም ሳንማር ወይም ጥሪ ሳይኖረን ራሳችንን የወንጌል ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎች፣ መጋቢዎች፣ ባለ ራእይና ነቢያት አድርገን የሾምንና የቀባን በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ አደጋ ጋርጠናል።

ከዚህም ጋር ባልተናነሰ መንገድ ለችግሮቻችን ሌላው ምንጭ ደግሞ የአንዳንዶቻችን ስሜትና ቅናት የሸፈነው የአመራር ዘይቤና ባሕርይ ነው። ከሌሎች ጋር ተግባብቶና ተባብሮ የመሥራት ዕውቀትና ልምድ ማነስ የሚፈጠሩ ችግሮችን በአግባቡ የመፍታት ችሎታችን ዝቅተኛ መሆንና የአመራር ግልጽነት ማጣት በአገልግሎታችን ላይ እያመጣ ያለው በጎ ያልሆነ ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ይህም በብዙ ስፍራዎች በግልጽ የሚታይ ነው። ሁላችንም በምንገኝባቸው በበርካታ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ችግር ነገርን በጋራ ተወያይቶ የመወሰን ባህል፣ የተግባቦት ክኅሎት፣ ራስን የመግዛትና በመከባበር የመነጋገር ልምድ ማጣት ሁኔታዎች ናቸው። ይህ የአንድነት መንፈስን የሚያጠፋና የአመራራችንን ሂደት የአገልግሎት አቅጣጫ የሚያስተን ይሆናል። የዚህ ድክመትና መዘበራረቅ የቤተ ክርስቲያኖቻችንን አገልግሎትና ዕድገት ወደ ኋላ ሲጎትተው ይታያል። ከዚህም ባሻገር ብዙዎቻችን ስለ አመራር ምንነትና የጋራ አመራር መርሕ ምን መሆን እንዳለበት ከእግዚአብሔር ቃልና ከልምድም አገናዝቦ የማየት በቂ ልምድ ስለሌለን በአፈጻጸም ላይ አላስፈላጊ ወደ ሆነ ውዝግብ ውስጥ እንገባና ውድ ጊዜና መልካም ዕድሎች በከንቱ ማለፋቸውን እንገነዘባለን።

4. ከመሪነት ጋር የሚመጣውን ኀላፊነትንና ተጠያቂነትን መዘንጋት

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የያዝነው ቦታ ከጌታ በአደራ የተቀበልነውና፣ በያዝነውም ቦታ እንዴት እንዳገለገልን በእርሱ ፊት ቀርበን መልስ የምንሰጥበት ኀላፊነት ነው። ጌታ በሉቃስ ወንጌል በምሳሌ እንዳስተማረው የተሰጠንን ኀላፊነት በሚገባ የተወጣን፣ ከእርሱ ዘንድ ሽልማትን ስንቀበል፣ የተሰጠንን ኀላፊነት በመዘንጋት ግን ለራሳችን ምቾትና ምኞት የምንሮጥ ከእርሱ ፍርድ ይጠብቀናል፤ "ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፣ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል።" (ሉቃ. 12፥48)

ሥልጣን ማዕረግን የምንወድ፣ ከእርሱ ጋር አብሮ የሚመጣው ኀላፊነት ግን የማይገደን/የማንወጣ መሪዎችን አለን። የቤተ ክርስቲያን ባለቤት ክርስቶስ ነው፤ እኛ አገልጋዮችና የእርሱ ባሪያዎች ነን። ለምናደርገው ሁሉ አንድ ቀን በፊቱ መልስ እንሰጣለን።

5. በአመራሩና በምእመናኑ መካከል ያለ የግንኙነት ክፍተት

በአመራር ላይ በምንገኘውና በምእመኑ መካከል የቅርብ ግንኙነትና መተዋወቅ አለመኖር ሌላው ዋና ችግር ነው። ይህ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ለሚታየው የአመራር ክፍተትና የአስተምህሮት ዝንፈት ዐይነተኛ ምክንያት ነው። ይህ የሚያጋጥመው አብዛኛውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምእመኑን የሚያሳትፍ ግልጽ የሆነ ውይይትና ምክክር የማይታይ ሆኖ ሲገኝ ነው። በተጨማሪም፣ በዕውቀታቸውና በልምዳቸው ለምእመኑ አጠቃላይ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ሊያደርጉ የሚችሉትንም አውቆ ለመጠቀም አለመቻል ነው። በበርካታ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረግ የሚችሉና ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ክርስቲያኖች ማንነታቸው ታውቆ ተገቢው የአገልግሎት ስፍራ ተሰጥቷቸው በተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሳተፉ ማድረግ የተለመደ አይደለም። መሪዎች አንዳንዴ በራሳችን እምነት ከማጣት እንዲሁም በጥያቄ ወይም በውይይት ሊነሡ ይችላሉ ብለን ከምንሰጋባቸው አሳሳቢ ጉዳዮች የተነሣ ዋና ዋና በሆኑ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ ምእመኑንም ሆነ ሌሎችን በሐሳብ ሊረዱ የሚችሉትን በግልጽነት እንዲወያዩ ማድረግ እንፈራለን። ግልጽነቱ ግራጫ፣ ተጠያቂነቱ ደግሞ ልል ሆኖ ይታያል።

ምንም እንኳን አብዛኛው ምእመናን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትንና አመራርን፣ የገንዘብ አጠቃቀምን፣ የአገሊጋዮች አመራረጥና ስምሪትን፣ ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ዕድገትንና ልማትን በሚመለከቱ ዐበይት ጉዳዮች ላይ ግልጽና እውነተኛ ውይይት እንዲደረግና ተሳትፎ እንዲኖረው የሚፈልግ

ቢሆንም የብዙዎቻችን የቤተ ክርስቲያን መድረክ ለዚህ ዐይነቱ ተሳትፎ በቂ ዕድል የሚሰጥ አይደለም። በየደረጃው እንደ አማኙ ብስለት የምእመኑ ተሳትፎ ማድረግ አስፈላጊና አግባብ መሆን ብቻ ሳይሆን የወንጌል አገልግሎት ሥራውንም የበለጠ ያግዛል፤ በቤተ ክርስቲያን የሚፈጠሩ የአመራር ችግሮችንም በቀላሉ ለመፍታት ያስችላል። ምእመኑ በዕውቀትና በባለቤትነት መንፈስ የሚሳተፍ ሲሆን፣ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ያመጣል፤ የተሻለ መቀራረብንና መተማመንን ይፈጥራል። ይሁን እንጂ አሁን እንደሚታየው ይህን በድፍረት የምናስተናግድ ለግልጽነትና ለእውነት በራችን የተከፈተ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅግ ጥቂት ሆነን እንገኛለን፤ የምእመን ተሳትፎዎች ለይስሙላ ብቻ የሚደረጉ ሆነው ይታያሉ።

6. መሪ ሊሆኑ የሚችሉና የሚገባቸው ሰዎች ከአገልግሎት መሸሽ

ጸጋው፣ ዕውቀቱ ችሎታ ያላቸው መሪ ሊሆኑ የሚገባቸው ሰዎች ችግሮችንና ጭቅጭቆችን በመፍራት ወይም ዋጋ ላለመክፈል በመፈለግ ከመሪነት ሲሸሹ ብቃት የሌላቸው፣ መሪነቱን ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል የሚፈልጉ ሰዎች ይይዙታል፤ በዚህም ቤተ ክርስቲያን ትጎዳለች። ከሩቅ ሆነው እየተቹ ነገር ግን ውስጥ ገብተው ለመለወጥ የማይፈልጉ ሰዎች ብዙ ናቸው። ሊያገለግሉ የሚችሉባቸውን ቤተ ክርስቲያናቸውን እየተዉ ምቾት ወዳለባቸው፣ ብዙም ኀላፊነትን ወደማይጠይቁ ቤተ ክርስቲያኖች በመሄድ በተቀማጭነት (የእሑድ ደንበኛነት) የሚኖሩ አሉ።

በአገራችን ያለው የኑሮና የኢኮኖሚ ሁኔታ ብዙ አገልጋዮችን በስፋት ሊያገለግሉ ከሚችሉበት መስክ እያፈናቀለ ወደ ውጭ አገራት እየሰደደ እንዳለ ይታወቃል። የነገረ መለኮት ተማሪዎችም ለመማር ከሄዱባቸው አገሮች ተመልሰው ለመምጣት ቁርጠኛ ውሳኔ የሚጠይቃቸው ሆኗል። በተለያየ ረገድ ልዩ ልዩ ሥልጠና፣ ችሎታና ሙያ ያላቸው ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ባያሌው መፍለሳቸውም ግልጽ ነው። በዚህም ምክንያት ብዙ የበሰሉ አገልጋዮች እያጣን ነው።

ውጪ ወጥተን ለመኖርስ ስናስብ፣ ‘በርግጥ እዚያ አስፈልጋለሁ? ጸጋዬንና ዕውቀቴን በሚገባ የምጠቀምበት ከአገር ውጪ ነውን?’ ብለን መጠየቅ ትልቅ የኀላፊነት ርምጃ ነው። ለአገልግሎት ስንጠራ ዋጋ ለመክፈል፣ ለመሥዋዕትነትም ጭምር እንደተጠራን የታወቀ ነው። ለጊዜው ከሚገኝ ምቾትና ደስታ ይልቅ ጌታንና ሕዝቡን በተሰጠን ጸጋ ማገልገል ዋጋው በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ነው። የተሰጠንን ጸጋ ቀብረን፣ ከኀላፊነት ሸሽተን በሩቅ ሆነን እየተቸን መኖር ከተጠያቂነት አያድነንም።

7. ግጭቶችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መንገድ መፍታት አለመቻል

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሡ ግጭቶች የተለያዩ መንስኤዎች ሊኖራቸው ይችላል። ከእነዚህ ግጭቶች የስንቶቹ መነሻ በትክክል ስለ ወንጌል በመቆርቆር፣ ሐሰተኛ ትምህርትን በመቃወም፣ በቅድስና ጉዳይ ጋር በተገናኘ ይሆን? ይህ ጥናትን የሚሻ ጉዳይ ነው።

ብዙ ግጭቶች ግን ከእኛ ከመሪዎች ግትርነት የተነሣ፣ ችግርን ተወያይቶ መፍታት ካለመቻል፣ ለጥቅም ወይም ለሥልጣን በሚደረግ ሽኩቻ፣ ቡድንን በማደራጀት፣ ደጋፊን በማሰባሰብ፣ በዘር በጓደኝነት፣ በጥቅም በመተሳሰር፣ ከልክ በላይ ባበጠ ‘እኔነት’ ምክንያት ነው። ትሕትና የጎደለን መሪዎች፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ የምንል፣ ግትርነታችን በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ግምት ውስጥ የማናስገባ፣ ብናውቅም ግድ የሌለን፣ ለእርቅ በር የማንከፍት መሪዎች ስንበዛ ግጭቶች ይፋፋማሉ። አጥፍቶ ይቅርታ መጠየቅ አለመቻል፣ እውነተኛ ንስሓ ለመግባት ፈቃደኛ አለመሆን፣ ከዛ ይልቅ ጥፋትን ለመሸፈን ሌላ ጥፋት ውስጥ መግባት ይታያል። በወንጌል ጉዳይ ወይም በጠቃሚ ጉዳዮች ላይ ሊጠፋ የሚገባው ጊዜና ገንዘብ፣ በጭቅጭቅ፣ በሙግት፣ በማያልቅ ስብሰባ ይባክናል። የምእመናን ልብ ይሰበራል፤ እንመራዋለን የምንለው ሕዝብ ለእኛ ይጨነቃል፣ እኛን ይታዘባል ወይም አኩርፎ ወደ ሌላ ይሄዳል። የጌታም ስም፣ የቤተ ክርስቲያንም ስም በዓለም ዘንድ ይሰደባል፤ ለወንጌል ሥራም እንቅፋት ይመጣል።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ፡-

ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን? ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን? በዓለምስ ላይ ብትፈርዱ ከሁሉ ይልቅ ትንሽ ስለሚሆን ነገር ልትፈርዱ አትበቁምን? . . .በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል፥ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን? እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ፣ ያውም ወንድሞቻችሁን። (1ቆሮ. 6፥1-8)

ይህ በግልጽ የተቀመጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ በብዙዎቻችን እየተጣሰ፣ በየፍርድ ቤቱና በየመንግሥት ቢሮ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ መታየት ከጀመረ ከርሟል። በዚህም ምክንያት እምነታችንን ለሚቃወሙ፣ መጥፎ ነገር ስለ እኛ ማውራት የሚያስችላቸውን በቂ ምክንያት እያቀበልን እንገኛለን። ለወንጌልም መስፋት እንቅፋት እየሆንን ነው። በመካከል የሚነሡ ግጭቶች፣ የሐሳብ ልዩነቶች በጸሎት፣ በሰከነ ውይይት፣ በእውነተኛ መወቃቀስ፣ በተገቢ ተግሣጽ፣ እርስ በርስ በመማማር፣ በወንድሞች መካከል በሚደረግ ልባዊ እርቅ መፈታት ይገባቸዋል።

8. አፍራሽ የብሔር አስተሳሰብና ወገንተኝነት

በወገንና በዘር ልዩነት ምክንያት ዓለም በትልቅ ችግር ላይ እንደሆነች ይታወቃል። ቤተ ክርስቲያን ጨውና ብርሃን የመሆን አገልግሎቷን በሚገባ መወጣት ስላልቻለች፣ በዓለም ላይ ተጽእኖ ማድረግ የሚገባትን ያህል ሳታደርግ በፈንታው ግን የዓለም ተጽእኖ እየተጫናት እንደ ሆነ በግልጽ ይታያል።

እስከ ቤተ ክርስቲያን አመራር ድረስ ወጥቶ የሚታየው፣ አንዳንዴም ከላይ ወደ ታች እያመረቀዘ የሚወርደው ችግር የግለ ሰቡ የዘር ወይም ክልላዊ

ማንነት ከሰማያዊው ሰብእና በላይ ደምቆ መገኘትና ለልዩነትም ምክንያት መሆኑ ነው። ቁመናንና ማንነትን ከቀዳሚውና ከሕያው እውነት በመቅዳት ፈንታ ከማኅበራዊ ተመራማሪዎች ወይም ፖለቲከኞች በልክ እያሰፉ ለብሶ ሌሎችን ማልበስ ሌላ የልዩነት አሰላለፍ ማምጣት ነው። ቅዱሳንን ከክርስቶስ ደም ይልቅ በዘር ሐረግ፣ በወንዝና በአካባቢ፣ በተመሳሳይ የኑሮ ደረጃና ማዕረግ እንዲሰበሰቡ መተው ወይም ግንባር ቀደም ሆኖ መገኘት በብዙ ቤተ እምነቶቻችን አካባቢ የሚታይ ቀውስ ነው።

የፖለቲካ አስተሳሰብና ልዩነት አመራሩን ማቃወሳቸው አንድ ችግር ነው። ገሚሱ አንዱን ጎራ፣ ሌላው ደግሞ ሌላውን ይደግፍና የእግዚአብሔር መንግሥት አውድማ የምድራዊ አመለካከቶች መናኸሪያና መጋደያ እየሆነ ነው።

በትልቁና በከበረው አካላዊ አንድነት ሥር በመሆን ፈንታ በንዑሳን ማንነት ሥር መተገን፣ አልፎም ተኪ የሆኑ ኅብረቶችን በዚሁ አሟላጭ ዓላማ ሥር ማስተባበር አንዱ የአመራር ቀውስ ነው። ግለ ሰቦች በዚህ ሁኔታ ቢገኙ የተናጠል ችግር እንደ ሆነ ተወስዶ የተናጠል ርምጃ ይወሰዳል፤ ክስተቱ ግን ዓላማ መር የሆነና ቡድኖችንና ኅብረቶችን ያቀፈ ነው።

የችግሩ ጠንሳሽ መሆን አንዱ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ እንደ ጎርፍ በርካቶችን እንዳያጥለቀልቅ ነቅተን አለመከላከል ወይም አለመገደብ ነው። 'እኔ ካላመጣሁት ምን ቸገረኝ!' 'በራሱ የመጣን እንደ አማጣጡ ማስተናገድ ነው' ወይም 'ያልጠሩት ናፍቆት!' ሆኖ ማኅበርን አውኳል፤ የከበረውንም የአንድነት ምክንያት ሸርሽሯል። በዙሪያችን የሚሆነው ነገር በቤተ ክርስቲያን ያለንበት ሁኔታ ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርግ ጥርጥር የለውም። ነገር ግን ተጽእኖው እስከምን ደረሰ ነው? አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ከምንመራ ይልቅ በዓለም ያየነውን እንደወረደ ተግባራዊ ማድረግን ስናስቀድም እንታያለን። ሰው ከዓለም ሸሽቶ የመጣውን ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል እያስተናገደች ነው? ከሰማያዊ አጀንዳ በላይ ምድራዊ አጀንዳ የምናራምድስ ስንቶች ነን?

9. መሪነትን (እረኝነትን) ለማገልገል ሳይሆን ለግል መገልገያነት መዋል

ሎሌ መሪ የእረኝነት ኀላፊነቱን የሚወጣ ነው። ጴጥሮስ በተለያየ ቦታ ተበትነው ለነበሩ ቅዱሳን አብያተ ክርስቲያናት መሪ ለነበሩ ሽማግሌዎች ሲጽፍ "በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ" በማለት የሚመሩት ሕዝብ የእግዚአብሔር እንደ ሆነና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመጠበቅ ኀላፊነታቸውን ያሳስባቸዋል። መሪነት የእረኝነት አገልግሎት ነው።

በአንዳንድ ሁኔታዎች እንደሚታየውና ብዙዎችም እንደሚገልጹት አንዳንዶቻችን አብዝተን የምንታገለውና የምንጋደለው ለእግዚአብሔር የቃሉ እውነት፣ ክብርና ሥራ መሆኑ ቀርቶ የአገልግሎት ቦታችንን ከዚህም ጋር የተያያዘውን አዳጉል ጥቅም ለማቆየት ሆኖ መታየቱ ብዙዎችን የሚያሳስብ ጉዳይ ሆኗል። ጥቂት የማንባል መሪዎችም ባለ ራእዮች ሳንሆን ባለ ኑሮዎች፣ ባለ አደራዎች ሳንሆን አደራ በሎች ሆነናል።

'ሰው እንዳይሄድ' እየተባለ ዘመኑ የሚያራግፍብንን አስተሳሰቦች በመንፈሳዊ ቋንቋ ማቅረብና የሕዝብን ሐሳብ እያሟሹ ማደናገር የተለመደ ሆኗል። "መምራት ለጥቅም" በሚል መርሕ የሚካሄደው እውነተኛ አገልግሎት ሳይሆን ጥቅምን ለማግኘት ያነጣጠረ የተጠና አካሄድ ገዢ ሆኖ ይታያል። መሪነት ከፍታ የሆነበት ይህ ግብ ራሱን ተአማኒ ለማድረግ የቃሉን እውነት ያደበዝዛል፣ ይሸራርፋል፣ የማይጮኽበት ቦታም ያስጮኸዋል። በውጪ ያለው የካፒታሊስት አስተሳሰብ ሰውን ውድድር ውስጥ ከቶት ኀላፊነት በጎደለውና ከጽድቅ እጅግ በወረደ ሁኔታ እንዲሠራ ሲያደርገው ስሙ የተጠራብን አማኞችም ከተመልካች አድናቂ፣ ከአድናቂ ደግሞ ተፎካካሪ ሆኖ በመለወጥ ሃይማኖትን የውድድሩ ማሸነፊያ ጥሩ አቋራጭ እያደረግነው ነው።

"ኀጢአተኛ በፊቱ የተናቀ" (መዝ. 15፥4) የሚለው "ኀጢአተኛ በፊቱ የከበረ" በሚለው የተተካበት ዘመን ነው። ገንዘብና ውጪያዊው ስኬትም በስውር የተቀመጡ የተልእኮ እሴቶች እስኪመስሉ መሪነት እነዚህን ነባራውያን ያማከለ ሆኗል። ይህ ዘመን የገንዘብ የስበት ኀይል ጉልበት የታየበት፣ ለእውነተኛውም ተልእኮ ያለን መሠጠት የተፈተነበት ዘመን ነው። መባ መሰብሰቢያው ተዟዟሪ ኪስ በሆነበት በዚህ ጊዜ የከልካይ መጥፋት ለመሪነቱ ቁልቁል መሄድ ዐይነተኛ ማሳያ ነው።

ወንጌል አቅም ማከማቺያ፣ ሕዝብ ደግሞ የገቢ ምንጭ በሆነበት ሁኔታ እውነተኛ እረኝነትን ማሰብ ፈጽሞ የዋህነት ነው። በጎች ለጌታ ሳይሆን ለሚሰጡት ጥቅም እየተወደዱ ሲታገዱ፣ አንዳንዶችም ሲቀለቡ ይታያል። ጥቅማቸው ብቻ እየታሰበም ንጽሕናቸውና ጤንነታቸው ትኩረት ተነፍጎታል፤ በዚህም አካሄድ ለጌታ ማቅረብ ሳይሆን የራስ ዓላማ ጋር ማስቀረት፣ ጥገኛ ማድረግና ማገልገል የተለመዱ ተግባራት ናቸው። ከእግዚአብሔር ሕዝብ በተለያየ መንገድ ገንዘብ የምንዘርፍ ለመንጋው ግን ምንም ርኅራኄ የሌለን በተለያየ የሹመት ስም በምእመናን ላይ የምንሠለጥን ጮሌዎች በዝተናል።

የእረኞች አለቃ መቼ እንደሚመጣ የሚታሰብበት፣ የሚጠበቅበትና አልፎም የሚፈራበት ጊዜ እንደዘበት እየተረሳ ተመልካችና ፈራጅ የሌለ በሚመስል ሁኔታ በረቱ ጌታ ጌታን ማለት ትቶ ሰው ሰው፣ ገንዘብ ገንዘብ እያለ መዓዛው ሌላውን ሊጠራ ቀርቶ ጠረኑ ያለውንም እያራቀው መጥቷል። ይህንንም ለመለወጥ የሚነሣ እየተወቀሰና እየተወገዘ ጥግ መያዙ የአመራር ቀውስ መንሰራፋቱን ማሳያ ነው። ትሩፋን እንዲበረታቱና ታጥቀው በመነሣት ለውጥ እንዲያመጡም ፈጣንና ቁርጠኛ አቋም መያዝ፣ ጨክኖ ማራመድም ያሻል።

ቤተ ክርስቲያናንንም እንደ ገዛ ድርጅታችን የምናስተዳድር መሪዎችም ብቅ ብቅ እያልን ነው። ከዚያም መንጋውን አኮናትረን ወይም ለሌላ ሽጠን የምንሄድ "መጋቢዎችም" እንዳለን ይሰማል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን እንደ ራስ ንብረት አድርጎ ማሰብ፣ ከቃሉ ጋር የሚጋጭ ትልቅ የመሪነት ንቅዘት ምልክት ነው።

በዘመናችን ለሥልጣን የምንጋፋ፣ ጥቅማችንን ለማስጠበቅ ስንል የእግዚአብሔርን መንጋ የምናምስ፣ ያለንን የምንሰጥ ሳንሆን ከመንጋው ለመውሰድ ወደ ኋላ የማንል፣ በቃኘን የማናውቅ በ'ጌታ ባረከኝ' ስም ሀብትን ያለ አግባብ የምንሰበስብ መሪዎች እየታየን ነው። ከእግዚአብሔር ሕዝብ በተለያየ መንገድ ገንዘብ የምንዘርፍ፣ ከሚገባን በላይ የምንወስድ፣ ራሳችንን ያበለጸግን፣ ለመንጋው ግን ምንም ርኅራኄ የሌለን፣ የተለያየ የሥልጣን ስም ለራሳችን እየሰጠን "የምናገለግል" አለን። ይህ እንኳን በጌታ ቤት ላለ መሪ በዓለምም እንኳ ላሉት የሚያስነውር ሥራ በእኛ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘንድ መታየቱ የሚያሳዝን ነው። ቃሉ ግን እንደሚያስተምረን መሪዎች ትኩረታችንን ማድረግ የሚገባን በምናገኘው ጥቅም ላይ ሳይሆን ለመንጋው በምንሰጠው አገልግሎት ላይ መሆን አለበት።

10. በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ከመፈለግ በላይ በሰው ተቀባይነትን ለማግኘት መሻት

መሪዎች ምንጊዜም ከእግዚአብሔር ሥራና እውነት በላይ ለኑሮአችን ወይም ለቦታችን አብዝተን የምንጨነቅ ወይም ሰዎችን የምንፈራ ከሆነ የእግዚአብሔርን ዐደራ መጣል ብቻ ሳይሆን በአካሄዳችንና በአገልግሎታችን፣ በቤተ ክርስቲያን የመንፈስ አንድነትና በምእመኑ ዕድገት ላይ በጎ ያልሆነ ተጽእኖ ማድረጋችን አይቀርም። አገልጋይ ምን ጊዜም ሕይወቱንና እምነቱን ቦታውን የማጣት ስጋት ሊገባው አይገባም። በታወቀ እውነት ላይ ይሉኝታ ወይም ቦታን የማጣት ሥጋትና እውነትን በመናገር ግጭት ሊመጣ ይችላል በሚል የሰው ፍርሃት አመራርን ሲሸፍነውና ዝምታና እውነትን ከመናገር መቆጠብ የአመራር ዘይቤ እየሆነ ሲመጣ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት መቀጨጭ ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን አንድነትና ኅብረትም እየተዳከመ ይመጣል፤ ሐሜት ይጨምራል፤ መከፋፈልንም ያመጣል። አንዳንዱም ትዕግሥት በማጣት ቤተ ክርስቲያኑን ለቆ ይወጣል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄና ገላትያ ሰዎች እንዲህ ጽፏል፡-

"ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥ እንዲሁ እንናገራለን፥ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም።" (1ተሰ. 2፥4)

"ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።" (ገላ. 1፥10)

ሕዝብ የተቀበለው፣ ብዙዎች የሚስማሙበት ወይም የሚበዙት የተሸነፉለትን ነገር፣ አቋም ወይም አመለካከት አድርጎ መያዝ ይታያል። እንዲህ ዐይነቱ የአስተሳሰብም ሆነ የሕይወት መርሕ መለኪያን ከሕያው ቃል በመቅዳት ፈንታ የጊዜውን ማዕበል እየጠበቁ የመቅዘፊያውን አቅጣጫ መቀየር ዓላማ መርና ግብ ተኮር ተልእኮን ይንዳል። ከፉውን ድርጊት በመግለጥ ፈንታ በክፉው እየተሳቡና መብራትን እያጠፉ መምጣት የአንድ ጊዜ ወይም የአንድ ቦታ ክስተት አይደለም። ዘወትር የሚታይ የብዙ ስፍራ ገጠመኝ እንጂ።

ተቀባይነት በቀደመበት እውነት ይበረዛል፤ ዓላማ ይከለሳል፤ ግብ ይጣሳል። ወንጌል ከዘመናት በፊት ታቅዶ፣ ዋጋ ተተምኖበትና ተከፍሎበት የመጣ፣ ያመነጨውና ዳር ያደረሰውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። ይህን የከበረን ተልእኮም ከሰው ሙገሳ ለማግኘትና ሰዋዊ ፍላጎት ለማርካት መበረዝና ማውረድ ፈጽሞ ተገቢ አይደለም።

11. ተተኪ መሪዎችን በማዘጋጀት ላይ ትኩረት አለመስጠት

ቀደም ብሎ እንዳየነው ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ብዙ ጊዜውን ያጠፋው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበር። ብዙውን ሕዝብ በተለያየ ቦታ ቢያገለግልም፣ ዋና ትኩረቱ እርሱ ሲሄድ ተልእኮውን የሚቀበሉትን ደቀ መዛሙርትን በማዘጋጀት ላይ ነበር። ዛሬም ያለን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተተኪ የሚሆኑ መሪዎችን ማሠልጠንና ማዘጋጀትን እንደ ትልቅ ኀላፊነታችን ልናየው ይገባል። የወንጌል ሥራ እንዲሰፋ፣ ቤተ ክርስቲያን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየጠነከረችና እየሰፋች እንድትሄድ ተተኪ መሪዎች ባለማቋረጥ የማዘጋጀት ኀላፊነት አለብን።

ሐዋሪያው ጳውሎስ በአገልግሎት ዘመኑ ሌሎች ተተኪ መሪዎችን ያሠለጥን ነበር። እርሱ የምድር አገልግሎቱን ሲጨርስ የወንጌሉን ሥራ የሚረከቡ ከዚያም ለሌሎች የሚያስረክቡ ሰዎችን ያዘጋጅ ነበር። ተተኪ አድርጎ ካዘጋጃቸው መሪዎች አንዱ ለነበረው ለጢሞቴዎስ እርሱም አደራ ተረካቢዎችን እንዲያዘጋጅ ሲያሳስበው እንዲህ ነበር ያለው፡- "እንግዲህ፥ ልጄ ሆይ፣ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ" (2ጢሞ. 2፥1-2)።

መሪዎች የያዝነውን ቦታ እንደያዝን ለረጅም ጊዜ ለመቆየት ከማሰብ ይልቅ ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው ሌሎች ተተኪ የሚሆኑ ሰዎችን በማዘጋጀት ራሳችንን ማብዛት ላይ ሊሆን ያሻል። ይህ ሲሆን ብቻችንን ሆነን ሊንሠራ ከምንችለው እጅግ የላቀ ውጤታማ ሥራ እንድንሠራ መንገድ ይከፍታል፤ ለትውልዶች የሚተርፍ በረከትም ምክንያት እንሆናለን። መሪዎች ሌሎችን የማናፈራ እኛ ብቻ ተፈላጊ ሆነን እንድንቆይ በማሰብ፣ ሊያድጉ የሚችሉ መሪዎችን የምንገፋ፣ በዙሪያችን እሺ ባዮችን ብቻ የምናሰባስብ ከሆንን ለሚቀጥለው ትውልድ እያሰብን አይደለም። ከማባዛት ይልቅ መቀነስን፣ ለብቻ መቅረትን እናመጣለን።

ባለንበት ዘመን ወንጌሉ ትርጉም እንዳያጣ ጊዜውንም ለመዋጀት እንዲቻል በተለይ ለወጣቱ ትኩረት መስጠት፣ በቃሉ ማሳደግ፣ ለአመራር ማዘጋጀትና ማሳተፍ ከምንጊዜውም ይልቅ አጣዳፊና ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኖ ይታያል። ወጣቱም ሆነ በአጠቃላይ ምእመኑ የወቅቱን ተግዳሮት እየተረዳ፣ በአሸናፊነት ለማለፍ የሚያስችሉትን የጊዜውን መልእክት ማዘጋጀትም አስፈላጊ ይሆናል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን በመፍራት የሚመራ የሰከነ አመራርን ይጠይቃል።

## VII. የመፍትሔ ሐሳቦች

1. የቤተ ክርስቲያን ዋና ተልእኮዋ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት እንደመሆኑ ሌሎች እንቅስቃሴዎቿም ይህንን ዋና ዓላማ የሚያራምዱ ሊሆኑ ይገባል። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስልታቸውም ሆነ አደረጃጀታቸው ለዚህ ተፈጻሚነት የሚጠቅም ሆኖ መዘርጋትን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

2. ቤተ ክርስቲያን ወደ መሪነት የምታመጣቸው ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሊሆኑ ይገባል። አሁን በመሪነት ላይ ያሉም ሕይወታቸውን በመመርመር፣ ጥሪያቸውንም በማረጋገጥ፣ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ዐይነት መሪዎች ለመሆን መትጋት ያሻቸዋል፤

3. ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮቿ ብቁ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባታል፤

4. የመሪነት ጥሪና ስጦታ ያላቸውን በመለየት ተተኪ እንዲሆኑ ማስታጠቅና ማብቃት የግድ ነው፤

5. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለተሰጣቸው ኀላፊነት ወይም አደራ ለእግዚአብሔርም ለሕዝቡም ተጠያቂነት እንዳለባቸው ማስገንዘብ ከቤተ ክርስቲያን ይጠበቃል። አዲስ ኪዳናዊ የሆነና የምእመናን ተሳትፎ ያለበት የመሪዎች ተጠያቂነት ሥርዐት የሚኀለብትበትን አሠራር ቤተ ክርስቲያን መዘርጋት አለባት።

## ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለችው ተልእኮ ታላቅ ነው። ይህንን ተልእኮዋን እንድትወጣ በተለያየ የመሪነት ስፍራ ያለን ሰዎች ሁሉ ኀላፊነታችን ታላቅ ነው። ይህንን ኀላፊነታችንን ለመወጣት ለሚቀጥለውም ትውልድ የጠነከረች፣ የሰፋች፣ ታላቁን ተልእኮ በትጋት የምትወጣ ቤተ ክርስቲያንን ለማስረከብ ራስን መካድ የእግዚአብሔር የሆነውን ትኩር ብሎ ማየትና ምእመኑን ምሳሌ ሆኖ ማገልገልና መምራት ይጠበቅብናል።

የወደቅንባቸውን ጉዳዮች በመረዳት በእውነተኛ ንስሓና ተሐድሶ ወደ እግዚአብሔር ካልቀረብን ከተጠያቂነትና ከፍርድ አናመልጥም። በአሁኑ ጊዜ በርካታ ምእመናን ከሚታይባቸው ዕውቀት ከተለየው ቅናት ተላቀውና ከባዶ ስሜታዊነት ርቀው በቃሉ መሠረትነት፣ በአእምሮ ብስለትና በመንፈስ ምሪት እንዲመላለሱ ማስተማርና በአግባቡ መምራት ይገባናል። በተጨማሪም፣ በየደረጃው ከአጥቢያ እስከ ቤተ እምነት ድረስ የመንፈስ አንድነትን በመጠበቅ ኅብረትን በማጠንከር እንዲሁም ምድራችንን ለመውረስ የሚያስችል በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ የተመሠረተ የወንጌል ሥርጭት ስልት መቀየስና መንቀሳቀስ ይገባናል።

የቤተ ክርስቲያን ብርሃን ጐልቶ በምድራችን እንዲታይ አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ መሪነትን፣ መልካም አስተዳደርንና የአመራር ልዕቀትን ማሳየት፣ በግልጽነት፣ በትሕትናና በእውነት ምእመናኖቻችንን መምራት ያሻናል። ከጠባብ አመለካከትና ከተሳሳተ ወገንተኝነት መላቀቅ፣ ምንጊዜም ለፍቅርና ለእርቅ ቅድሚያ መስጠት፣ ዕድሎችን በመጠቀም ጊዜውን መዋጀትና በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ተጠያቂነት ያለብን መሆኑንም አምኖ መቀበል ይጠበቅብናል። ከዚህም ጋር ለአገራቸው ዕድገትና ልማት አካልና በረከት እንዲሆኑ ምእመኖቻችንን ማስተማር፣ ማደፋፈርና በሥርዐትና በእውነት መምራት ይኖርብናል። ይህ ሲሆን ብርሃናችን በውስጥም በውጭም ደምቆ ይበራል። ምድራችን ትባረካለች፤ ኢትዮጵያም እጆቿዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።

ክብር ለእግዚአብሔር አብ

ክብር ለእግዚአብሔር ወልድ

ክብር ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሁን!

## “የአመራር ጥራት” ጥያቄዎች

1) በዐዲስ ኪዳን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከተቀመጡት መርሆዎች መካከል ከሎሌ መሪነትን መለማመድና መሥዋዕታዊ ሕይወትን ከመኖር አንጻር ዛሬ ያለው የቤተ ክርስቲያን አመራር እንዴት ይመዘናል?
2) በዐዲስ ኪዳን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከተቀመጡት መርሆዎች መካከል ቃሉን በሚገባ ከመማርና ማስተማር የቤተ ክርስቲያን አንድነት ከማስጠበቅ አንጻር ዛሬ ያለው የቤተ ክርስቲያን አመራር እንዴት ይመዘናል?
3) በዐዲስ ኪዳን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከተቀመጡት መርሆዎች መካከል ምሳሌነት ባለው ሕይወት ከመምራትና ሌሎች መሪዎችን ከማፍራት አንጻር ዛሬ ያለው የቤተ ክርስቲያን አመራር እንዴት ይመዘናል?
4) እንደ ቤተክርስቲያን መሪዎች ከጌታ የተቀበልነውን ሰዎችን ደቀመዝሙር የማድረግን ዋና ተልዕኮ ምን ያህል ትኩረት ሰጥተነዋል? ይህንን ተልዕኮ ቤተክርስቲያን እንድትወጣ ምን ዓይነት አሠራር ልንዘረጋ ይገባናል?
5) ባለ ዐደራ የሆኑ ተተኪ መሪዎችን ማፍራትና ወደ አመራር ማምጣት የምንችለው እንዴት ነው?
6) የቤተ ክርስቲያን አመራር ውጪአዊው አሉታዊው ትኩሳት ሳይነዳው ምዕመናንን በማነጽ በማኅበረሰቡ ላይ በጎ ተጽዕኖ ሊያመጣ እንዴት ይችላል?
7) በአገልጋይ ወይም መሪዎች መካከል በአሁኑ ጊዜ እየተባባሱ የሚታዩት ብርቱ ግጭቶች፣ መካሰሶችና ውንጀላዎች መነሾአቸው ምንድነው? እንዴትስ መፍታት ይቻላል?
8) ከላይ በተነሡ ችግሮች አኳያ፣ ራሳችንን ስንመረምር በግልም ሆነ በጋራ ንስሐ ልንገባባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ምንስ የንስሓ ፍሬ እናሳይ?

# በመሪነት አንጻር ከተሳታፊዎች የተሰጡ የመፍትሔ ነጥቦች

1. መሪዎችን በመልካም ስምና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ ምግባር እንዲገነቡ ማድረግ፤
2. በመጽሐፍ ቅዱስ የተቃኘ ኑሮ፣ የቃሉን ዕሴቶች ያነገበ አመራር መሻትና ማደፋፈር፤
3. በቃል ብቻ ሳይሆን በሕይወትም መገለጥ፣ በማኅበረ ሰቡ ላይ በጎ ተጽእኖ ለማሳረፍ ሁልጊዜም ዝግጁ መሆን፤
4. መሪዎች ተጽእኖን እንዲያመጡ ከውጪአዊ ነገሮች በላይ በቤተ ክርስቲያን ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፤
5. ለማስተማር ብቃት ያላቸውን ወደ መሪነት ማምጣት፤ ጊዜአቸውን ለማንበብና ለማስተማር፣ ለማማከርም እንዲያውሉ በአስተዳደራዊ ሥራ አለማጨናነቅ፤
6. ቤተ ክርስቲያን ከፊታ ላይ ሳይሆን ተከላ ላይ በማተኮረ ከአጎዝ አልፎ ጥራት ላይ ማተኮር፤
7. በክርስቶስ ጤናማ ትምህርት ላይ የታነጹ መሪዎችን ማፍራት፤
8. የመሪዎችን አቅም በማጎልበት ግልጽና ተጠያቂነት ያለበትን አሠራር ማበጀት፤
9. የውጪአዊውን ዓለምም ሆነ የተዛባ አስተሳሰብን ያልኮረጀና ንጹሕ የሆነን አመራር ማጎልበት፤
10. ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ለይታ ማወቅና ለዚያ ዐላማ የሚሆኑና ማስፈጸም የሚችሉ መሪዎችን ማሰናዳት፤
11. ቤተ ክርስቲያን የለውጥ ኀይል የሆኑትን ወጣቶች ማመን፣ እንዲጠጉ መፍቀድና ወደ ኀላፊነት ማውጣት፤
12. ቤተ ክርስቲያን አሳታፊ በመሆን አንድነትን ማስጠበቅ፤
13. ወጥ የሆኑ ትምህርቶችን ማሰናዳትና ማስተማር፤ የጊዜውን ሁኔታ ከሚነካው ስብከት ባለፈ መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶች ላይ ማተኮር፤
14. መሪነትን እንደ ሥልጣን ሳይሆን እንደ ኀላፊነት ማየት፤
15. ራእይ፣ ተልእኮና ግብን ያካተተ መሪነትን ማካሄድ፤ እሳት አጥፊ የሆነን አሠራር ብቻ አለማራመድ፤
16. ዋና የቤተ ክርስቲያን መሪ ለሆነው መንፈስ ቅዱስ ቅድሚያ መስጠትና ጌታ ኢየሱስን እንዲያጎላ መፍቀድ፤
17. ለግጭት ምክንያት የሚሆኑ ምድራዊ አስተሳሰቦችን ወደ መሪነት አለማምጣት፤ አቅምንና ትኩረትንም በትልቁና ገዢው አጀንዳ ላይ ማተኮር፤
18. አገልጋዮች ከስምና ቢሮ ሽሚያ ወጥተው እግዚአብሔርን በመፍራት ለመንጋው የሚመጥን ሕይወትና አገልግሎትን ማካሄድ፤
19. አነስተኛ ኅብረቶችን እንደ ለውጥ ኀይል ማየት፤ የመሪዎችም ግንዛቤ ሕይወት ተኮር እንጂ ፕሮግራም ተኮር እንዳይሆን ሥልጠናና እገዛ ማድረግ፤
20. ሰዎችን ከሚያጎላ የታዋቂነት አባዜ (ሰለብሪቲ ሲንድሮም) በመውጣት ዋጋ ለሚጠይቅ ነገር ሁሉ ቁርጠኛ መሆን፣ ሲያስፈልግም መክፈል፤
21. መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን የራስ ጥቅም ማግኚያ እንደሆነች ሳይቆጥሩ እንደ እግዚአብሔር ወኪል ራሳቸውን መመልከት፤
22. መሪዎች የሚጸልዩ፣ ቃሉን የሚያነቡና መንግሥተ እግዚአብሔር ተኮር እንዲሆኑ ማደፋፈር፣ ሆኖም መገኘት፤
23. የጠፋውን የክርስቶስን ትምህርት መመለስ፤ የክርስቶስን መስቀል የሚያይ ትውልድ ማፍራት፤
24. ስሕተትን ለመስማትና ለመታረም ፈቃደኛ የሆኑ መሪዎች መሆን።

# የተሐድሶ ጥሪ ጉባኤ

## የጋራ አቋም መግለጫ

እኛ ከተለያዩ የወንጌል አማኝ አብያተ ክርስቲያናት፥ የቤተክርስቲያን አጋዥ ድርጅቶችና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የመጣን አገልጋዮች፥ አስተባባሪዎችና መሪዎች "የተሐድሶ ጥሪ:- መመርመር-መመለስ-መታደስ" በተሰኘ ርእስ በቢብሊካ ኢትዮጵያ፣ በደወል የወንጌል አገልግሎት፣ በኢቫንጀሊካል ቲዮሎጂካል ኮሌጅ፣ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን ተማሪዎችና ምሩቃን ማኅበር (ኢቫሱ)፣ በቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማኅበር እና በጎልደን አይል ሚኒስትሪስ የጋራ አስተባባሪነት በአይ.ኢ.ሲ/ኢ.ቲ.ሲ አዳራሽ ከሰኔ 5-6 ቀን 2007 ዓ.ም. በተዘጋጀ ጉባኤ ላይ ተገናኝተን ምክክርና ጸሎት ስናደርግ ቆይተናል። የሕይወት ጥራት፥ የአስተምህሮ ጥራት እና የአመራር ጥራት በሚሉ ሦስት አርእስት ሥር በቀረቡ ጽሑፎች ዙሪያ ዛሬ ቤተክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታ ተመልክተን፥ ልንወስዳቸውም የሚገቡንን ርምጃዎች አጢነን ከዚህ በታች ባጭሩ ያቀረብነው የወል ስምምነታችንን የሚያሳይ የጋራ የአቋም መግለጫ አውጥተናል።

1ኛ. ይህ ጉባኤ ያነሣቸው አሳሳቢ ጉዳዮች በሙሉ የእኛን ወቅታዊ ሁኔታ የሚመለከቱና ከእያንዳንዳችን በተናጠል እንዲሁም በማኅበር ምላሽ የሚጠብቁ መሆናቸውን ተቀብለን መፍትሔውን በጋራ ለመሻት ተስማምተናል።

2ኛ. በምክክር መድረኩ ላይ የቀረቡት ሦስቱም ጽሑፎች አሁን በቤተክርስቲያኖቻችን ውስጥ የሚታዩትን ድካሞቻችንን የሚያንጸባርቁ እንደሆኑና ለእውነተኛ ተሐድሶም የሚጣሩ መሆናቸውን ተገንዝበናል።

3ኛ. የክርስትና ሕይወታችን ጥንካሬና ጥራት በግልም ሆነ በጋራ በአሳሳቢ ሁኔታ እየወረደ መምጣቱን ተገንዝበናል። የጥሞና ሕይወታችንን የምር ለማጠናከር፥ የቤተሰብን ተቋም በቃሉ ትምህርት ለማጎልበት፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነምግባር በሁላችን መካከል እንዲሰርግ አጥብቀን ለመሥራት የቡድናዊነትና የዘረኝነትን ጠንቆች በእውነተኛ ትምህርትና በፍቅር ለመዋጋት፥ ተስማምተናል።

4ኛ. ለብዙ ችግሮቻችን መነሻ ሆኖ ያገኘነው የአስተምህሮ ብልሽት ጥልቅ የሆነ መቃናት እንደሚያስፈልገው አምነናል። በዚህም ረገድ የቃለ እግዚአብሔርን ሥልጣን በእምነታችንም ሆነ በልምምዳችን ላይ ገዢነቱን ማረጋገጥ፥ ተገቢ የአተረጓጎም ስልት በየቤተክርስቲያኖቻችን ማስለመድ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የሁሉ ማእከልነትና የመስቀሉን ዋናነት አጉልቶ ማሳየት እንዳለብን እንዲሁምእውነተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የቃሉ አጋር እንጂ ተጻራሪ አለመሆኑን አጥብቀን መረዳትና ማስረዳት እንደሚገባን ተገንዝበን ይህንኑ ለማድረግ በቁርጠኝነት ተስማምተናል።

5ኛ. የቤተክርስቲያን አመራር ዐዲስ ኪዳናዊ ዘይቤን ተከትሎ ሎሌነትን፥ ምሳሌያዊነትን፥ ተጠያቂነትን፥ የሥራ ትጋትንና መሥዋዕታዊነትን የመሰሉ ባሕርያትን ያገናዘበ እንዲሆን እራሳችንን በዚህ መሥመር እየቃኘን ኀላፊነታችንን ለመወጣት ዝግጁ መሆን እንዳለብንና ተገቢ የማስተካከያ ርምጃዎች መውሰድ እንዳለብን ተስማምተናል።

6ኛ. ልዩ ልዩ መገናኛ ብዙኀንን በተለይም የቴሌቪዥን ሚዲያን በመጠቀም እውነተኛውን ወንጌልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በሕዝባችን ውስጥ ለማስረጽ ቤተእምነቶችና ሌሎችም ክፍሎች ሀብታችንንና ችሎታችንን በቁርጠኝነት ለዚህ ዐላማ በማስተባበር የሚቻለንን ሁሉ ለማድረግ ተስማምተናል።

7ኛ. ቃሉ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በብርቱ ፈልጉ እንደሚል በግልም በማኅበርም ለቤተክርስቲያን የተሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች በመካከላችን እንዲነሣሡ፥ በሙላትም እንዲገለጡ መጸለይ፥ ሲገለጡም ለጋራ ጥቅም ይሆኑ ዘንድ በአግባብና በሥርዐት ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀውን ኀላፊነት ለመወጣት ተስማምተናል።

8ኛ. በዚህ የተሐድሶ ጥሪ ረገድ ራስን መመርመር፥ መመለስና መታደስ በግልም በቤተክርስቲያንም ደረጃ ሕያው ባህል ይሆን ዘንድ የሚቻለንን ሁሉ እንደቃሉ ለማድረግ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጥሪውን ለማስተጋባት በሙሉ ልባችን ተስማምተናል።

እግዚአብሔር የገባነውን ቃል እንድንጠብቅ ይርዳን።

ክብር ለአብ፣

ክብር ለወልድ፣

ክብር ለመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሁን!

አሜን!